


‘ ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ ኣለው፤ በሥጋ ውስጥ ያድራል፤ ’
ለሚለው ኑፋቄ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ።

ዘላለም መንግሥቱ




‘ ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ በሥጋ ውስጥ ያድራል፤ ’
ለሚለው ኑፋቄ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ።

ዘላለም መንግሥቱ

# ሰው ምንድር ነው?

‘ሰው መንፈስ ነው፣ ነፍስ አለው፣ በሥጋ ውስጥ ያድራል፣’ ለሚለው ኑፋቄ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ።

ዘላለም መንግሥቱ (© ፳ሺህ፲ ፫ ዓመተ ምሕረት)

ይህን መጽሐፍ ባለቤትነቱን ሳይወስዱና ለሽያጭ ሳያውሉ ጸሐፊውን በማሳወቅ ማባዛትም ማሰራጨትም ይፈቀዳል።
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት ከ፲፱፻፶፬ ዓ. ም. የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ካሳተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።
የሽፋን ገጽ ቅንብር፣ ዘመን ግራፊክስ።

* * * * * *

# What is Man?

A Biblical Response to the ‘Man is Spirit, Has a Soul, Lives in a Body’ Heresy

Zelalem Mengistu (© 2021)

This work can be reproduced and disseminated by only notifying the author, without claiming ownership and so long as it is not for profit.
All Scripture quotations are from the 1962 edition of the Amharic Bible published by the Bible Society of Ethiopia.
Cover Design: Zemen Graphics

መድረክ ዕዝራ
ለጌታ ቃል እና ለቃሉ ጌታ ታማኝ በመሆን
ezra forum
being true to the Word of God and the God of the Word

# ማውጫ


መግቢያ 5

ሰው ምንድር ነው? 7

መንፈስስ ምንድር ነው? 11

የስሕተቱ ምንጭ 13

'ሰው መንፈስ ነው' በአገራችን ሲጀመር እና ዛሬ፤ 14

አሐዳስ እና አምስቱ ቢሮዎች፤ 18

የ'ሰው መንፈስ ነው' ትልልቅ አደጋዎች፤ 19

አደጋ አንድ፥ መንፈስ ስለሆንን አንረክስም፤ 19

አደጋ ሁለት፥ እኛ አማልክት ነን፤ 23

ኮራጆች 32

ስም መጥራት 34

'አማልክት ናችሁ።' 39

የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ መሆን መለኮት ያአደርገናል? 44

ሀ. መለኮት 45

ለ. ባሕርይ 47

ሐ. ተካፋይ 50

ከመንፈስ መወለድ መናፍስት ያደርገናልን? 52

ከመንፈስ መወለድ ዳግም ልደት እና መንፈሳዊነት ነው። 59

ሰው አምሳለ አምላክ፥ መልክዓ አምላክ ነው። 66

ሰው በስዕላዊ ሞዴል ሲታይ፤ 67

ሰው ሁለንተናው ነፍስ ወይም መንፈስ ሲባል ምን ማለት ነው? 71

አሳቾች ንስሐ መግባት የለባቸውም? 7

መደምደሚያ፤ ሰው ሰው ነው፤ ዛሬም፥ ነገም፥ ለዘላለምም። 81

ዋቢዎች፤ 83

## መግቢያ




የዚህች መጽሐፍ መነሻ በ2017 ሜይ ወር የጻፍኩትና በዕዝራ የኢንተርኔት መጽሔት የበተንኩት፥ ‘ሰው መንፈስ ነው? ወይስ ሰው ነው?’ የሚል መጣጥፍ ነው። ያንን ጽሑፍ የጻፍኩት በጊዜው ይህ ትምህርት እየተነዛ ነበርና፥ ከበርካታ ሰዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ተጠይቄ፥ አንድ የተጻፈ ነገር በእጃቸው እንዲኖራቸው በማሰብ ነው። የመጀመሪያውን ጽሑፍ ከጻፍኩ በኋላም በርካታ ጥያቄዎች በየጊዜው እየተጠየቅሁ አጫጭር ምላሾች ስሰጥ ቆይቻለሁ። የመጀመሪያው ጽሑፍ ተደራሾች ጥቂት ሺህ ሰዎች ብቻ ስለነበሩ፥ በማኅበራዊ ገጾች ማካፈል አስፈላጊ ስለመሰለኝ በቪድዮ በሰባት ተከታታይ ክፍሎች አዘጋጅቼ አቀረብኩት። በቪድዮ የቀረበባቸው ገጾች ምንጮች በመጽሐፉ መጨረሻ በዋቢ መጻሕፍት ገጽ ይገኛሉ።

ለቪድዮ ትምህርት ማስታወሻ ጽሑፎች ሳዘጋጅ ቀድሞ በነበረው ጽሑፍ በብዙ ጨምሬበት ስለነበረ፥ ደግሞም በየጊዜ የመለስኋቸው ጥያቄዎችም እየተጨመሩበት ያ የመጀመሪያው መጣጥፍ ስለዳበረ በመጽሐፍ መልክ ቢቀርብ ሌሎችን ሊጠቅም እንደሚችል በማመን በዚህ መልኩ እንደገና ቀርቧል። ይህ ሥራ ከቪድዮው ቃል በቃል ተገልብጦ በመጠነኛ አርትዖት እንደገና የተዘጋጀ ነው።

አንዳንድ ጥያቄዎች መልሳቸው ገሐድ ስለሆነ ሞኝ ጥያቄዎች ይመስላሉ። ‘ሰው ሰው ነው? ወይስ መንፈስ ነው? ሰው ሰው ነው? ወይስ ሰው ወይስ እግዜር ነው?’ ብሎ መጠየቅ ጅልነት ይመስላል። ምክንያቱም፥ ነገሩ ገሐድ ነዋ! ይሁን እንጂ፥ ጥያቄው እንዲጠየቅ ግድ የሚያደርጉ ነገሮች ሲፈጠሩ፥ ሰው ሰው አይደለም የሚሉ ስሕተቶች ሲናኙ፥ ‘ሰው መንፈስ ነው፤ ሰው እግዜር ነው፤ እኔና አብ አንድ ነን፤ እኔ የእግዚአብሔር ዓይነት ነኝ፤’ የሚሉ ስሕተቶች ሲነገሩ፥ እውነት እየመሰሉ ሲመጡ፥ ያኔ ሞኝ ጥያቄ መጠየቅ ግድ ይሆናል። ‘ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ በሥጋ ውስጥ ያድራል’ ሲባል መስማት በወንጌላውያን አማኞች አካባቢ አዲስ አይደለም።

ይህ የዘመናዊዎቹ የስሕተት ትምህርቶች ሁሉ እናት በሆነችው በአሜሪካ ውስጥ የተወለደ፥ እዚያው አሜሪካ ጡጦ ጠብቶ ያደገና በዓለም ዙሪያ የተወነጨፈ፥ ጥቂት ያልሆኑ ሰዎች በማደጎ የራሳቸው ልጅ ያደረጉት፥ በእውቀትም፥ ያለ እውቀትም፥ በስሕተትም፥ በመታለልም፥ የተቀበሉት፥ ያሳደጉት የስሕተት ትምህርት ነው። ይህ 'ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ በሥጋ ውስጥ ያድራል' የሚባለው ነገር የቃለ እምነት ስሕተት የተጣረሰ ስነ ሰብእ ነው።

እንደዚህ ያለ አሳችና አሳሳች ነገር በመኖሩ፥ 'ሰው ምንድርን ነው?' ተብሎ መጥጠየቅ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊው የሰው ማንነት ትምህርት መገለጥ አለበት። በአገራችን ይህንን ስሕተት ከመንዛት ጋር የሚቆራኙ ጥቂት ሰዎች ቢኖሩም ምንጩ ግን እነርሱ አይደሉም። ከማን ተኮረጀ? ከየት መነጨ? ያንንም እንመለከተዋለን።

ይህ መጽሐፍ በማተሚያ ቤት አልታተመም። በፒዲኤፍ በነጻ እንዲታደል የተዘጋጀ ነው። በቪድዮ የተላለፈው ተከታታይ ትምህርት ድምጽ ወደ ጽሑፍ ከተመለሰ በኋላ፥ ከጽሑፉ ጋር አብሮ የሚሠራጨውን ኦዲዮ በማንበብ የተሳተፉ በርካታ (ከኔ ጋር ሌሎች 10 ወንድሞችና እኅቶች ይገኛሉ። እነርሱም፥ ነቢዩ መንገሻ፥ ተመስገን ሳህሌ፥ ኮነ ፍስሐ፥ ፌቨን መኮንን፥ ስንታየሁ አስፋው፥ ሙሉቀን መለሰ፥ ስንታየሁ በቀለ፥ ርብቃ ላቀው፥ ራሔል አሰፋ፥ እና ነቢየልዑል አፈወርቅ ፍስሐ ናቸው። ሁሉንም ከልብ አመሰግናለሁ፤ ጌታ በብዙ ይባርካቸው።

መልካም ንባብ፤ መልካም ማድመጥ።

ዘላለም መንግሥቱ።

## ሰው ምንድርን ነው?

'ሰው *መንፈስ ነው፤* ነፍስ አለው፤ *በሥጋ* ውስጥ *ያድራል'* ወደሚለው ስሕተት እና ሐሳውያኑ ስለሚያቀርቧቸው አሳሳች አጠቃቀሶች ከመግባቴና ስሕተቱን ከመግለጤ በፊት ግን በቅድሚያ ትክክለኛውን፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ትምህርት በአጭሩ እንመልከት። ይህንን የምጀምርበትን ትምህርት መደምደሚያውም አደርገዋለሁ።

ሰው ምንድርን ነው? በአጭሩ፥ ሰው ሰው ነው። ሰው ሲፈጠር ሰው፥ ሲኖር ሰው፥ ሲሞት ሰው፥ ከሞት በኋላም እንኳ፥ በትንሣኤም ሰው ሰው ነው። ካላወቅን እንወቅ፤ ሰው ሰው ነው። ሰው ከሌሎች አካላውያን ፍጡራን ሁሉ የላቀና የፍጡራት ሁሉ ቁንጮ የሆነ ፍጡር ነው። የፈጣሪያችን የእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ መሆናችን ብቻውን እንዴት የከበረ ነገር ነው! ያ ሰው ሆነን በመልኩ እንደ ምሳሌው መፈጠራችን ልካችን ነው፤ ያልበዛ፥ ያልተንዛዛ፥ ያላነሰ፥ ያልጎደለ ልካችን። ሰው መሆን በልካችን የተሠራ ማንነታችን ነው። ሰው ሲፈጠር ሰው ነው፤ በምድር ሲመላለስም ሰው ነው። ከውድቀት በፊት ሰው፥ ከውድቀት በኋላም የእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የሆነ ሰው ነው፤ ዘፍ. 1፥26-27፤ 2፥7፤ 9፥6። ከውድቀት በኋላም፥ ማለትም ከዘፍ. 3 በኋላም የሰውን ሰውነት ኃጢአት በከለውና ከአምላኩ ለየው እንጂ ሥሪቱ አልተቀየረም። የሰው ሰውነት ወይም ማንነት ዘላለማዊ ነው። ሰው ለዘመን ብቻ ሳይሆን ለዘላለምም ሰው ነው።

ሰው መንፈስ ነው የሚሉ ሰዎች ከጅምሩ የተሳሳቱ መሆናቸውን የጅምሩ መጽሐፍ ያረጋግጥልናል። ሰው በውስጡ መንፈስ አለ እንጂ መንፈስ አይደለም። ሰው መንፈስ ቢሆን ኖሮ፥ ገና ሲፈጠር እግዚአብሔር፥ መንፈስን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር ይል ነበር። ቃሉ ግን፥ በዘፍ. 1፥26፤ *እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን* [መንፈስን አይደለም፤ ሰውን] *በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ።* ይላል። 'እንፍጠር' ያለው መንፈስን ሳይሆን ሰውን ነው። ቁጥር 27 ደግሞ፥ *እግዚአብሔርም ሰውን* [መንፈስን አይደለም፤ ሰውን] *በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።* ይላል። በመልኩ የፈጠረው ሰውን እንጂ መንፈስን አይደለም። ወንድም ሴትም በመልኩ የተፈጠሩ ሰዎች ናቸው። ሰዎች ሰዎች ናቸው፤ መናፍስት ወይም መንፈሶች አይደሉም።

በዘፍ. 2፥7 *እግዚአብሔር አምላክም ሰውን* [መንፈስን አይደለም፤ ሰውን] *ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም* [መንፈስ

አይደለም፤ ሰው] *ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።* ይላል። ይህ እዚህ ዘፍ. 2፥7 ላይ የተብራራው ያ እዚያ ዘፍ. 1፥26-27 የተፈጠረው ነው። ሰው እዚያ በስድስት ቀናት ሁሉ ነገር ሲፈጠር የተፈጠረበትን፥ የተሠራበትን፥ የተበጀበትን መንገድ መናገሩ እንጂ ሌላ ታሪክ አይደለም። አንዳንድ አሳቾች ይህንን የሰው አፈጣጠር ምንባብ እንደ ሌላ ፍጥረት፥ እንደ ሌላ *ሥሪት* አድርገው፥ ወይም ከተፈጠረ በኋላ ሌላ ተጨማሪ ንጥረ ነገር እንደተገጠመለት አድርገው ሊያቀርቡ ይሞክራሉ። ዘፍ. 2፥7 የዘፍ፣ 1፥26-27 ከሳችና ማብራሪያ ብቻ ነው። እዚያ ሰው ተፈጠረ፤ እዚህ ደግሞ እስትንፋስ እፍ ስለተባለበት ሕያው ነፍስ ሆነ ይላሉ። ስሕተት ነው። ከሆነም ደግሞ፥ ሰው ነፍስ ነው ማለት ነው የነበረባቸው እንጂ፥ መንፈስ ነው ማለት አልነበረባቸውም። አሳቾቹ ነፍስ አለው ከማለት ይልቅ 'ሰው ነፍስ ነው' ቢሉ ነበር የሚቀርበው። ምክንያቱም፥ *ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።* ስለሚል። መንፈስ ሩኻ ወይም ሩዋኽ ነው የሚባለው በዕብራይስጥ። ዘፍ. 1፥2 ላይ ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ የሚለው *רוּחַ אֱלֹהִים* ሩኻ ኤሎሂይም ወይም ሩዋኽ ኤሎሂይም ነው። በአማርኛም ሩህ እንላለን። ከዚያ የመጣ ነው። ሕያው ነፍስ ሆነ የሚለው ግን ኻያህ ኔፌሽ *חַיָּה נֶפֶשׁ* ነው። በዕብራይስጥ ኔፌሽ በአማርኛ ነፍስ ነው። ይህም ከዚያ የመነጨ ነው። ስለዚህ ሰው መንፈስ አይደለም። ነፍስም አይደለም፤ ሰው ሰው ነው እንጂ።

ከዚህ ክፍል የምንረዳው ሰው ወይም የሰው አፈጣጠር በመጀመሪያ መንፈስ ተፈጥሮ ያ መንፈስ *ሥጋ* ሲመረግበት አይደለም። ሰው ከአፈር ተፈጥሮ ከዚያ ከእግዚአብሔር የሕይወት እስትንፋስ እፍ ሲባልበትና ሕያው ነፍስ ያለው ሲሆን ነው። ልብ እንበል፤ ነፍስም አልተባለም፤ 'ሕያው ነፍስ ያለው' ሆነ። ሕያው ነፍስ ያለው ምን? ሕያው ነፍስ ያለው ሰው። የተፈጠረው ሰው ነዋ! ሕያው ነፍስ ያለው መንፈስ አልተባለም። ሰውን በተመለከተ፥ 'መንፈስ' የሚለው ቃል በዚህ ሰው በተፈጠረበት ታሪክ ውስጥ ጨርሶም የለም። ስለዚህ የመጀመሪያው ሰው አዳም፥ ምንድርን ነው? ሰው ነው። የመጀመሪያዋ ከአዳም አጥንት የተሠራችው ሴትም ምንድርን ናት? ሰው ናት፤ ሴት ሰው፤ በጾታ ሴት የሆነች ሰው።

የማስተምረው ስለ ሰው ሰው-ነት፥ ወይም ሰው ሰው ስለመሆኑ ነው። ከላይ ስለ ሞኝ ጥያቄ እንዳልኩት አንዳንድ ጊዜ፥ መነገር እስከማይገብባቸው ድረስ ግልጽ የሆኑ ነገሮችን እንድንናገር የሚያደርጉት ግልጹን የሚሰውሩ ሰዎች ናቸው። ሰው ሰው መሆኑ በጣም ግልጽ የሆነ እውነት ሆኖ ሳለ ሰውን ሰው አይደለም፤ ሰው መንፈስ ነው የሚሉ አሳቾች ቀድሞም ግልጽ የሆነውን ነገር እንደገና እንድንናገረው ያደርጉናል። እነዚህ ሰዎች ሰው ሰው መሆኑ ግልጽ ሆኖ ሳለ፥ 'ሰው መንፈስ ነው እንጂ' በማለት ጥቅስ እየገመዱና እያጠናገሩ ሰውን ያደናግራሉ፤ ያደናቁራሉ። 'ሰው መንፈስ ነው' ሲሉ፥ ሰው ሰው አይደለም ማለታቸው ነው።

ሰውን መንፈስ የሚያሰኙት ሰዎች ከአፈጣጠሩ የሚወስዱት አሳብ በመልኩና በምሳሌው መፈጠሩን ነው። ያም፥ 'እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ ሰው በመልኩና በምሳሌው ከተፈጠረ ሰውም መንፈስ መሆን አለበት' ነው። መነሻቸውና ድምዳሜያቸው ወይም መድረሻቸው ይህ ነው። ግን በግልጽ ከተጻፈው እውነት ነው የምንንደረደረውና፥ እግዚአብሔር ሰውን ነው በመልካችንና በምሳሌያችን እንፍጠር ያለው እንጂ መንፈስን አይደለም። ስለዚህ ያ የተፈጠረው ነገር፥ ማለትም ሰው፥ የፈጣሪው ምሳሌና መልክ አለው ማለት ነው እንጂ ትንሽ እግዜር አልተፈጠረም። ሰው ነው የተፈጠረው።

መልክና ምሳሌው መንፈስነቱ ከሆነ ደግሞ፥ የተፈጠረው ሰው አካል ስላለው፥ ሥጋ ስላለው፥ ቁስ ስለሆነ፥ እንዲህም ሆኖ አምሳል ስለሆነ፥ የአምሳሉ፥ የመልክና ምሳሌው ምንጭ የሆነው እግዚአብሔርም አካልና ቁስ ነው ማለት ነው፤ ወይም አካልና ቁስ ሊሆን ነው ማለት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔርም አካል አይደለም፤ ቁስም አይደለም። ስለዚህ የሰው መልክና ምሳሌነት፥ መንፈስነት ሳይሆን ሰው ሳለ አምላኩን መምሰሉ ነው።

እንዴት ነው የሚመስለው? በብዙ ዘርፎች ነው ሰው ፈጣሪውን የሚመስለው። ገዢ መሆኑ፥ እውቀትን የሚያውቅ መሆኑ፥ መንፈስ ስላለውና፥ ከአምላኩ ጋር ግንኙነት ስለሚያደርግ፥ ወዘተ። ሰው ሲፈጠር መንፈስ ሳይሆን መንፈስ ያለው ወይም መንፈሳዊ ፍጡር ነው። ሰው ሲፈጠር በሥጋ ውስጥ የሚያድር መንፈስ ሳይሆን፥ በሥጋው ውስጥ፥ በሰውነቱ ውስጥ፥ በውስጡ ሕያው ነፍስም መንፈስም ያለው ሰው የተሰኘ፥ ሰው የተባለ፥ ሰው የሆነ ፍጡር ነው። ከሌሎች አካል ካላቸው ፍጥረታት ሁሉ የተለየና ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት፥ ግንኙነት ማድረግ የሚችል፥ ማምለክ፥ ለእግዚአብሔር ምላሽ መስጠት የሚችል ፍጥረት ሰው ብቻ ነው። አካል ካላቸው ፍጥረታት ሁሉ ያልኩት መላእክትን ከስሌቱ ውስጥ ለማውጣት ነው። መላእክት መናፍስት ወይም አካል የለሽ ፍጡራን ናቸው። መንፈስ ማለት በፍጥረቱም፥ በትርጉሙም ረቂቅ፥ አካል አልባ፥ ቁስ ወይም ቁሳዊ ያልሆነ ማለት ነው። መንፈስ ቁሳዊ አይደለም፤ ቁስም የለውም። ሰው መንፈስ ነው ሲባል የዚህ ትርጉም ተቃራኒ ነው። ሰው መንፈስ ነው ማለት ቁስ የለውም፥ አካል የለውም ማለት ነው። ይህ በራሱ ተቃርኖ ነው። ትምህርቱን ስሑት የሚያደርገው አንድ ነጥብም ይህ ነው።

ከላይ እንዳየነው፥ እግዚአብሔር በመጀመሪያ መንፈስን አልፈጠረም፤ አዳም መንፈስ አልነበረም። ሔዋንስ? ሔዋንም ከሥጋ የተገኘች ሥጋ እንጂ መንፈስ አልነበረችም። የሔዋንንም አፈጣጠር እንመልከት፤ ዘፍ. 2፥23፤ *አዳምም አለ፦ ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፥ ሥጋም ከሥጋዬ ናት፤ እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል።* ነው የተባለው። በቀዳሚ ጽሑፉ፥ 'ከኢሽ ተገኝታለችና ኢሻ ትባል' ነው የሚለው።

*ደግሞም፥ ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፥ ሥጋም ከሥጋዬ ናት፤* ነው ያለው እንጂ፥ 'ይህች መንፈስ ከመንፈሴ ናት' አላለም። እግዚአብሔር በመጀመሪያ መናፍስትን አልፈጠረም። ሰዎችን ነው የፈጠረው። *አጥንት ከአጥንቴ፥ ሥጋም ከሥጋዬ።*

ሰው *ሥጋና* አጥንት አለው። አዳም *ሥጋና* አጥንት ካለው፥ ሔዋን *ሥጋና* አጥንት ካላት አዳምና ሔዋን ሰዎች ናቸው እንጂ መንፈሶች አይደሉም። መንፈስ *ሥጋና* አጥንት የለውም። መንፈስ *ሥጋና* አጥንት እንደሌለው የነገረን ጌታ ኢየሱስ ራሱ ነው። ከትንሣኤው በኋላ በዚያው በተነሣበት ቀን ወደ ኤማሁስ ይሄዱ ከነበሩት ከነቀለዮጳ ጋር ከሄደ፥ ወደ ቤታቸው ከገባ በኋላ፥ እራት አብረው ሲበሉ፥ እንጀራ ቆርሶ ሲሰጣቸው፥ ዓይናቸውም ተከፈተ፥ አወቁትም፤ እርሱም ከእነርሱ ተሰወረ። (ሉቃ. 24፥31)። እነዚህ ሰዎችም በዚያች ሰዓት ተነሥተው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ ሲመለሱም አሥራ አንዱና ሌሎችም ከነሱ ጋር ተሰብስበው ስለ መነሣቱ ሲያወሩ አገኟቸውና የሆነውን ተረኩላቸው። ከቁጥር 36-39 ያለውን በቀጥታ እናንብበው፤

> 36-39፥ ይህንም ሲነጋገሩ ኢየሱስ ራሱ በመካከላቸው ቆሞ፦ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። ነገር ግን ደነገጡና ፈሩ <u>መንፈስም ያዩ መሰላቸው።</u> እርሱም፦ ስለ ምን ትደነግጣላችሁ? ስለ ምንስ አሳብ በልባችሁ ይነሣል? እኔ ራሴ እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ፤ በእኔ እንደምታዩት፥ <u>መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና</u> እኔን ዳሰሳችሁ እዩ አላቸው።

*መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳሰሳችሁ እዩ።* ቀደም ሲል ባየነው በዘፍ. 2፥23 አዳም ምን አለ? *አዳምም አለ፦ ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፥ ሥጋም ከሥጋዬ ናት፤ እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል።* ሔዋን አጥንትና *ሥጋ* ነበራት፤ አጥንትና *ሥጋ*ዋም የተሠራው ከአዳም ነው፤ ስለዚህ፥ ሔዋን *ሥጋና* አጥንት ከነበራት ወይም ስለነበራት መንፈስ አይደለችም። *ሥጋና* አጥንቷ የተገኘው ደግሞ ከአዳም ከሆነ፥ አዳም *ሥጋና* አጥንት አለውና እርሱም መንፈስ አይደለም። ሰው መንፈስ ነው የሚሉ ሰዎች የሚፎርሹት ገና ከመጀመሪያው፥ ከፍጥረትም ጅማሬ ነው ማለት ነው።

ከኛ ከራሳችን ማንነት ተነሥተን ወደ ኋላ በመሄድ እነአዳምን እንፈትሽ ካልን፥ እነአዳም ሲፈጠሩ ከኃጢአትና የኃጢአት መዘዝ ከሆነው ነገር ሁሉ በቀር ልክ እንደ እኛ ያሉ ናቸው። እኛ *ሥጋ* አለን? አዎን፤ አለን። አጥንትስ አለን? በእርግጥ አለን። ካልካድን በቀር። እኛ *ሥጋና* አጥንት፥ *ሥጋና* ደም የሆንን ሰዎች ነን፤ ስለዚህ መናፍስት አይደለንም። እኛ መናፍስት ያልሆንነው እነ አዳምም መናፍስት ስላልነበሩ ነው። ስለዚህ ሰው ምንድርን ነው? ሰው ሰው ነው። ሰው፥ ሰው ነው።

## *መንፈስስ ምንድር ነው?*

መንፈስ የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ብዙ ተጠቅሷል። የእግዚአብሔር መንፈስ፥ መንፈስ ቅዱስን ያሳያል። መላእክትን እና አጋንንትን ወይም ርኩሳን መናፍስትንም ያመለክታል። የሰውን መንፈስ ወይም በሰው ውስጥ ያለውን መንፈስም ያሳያል። እዚህ የምንካፈለው ስለ ሰው መንፈስ ስለሆነ እሱ ላይ እናተኩራለን።

ሰው መንፈስ እንዳለው እንጂ ሰው መንፈስ መሆኑን የሚናገር ትምህርት በብሉይ ኪዳን ውስጥ አይገኝም። የሰው መንፈስ የሰውን ውስጣዊ ማንነትም ያሳያል፤ መዝ. 51፥10 አቤቱ፥ *ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፥ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ።* ይላል። እዚያው ቁጥር 17 *የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው፥ የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም።* ይላል። ሁለቱም መንፈስና ልብ በተመሳስሎት ተጣምረው፥ አንዱ ሌላውን በሚገነባ አጻጻፍ ቀርበዋል።

ብሉይ ኪዳን ስለ ሰው መንፈስ ይናገራል፤ ሲናገር ግን በሰው ውስጥ ስላለ መንፈስ እንጂ ሰው ራሱ መንፈሱ መሆኑን አይናገርም። የማይናገረው ደግሞ ቃላት አጥረውት ወይም አፍሮ አይደለም። እውነቱ ያ ስለሆነ እንጂ! ለምሳሌ፥ ምሳ. 20፥17 *የሰው መንፈስ የእግዚአብሔር መብራት ነው የሆዱን ጒርጆች ሁሉ የሚመረምር።* ሲል፥ መንፈስ ሰው መሆኑን ወይም ከሰው ጋር እኩል ነገር መሆኑን ሳይሆን በሰው ውስጥ የሚገኝ መሆኑን አመልካች ነው።

ሌሎችም በርካታ ስፍራዎች ይህን ያሳያሉ፤ መንፈስህ (ያንተ መንፈስ) በእኔ ላይ ሁለት እጥፍ ይሆን ዘንድ እለምንሃለሁ፤ የኤልያስ መንፈስ በኤልሳዕ ላይ ዐርፎአል፤ የአሦርን ንጉሥ የፎሐን መንፈስ፥ የአሦርንም ንጉሥ የቴልጌልቴልፌልሶርን መንፈስ አስነሣ፤ የቂሮስን መንፈስ አስነሣ፤ እግዚአብሔርም የይሁዳን አለቃ የሰላትያልን ልጅ የዘሩባቤልን መንፈስ፥ የታላቁንም ካህን የኢዮሴዴቅን ልጅ የኢያሱን መንፈስ፥ የቀሩትንም ሕዝብ ሁሉ መንፈስ አስነሣ፤ ወዘተ፥ ሲል ኤልያስ፥ ፎሐ፥ ቂሮስ፥ ዘሩባቤል፥ ወዘተ፥ ሰዎቹ ናቸው፤ መንፈሱ የሰውየው ወይም በሰውየው ውስጥ ያለው ነው። የእገሌ በሚለው ውስጥ 'የ' የሚለው አመልካች ባለቤቱን የሚያሳይ ነው። ሰውየው ራሱ መንፈስ መሆኑን ሳይሆን መንፈሱ የሰውየው መሆኑን አመልካች ነው። ሰው መንፈስ መሆኑን ብሉይ ኪዳን አይናገርም።

ብሉይ ኪዳን ማለት እኮ ሰው የተፈጠረበት ታሪክ ያለበት የመጽሐፍ ቅዱሳችን ክፍል ነው። በዚያ የፍጥረት መጽሐፍ ሰው መንፈስ መሆኑን ሳይሆን መንፈሱ በሰው ውስጥ ያለ ወይም የሚገኝ መሆኑን ነው የምናገኘው። ሰው መንፈስ ቢሆን ኖሮ ብሉይ ኪዳን አሳምሮ፥ ሳይንተባተብና የዘንድሮዎቹ መጥተው እስኪፈቱልን ምስጢርና ድብቅ

አድርጎ አሸን ሳያስቀምጥልን፥ በግልጹ ቋንቋ ሰው መንፈስ ነው ይለን ነበር። ብሉይ ኪዳን ግልጽ ነው።

ጥቂት ጨምረን ለማየት፥ ዳን. 7፥15 *በእኔም በዳንኤል በሥጋዬ ውስጥ መንፈሴ ደነገጠች፥ የራሴም ራእይ አስቸገረኝ።* ይላል። ይህ የመንፈስን መገኛ ያሳያል። ዘካ. 12፥ 1 ደግሞ፥ *ስለ እስራኤል የተነገረ የእግዚአብሔር ቃል ሸክም ይህ ነው። ሰማያትን የዘረጋ፥ ምድርንም የመሠረተ፥ የሰውንም መንፈስ በውስጡ የሠራ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡-* ይላል። *የሰውንም መንፈስ በውስጡ የሠራ!* እንግዲህ የሰው መፈጠር ታሪክ መገኛ የሆነው ብሉይ ኪዳን የሰውን መንፈስ እንዲህ ነው የሚገልጠው። በብሉይ ኪዳን አንዴም ሰው ሰው ብቻ እንጂ መንፈስ መሆኑ አልተጻፈም። የሰው መንፈሱ በውስጡ የሚገኝ የማንነቱ ክፍል ነው።

በአዲስ ኪዳንም ሰው መንፈስ ነው ተብሎ አልተነገረም።

ሮሜ. 1፥9 *በልጁ ወንጌል በመንፈሴ የማገለግለው እግዚአብሔር ምስክሬ ነውና፤* ይላል፤ 'በ' የሚለው አያያዥ የሚያሳየው ሰው እራሱ መንፈስ መሆኑን ሳይሆን መንፈስ በሰው ውስጥ ያለ መሆኑን ነው።

1ቆሮ. 2፥11 *በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም።* ሰው መንፈስ ሳይሆን በሰው ውስጥ መንፈስ አለ ነው የሚለን። *በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር* ሲል፥ 'ከ' የሚለው አያያዥ የሚያሳየው ሰው እራሱ መንፈስ መሆኑን ሳይሆን መንፈስ በሰው ውስጥ ያለ መሆኑን ነው።

2ቆሮ. 2፥12 *ስለ ክርስቶስም ወንጌል ወደ ጢሮአዳ በመጣሁ ጊዜ፥ ለጌታ ሥራ በር ምንም ቢከፈትልኝ፥ ቲቶን ወንድሜን ስላላገኘሁት መንፈሴ ዕረፍት አልነበረውም።* መንፈሴ ሲል የእኔ መንፈስ ማለቱ ነው። በውስጤ ያለው መንፈስ ማለቱ ነው። መንፈሱ እርሱ መሆኑን ሳይሆን መንፈሱ በውስጡ፥ በሰውየው ውስጥ መኖሩን ነው የሚናገረው።

1ተሰ. 5፥23 *የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ።* ጳውሎስ በጻፈበት ቋንቋ ይህ አሳብ፥ ሁለንተናችሁና ሙሉ በሙሉ ወይም ፈጽሞ የሚለው አብረው ነው የተጻፉት። ሁለመናችሁ ምንም ሳይቀር ማለት ነው። ይህ የሚያሳየን መንፈስ፥ ነፍስ እና ሥጋ፥ 'ሁለንተናችሁ' የተባለው የሰው ማንነት

ውስጥ የተካተቱ ክፍሎች መሆናቸውን እንጂ ሰው መንፈስ መሆኑን ነፍስ ያለውና በሥጋ ውስጥ የሚያድር መሆኑን አያሳይም።

## የስሕተቱ ምንጭ

ወደ ስሕተቱ ትምህርት መግለጥ እንለፍ። ታዲያ ይህ ሰው መንፈስ ነው የሚል ትምህርት ከየት መጣ? ለምንስ መጣ? ከላይ ይህ ስሕተት ሰዎች የራሳቸው የማደጎ ልጅ ያደረጉት የስሕተት ትምህርት ነው ብያለሁ። በምዕራቡ ዓለም ይህ ስሕተት የቆየ ነው። ብዙ አሥርታት አስቆጥሯል። በአገራችንም ዓመታት አስቆጠረ። ስር ሳይይዝ ጠወለገና የጠፋ መሰለ እንጂ ቀደም ሲል ዘሩ የተዘራበት ጊዜ ነበረ፤ ይህንን ኋላ አነሣዋለሁ።

በምዕራቡ ዓለም በአንድ ከረጢት ውስጥ የታጨቁ በሽተኛ የሆኑ የከፉ ትምህርቶች አሉ። ከረጢቱ የቃል-እምነት፥ ወይም ቃለ እምነት ወይም Word of Faith ይባላል። ቃለ እምነት፥ ቃልም ያልሆነ፥ እምነትም ያልሆነ መርዝ ነው። በሽታ ነው፤ ደዌ። የሚቀበሉት ሰዎችም መንፈሳዊ ድውያን ናቸው። ቃለ እምነት የሚሉት ነገራቸው፥ 'ቃልህ አምነህ ካልከው፥ የፈለከውን ነገር መፍጠር ይችላል። እግዚአብሔርም ራሱ እንኳ የፈጠራቸውን ፍጥረታት ሲፈጥር ቃሉ እንደሚፈጥር ያምን ነበር፤ እምነት ነበረው፤' ይላሉ። እግዚአብሔርም እንኳ በቃሉ ላይ ይታመን ነበር ይሏችኋል! ይታያችኋል? እግዚአብሔር ሲታመን! መታመን በሌላ ከራስ በላይ በሆነ ነገር መደገፍ ነው። እግዚአብሔር በሌላ ከእርሱ በበለጠ ነገር ሲታመን ይታያችኋል?

የቃለ እምነት ስሕተትን የብልጽግና ወንጌል ደግሞ ይሉታል። በእውነቱ፥ የብልጽግና ወንጌል የስግብግብነት ወንጌል ወይም gospel of greed ተብሎ ትክክለኛ ስም በተፈጠረበት በምዕራቡ የተሰጠው ስሕተት ነው። እኔ፥ 'የሰብስቤነት ወንጀል' ብዬ ነው የምጠራው። እነሱ የብልጽግና ወንጌል ይሉታል እንጂ ይህም ከሁለቱም የጸዳ ደዌ ነው፤ ብልጽግናም የለበትም፤ ወንጌልም የለበትም። ልክ ያኛው ቃልም እምነትም እንደሌለበት። እርግጥ ነው፥ አንርሳ፥ የሚበለጽጉ አሉ፤ አካባቾቹ፥ ሰብሳቢዎቹ፥ ሰብስቤዎቹ ይበለጽጋሉ። አገራችን በቅርብ የተፈለፈሉትን ብንወስድ፥ ለቤታቸው ኪራይ 70 ሺህ በወር ይከፍላሉ፤ ለሚስቶቻቸው የ10 ሚሊየን ብር መኪና ልክ ከግሮሰሪ ማርማላታ እንደሚገዙ ይገዛሉ፤ ሁለት ዓመት ቀረጥ ባልተከፈለበትና ባልተፈተሸ ገንዘብ የ100 ሚሊየን ብር ቤት ይገዛሉ። እነዚህ የአገራችን ጉዶች ናቸው።

አሜሪካ ያሉት ቤት ሰልችቷቸው የመንሸራሸሪያ መርከብና የግል አውሮፕላን ይገዛሉ። ሕዝብ ሕዝብ እንዳንሸት ብለው ነው ይህንን የሚያደርጉት። ሕዝብ ሕዝብ እንዳይሸቱ! ኬነት ኮፕላንድ ከአንድ ብጤው ጋር ሲያወራ እንደዚያ ነበር ያለው፤ ከbunch of demons ጋር አብረን መጓዝ የለብንም። ከአንድ መንጋ ዲያብሎሶች ጋር አብረው እንዳይጓዙ፥ በግል አውሮፕላን ይበርራሉ። በለጸጓ! ምን ያድርጉ! ለነገሩ አጋንንቱን ፈርተው ሳይሆን እዚያ አውሮፕላን ውስጥ የጌታ ልጆች የሆኑ ቅዱሳን ስለማይታጡ፥ ያንን ስለሚፈሩ ነው። የብልጽግና ወንጌል ይሉታል። 'የብልጽግና ወንጌል' ወይም የብልጽግና ወንጀል ያበለጽጋል፤ ሰብስቤዎቹን።

'የጤንነት ወንጌል' ደግሞ ይሉታል። ቃለ እምነት፥ የብልጽግና ወንጌል፥ የጤንነት ወንጌል። መልከ ጥፉን በስም መደጋገፍ ያውቁበታል። ስንቱን መድኃኒት እያስጣሉ፥ እየገደሉ፥ ለሞት እየዳረጉ የጤና ወንጌል! ደግሞ እኮ፥ ራሳቸውም ይታመማሉ፤ እነዚህ መናፍስት ነን የሚሉትም ሳይቀሩ አንዳንዴ ይሰበራሉ፤ በጄሶ በፋሻ ታስረው ይታያሉ፤ ደፈር የሚሉት ናቸው የሚታዩት። እንጂ ብዙኃኑ ተደብቀው ነው የሚታከሙት። ሰብስበው የበለጸጉቱ ላለመታየት እውጭ እየሄዱ ይታከማሉ። መንፈስ እኮ ቢሆኑ ኖሮ መንፈስ የሚታመም ነገር የለውምና ይህ ችግራቸው ባልሆነም ነበር። ሲታመሙ የሚደበቁትና መታመማቸውን የሚክዱት ስለሚያፍሩ ነው።

ሰው ሰው ነውና በኃጢአት ከወደቀ በኋላ የተከሰቱት መዘዞች ሊያገኙት ይችላሉ። ከነዚህ መዘዞች ዋናውና ትልቁ ሞት ነው። ወደ ሞት የሚወስደው ጎዳናው ደግሞ ብዙ ነው። ማርጀትም ራሱ የውድቀት መዘዝ፥ የኃጢአት ጠንቅ ነው። ወረርሽኞችም፥ ሕመሞችም፥ አደጋዎችም ሊከሰቱ ይችላሉ። ማንም ሰው ከዚህ አያመልጥም፤ በተለይም ከሞት፤ እንደ ኤልያስ ወይም እንደ ሄኖክ ካልተነጠቀ በቀር። ለምን? ሰው ነዋ! የጤንነት ወንጌልም እንደ ብልጽግና ወንጌል ነው፤ ጤንነትም ወንጌልም የሌሉበት በሽታ ነው።

## 'ሰው መንፈስ ነው' በአገራችን ሲጀመር እና ዛሬ

ወደ ሰው መንፈሶቹ ስንመጣ፥ ይህንን ችግረኛ፥ ችግረኛ አይደለም በሽተኛ ትምህርት በአገራችን ከልጅ እስከ አዋቂ፥ በልጅነትም፥ በጅልነትም፥ በአውቆ አበድነትም የዘሩት ጥቂት አይደሉም።

> "ዱሮ ሰው መንፈስ አይደለም፤ ሰው መንፈስ ነፍስና ሥጋ ነው ብዬ አስተምሬ ነበር። ዱሮ እዚህ ኢትዮጵያ የነበርኩ ጊዜ ማለት ነው። ስለዚህ ባወቅሁ ጊዜ

> አሳቤን ቀይሬአለሁ፤ አሁን ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ ሥጋ ውስጥ ያድራል ብዬአለሁ።" ኃይሉ ዮሐንስ።

> "ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ በሥጋ ውስጥ ነው ሚኖረው።" ዶ/ር ቶሎሳ ጉዲና።

ዱሮ ኢትዮጵያ የነበረ ጊዜ ሰው መንፈስ፥ ነፍስ፥ ሥጋ ነው ያለው ኃይሉ ዮሐንስ ወደ አሜሪካ ከሄደ በኋላ ይህን ትምህርት ከየት አገኘው? ግልጽ ነው፤ ከአሜሪካ ነው ያገኘው። አሜሪካ ውስጥ ይህን የሚያስተምሩ ሰዎች ይኖሩ ይሆን? የተወለደውስ የት ሆነና!? ኃይሉ በአንድ ወቅት እንደ መንፈሳዊ አባቱ እንደሚያየው የተናገረለት ኬነት ኮፐላንድ የዚህ አስተማሪ ነው። ስለዚህ የዚህ የኃይሉ ዮሐንስ፥ 'ሰው መንፈስ ነው' ትምህርት ምንጭ ኮፐላንድ ነው ማለት ነው። ኬኔት ኮፐላንድ ደግሞ ትምህርቶቹን የኮረጀው ከኦራል ሮበርትስ እና ኬኔት ሄግን ነው።

እንደ Word of Faith ወይም የቃል እምነት ትምህርት አባት የሚቆጠረው Kenneth E. Hagin, Man on Three Dimensions በተባለው መጽሐፉ ገጽ 8 እንዲህ ብሏል፤

> Man is a spirit who possesses a soul and lives in a body. Man's spirit is that part of him that knows God. He is in the same class with God because God is a Spirit and God made man to fellowship with Him. God made man for His own pleasure. Man is not an animal. In order to fellowship with God, man must be in the same category with God. Therefore, just as God is Spirit, so is man spirit.[1]

የዚህ ጥቅስ የመጀመሪያ ዐረፍተ ነገር፤ Man is a spirit who possesses a soul and lives in a body. ይላል። ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ በሥጋ ውስጥ፡ ያድራል ወይም ይኖራል ማለት ነው። ይህ ቀመር የኛዎቹ የፈጠሩት አይደለም። የኮረጁት ነው። ሄግን ራሱ ትምህርቱን ያገኘው ከE. W. Kenyon ነው። ኬንየን ከሞተ ከ21 ዓመታት በኋላ በልጁ አማካይነት ተሰባስቦ በታተመው The Bible in the Light of Our Redemption በተባለ መጽሐፉ ገጽ፥ 17-18 እንዲህ ይላል፤

---

[1] Hagin, Kenneth E. *Man of Three Dimensions* Kenneth Hagin Ministries Inc. Tulsa, OK. 1973. P. 8.

> The spirit is the real man, created in the image of God . . . Your body is not you. Your mind is not you. You have a mind which you use. You possess a body which you use. Your mind and body are merely the instruments of your spirit, the real YOU.[2]

እንደ ኬንየን ትምህርት፥ ‘the real YOU’ ያለው እውነተኛው ሰው መንፈስ ነው። ሌሎቹ ነገሮች ሁሉ የዚህ መገልገያዎች ናቸው።

በአገራችን ይህንን የተለከፈ ትምህርት የሚያስተምሩ ሌሎችም አሉ። ከአዲሶቹም ከቆዩትም። ፓስተር ቄስ ዶክተር ቶሎሳ ጉዲና፥ በብስራት ብዟየን ጉባኤ፥ ‘ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው በሥጋ ውስጥ ይኖራል’ ሲሉ፥ የጉባኤው ጠቅላላው ፉጨትና ጭብጨባ እንዴት እንዳስተጋባ ያስገርማል። ‘ለምን ጭብጨባ አስተጋባ?’ ተብሎ ቢጠየቅ፥ ‘ይኸው! አንጋፋዎቹም ያምኑበታል! ውሪዎቹ ብቻ ሳንሆን፤ ይኸው! አባቶቹም ያምኑበታል፤ ፈልፈላዎቹ ብቻ ሳንሆን’ የሚል ያስመስለዋል። ይመስላል።

በእውነቱ፥ ለአንጋፋ ለአንጋፋማ እነ ኬኔት ኮፐላንድ ራሳቸውም እኮ አሉ፤ ኮፐላንድ 80ዎቹ አጋማሽ ዕድሜ ላይ የሚገኝ አዛውንት ነው፤ ሽማግሌ ነው፤ አንጋፋ ነው፤ እሱን ምስክር ማድረግ ይችላሉ እኮ ኃይሉ ዮሐንስ እንዳደረገው። እነ ሄግንንም እነ ኬንየንንም መጥራት ይችላሉ እኮ በሕይወት ባይኖሩም። እንዲህ ያስቦረቃቸው ከአገራችን ከቀድሞዎቹ አንድ ስላገኙ ነው።

አዲሱ ሐዋርያዊ ዳግም ሥሪት (አሐዳስ ወይም NAR) በሚባለውን እንቅስቃሴ ውስጥ የተተበተቡት እኮ ፓስተር ቄስ ዶክተር ቶሎሳንም ጨምሮ ጥቂት የማይባሉ አበሾችም ናቸው። አንዳንዶቹ ቀደምት እና ትልልቅ የሚባሉትቱ የአዳዲሶቹ ‘አባቶችና’ ወርሃዊ ተቆራጭ የሚሰጣቸው ተከፋዮች ናቸው። በሥርዓት ‘አባት’ ወይም አሠልጣኝ፥ mentor እየተባሉ አሥራት የሚከፈላቸው ተጧሪዎችም አሉ። ከፋዮቹ ደግሞ የውስጥ ነገራቸው ውስጥ እየገቡ እንዳያምሷቸው በጣም አያቀርቧቸውም፤ በገደብ ያርቋቸዋል፤ እነዚያም ክፍያዋ እስካልቀረች ድረስ አይጫኗቸውም። አንዳንዶቹ ደግሞ አሠልጣኝ ሳይሆኑ ለዕለት የሚሆን ዘይት ይዘው የሚዞሩ ቀቢዎች ናቸው። እነሱም ተከፋዮች ናቸው። ሌሎች ደግሞ በአደባባይ አይናገሩም፥ አይጽፉም፥

---

[2] Kenyon, *The Bible in the Light of Our Redemption* pp.17-18, emphasis original. Kenyon’s Gospel Publishing Society, 3rd printing, 1969 (posthumously edited and compiled by Ruth Kenyon Housworth) Lynnwood, WA.

አያሥለጥኑም፥ አይቀቡም እንጂ ያምኑታል። ብቻ እንደዚህ እንደ ፓስተር ቄስ ዶክተር ቶሎሳ በመድረክ፥ በአደባባይ፥ በድፍረት ራሱን የሚገልጥ አንድ ሲገኝ ያስቦርቃል፤ ያስፈነድቃል። እና እነ ብስራት እና ጉባኤው ቢፈነድቁ አያስገርምም።

በአገራችን፥ 'መንፈስ ነን' የሚሉ ሰዎች በኛ አቆጣጠር በ1970ዎቹ መጨረሻና 80ዎቹ መጀመሪያ ተነሥተው ነበር። ያኔ እኔ አዲስ ክርስቲያን ስለነበርኩ እንደዚያ የሚሉ አሉ ሲባል ነው የምሰማው። ኋላ እኛም ቤተ ክርስቲያን ብቅ አሉ። ታዲያ እነዚህ ሰዎች ምንም ዓይነት አካላዊ ችግር (እጦት፥ ሕመም፥ ሌላም፥) ሲገጥማቸውና ስሞታ ሲያቀርቡ ይቀለድባቸው ነበር። ሲታመሙ መንፈስ እንዴት ይታመማል? ይባሉ ነበር። ልብሳችን አያረጅም፤ እኛም አናረጅም፤ 120 ዓመት ነው የምኖረው ይላሉ። አንሞትም የሚሉም ነበሩ፤ እንዲያውም ሳልሞት እንደ ኤልያስ ነው የምነጠቀው ያለኝም ነበረ። እየቆዩ እያረጁ ብዙዎቹ ሞቱ እንጂ!

በዚያኑ ዘመን መናፍስት ስለሆኑ አንሞትም ከሚሉትና ሞትን ከሚክዱት መካከል አንዱ በአዋሳ የክብሩ ወንጌል የሚባል ቤተ ክርስቲያን መጋቢ የነበረ ሰው ነው። ይህ ሰው የገዛ ልጁ ሲሞትበት የሚከደው ሞት እቤቱ መግባቱ እንዳይታወቅ በድኑን እንደ ዕቃ በጆንያ ጠቅልሎ ሲያሸሽ ጥቁር ውኃ የሚባለው ከአዋሳ በሰሜን የሚገኘው ኬላ ላይ ተይዞ ነበር። በጊዜው ለክርስትና እፍረት የነበረ የናኘ ዜና ነበረ። እነዚህ ሰዎች ያኔ ብዙም በአገራችን ከማይታወቀው ቃለ እምነት ስሕተት ሰምተውና አንዷን ቀንጭበው ወስደው በራሳቸው እርሾ አቡክተውና አባዝተው ነበር ይህን 'አንሞትም' የሚሉትን ስሕተት የነዙት። በዚህ ትምህርት የተለከፉት ብዙዎቹ (ብዙዎቹ ሳይሆን በሙሉ ማለት ይቻላል) የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን የሚጠየፉና የሚያንቋሽሹ፥ ከቃሉ ትምህርት የጸዱ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቶ መማርን የሚንቁ፥ ራሳቸውም ገብተው ያልተማሩ ሰዎች ናቸው።

በአገራችን ይህ 'ሰው መንፈስ ነው፤ ሰው አምላክ ነው፤ እኔና አብ አንድ ነን' ትምህርት እንደገናና አሁን በሚታወቅበት መልኩ የተረጨበት ዋና እና አዲሱ ቱቦ የሆነው ኃይሉ ዮሐንስ ነው። "ዱሮ ሰው መንፈስ አይደለም፤ ሰው መንፈስ ነፍስና ሥጋ ነው ብዬ አስተምሬ ነበር። ዱሮ እዚህ ኢትዮጵያ የነበርኩ ጊዜ . . . አሁን ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ ሥጋ ውስጥ ያድራል ብዬአለሁ።" ማለቱን ቀደም ሲል አውስቼአለሁ።[3] ይህን ያለው፥ 'ተሳስቼ ነበር አሁን አረምኩ የምትለው ነገር አለህ ወይ?' ተብሎ በጋዜጠኛዋ ለተጠየቀው ሲመልስ ነው። ይገርማል! ትክክለኛው ትምህርት ስሕተት፥ የተሳሳተው ደግሞ ትክክል ሲሆን የመሳትና የማሳት ምስጢር ወለል ብሎ ይታያል።

---

[3] Exodus TV Show፡ https://www.youtube.com/watch?v=DaSXi8EKlKk

# አሐዳስ እና አምስቱ ቢሮዎች

ሰው መንፈስ ነው የሚለው የስሕተት ትምህርት የታቆረበትና የሚንቆረቆርበት ምንጭ አለው። ሳቾቹና አሳቾቹ ሐዋርያትና ነቢያት የሚባሉቱ በአዲሱ ሐዋርያዊ ዳግም ሥሪት (New Apostolic Reformation - NAR) ጎርፍ ውስጥ ያሉ ሰዎች ናቸው። 'አምስቱ ቢሮዎች' ብለው የሐዋርያትና ነቢያትን አገልግሎት የሚያደናንቁና የሚያራግቡት፥ የሚሉቱና የሚያስብሉቱም ናቸው። The Five-fold Ministryም ይባላል። እዚህ ላይ ይህን ነጥብ እናንሣ፤ ለምን አምስት ሆነ? የአምስቱ ቢሮዎች የንግድ ፈቃዱ ከኤፌ. 4፥11 የተወሰደችው ናት። ለምን ከሮሜ 12፥6-8 ተወስዶ ሰባቱ አልሆነም? ወይም እንደ 1ቆሮ. 12፥8-9 ለምን ዘጠኝ ወይም እንደ 1ቆሮ 12፥28 ለምን ስምንቱ ቢሮዎች አልሆኑም? አንድ ሰው አንድ ነገር ከጀመረ ያንን ማስተጋባት የተለመደው ዘዬ ነው። አንድ ሰው አምስቱ ቢሮዎች ብሎ ጀመረ ከዚያ ሌሎቹ ማስተጋባት ነው።

አምስቱ ቢሮዎች የሚለው ነገር የተጀመረው ከአዲሱ ጴንጤቆስጣዊነት (Neo Pentecostalism) ወዲህ ከመንግሥታሁን (Kingdom Now) እና የግዛት ስነ መለኮት (Dominion Theology) ጋር ተቆራኝቶ ነው። እነዚህ አምስቱ፥ በተለይም ከአምስቱ ሁለቱ ሐዋርያትና ነቢያት የዘመናዊቷ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ተደርገውም እስከ መቆጠር ደርሰዋል። አንድ መርሳት የሌለብን ነገር፥ የቀድሞው መሠረት እንዳልተፈረከሰና አሁንም በቦታው ያለ መሆኑን ነው። አዲስ መሠረት አይመሠረትም። በመሠረቱ ላይ እናንጻለን፥ እናጸናለን እንጂ አዲስ የሐዋርያትና የነቢያት መሠረት አንመሠርትም። መሠረቱ ቀድሞውኑ ተመሥርቶአል።

የዘመናችን ሐዋርያትና ነቢያት <u>የስሕተት መሠረቶች</u> ናቸው እንጂ የአዲስ ኪዳን መሠረቱ አይደሉም። በኤፌ. 2፥20 *በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤* የሚለው እነሱ መሠረቶቹ መሆናቸውን ሳይሆን እነሱም ራሳቸው የተመሠረቱበት ዓለት መኖሩን የሚያሳይ ነው። መሠረቱ ተመሥርቷል፤ *የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተሰጠኝ መጠን እንደ ብልሃተኛ የአናጺ አለቃ መሠረትን መሠረትሁ፥ ሌላውም በላዩ ያንጻል። እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንዲያንጽ ይጠንቀቅ። ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።* 1ቆሮ. 3፥10-11። መሠረቱ ኢየሱስ ነው አለቀ። አይደለም ኢየሱስ ሳይሆን ነቢያትና ሐዋርያት ናቸው እንደ ኤፌ. 2፥20 ከተባለም እሱም አልቋል፤ ነቢያቱ በወከሉት በብሉይ ኪዳንና ሐዋርያቱ

በወከሉት በአዲስ ኪዳን ላይ ተመሥርተናል። የዘመናችን ሐዋርያትና ነቢያት የስሕተት መሠረቶች ናቸው እንጂ የአዲሱ ኪዳን መሠረቶች አይደሉም።

## የ'ሰው መንፈስ ነው' ትልልቅ አደጋዎች

ቀደም ሲል፥ 'ሰው መንፈስ ነው' የሚለው ጥያቄ ሞኝ ጥያቄ እንደሚመስልና ግን የግድ አንዳንድ ሞኝ ጥያቄዎች መቅረባቸውና መልስ መሰጠቱም አስፈላጊ መሆኑ ግድ መሆኑን እና ጥያቄው እንዲነሣ አስገዳጅ የሆነው የተሳሳተው የቃለ እምነት የስሕተት ስነ ሰብእ (Word of Faith Anthropology) መሆኑን አየን። ጤናማው ትምህርት ሰው ሰው መሆኑና እግዚአብሔር በስድስተኛው ቀን የፈጠረው መንፈስን ሳይሆን ሰውን መሆኑን፥ አዳምና ሔዋን መናፍስት ሳይሆኑ ሰዎች መሆናቸውን፥ ሰው መንፈስ ወይም መንፈስ ሰው አለመሆኑን አየን። ሰው መንፈስ መሆኑን የሚያሳይ አንድም የብሉይ ኪዳን ክፍል አለመኖሩን እና መንፈስ በሰው ውስጥ የሚኖር የማንነቱ ክፍል መሆኑን የሚያሳዩ በቂ ጥቅሶችን አይተናል። የስሕተቶቹን ምንጭ ስንመረምርና ስንፈትሽ ስሕተቱ የተወለደው በአሜሪካ መሆኑን፥ የቃለ እምነት አስተማሪዎች የነዙት ትምህርት መሆኑን፥ ከኬንየን ወደ ሄግንና መሰሎቹ፥ ከነሄግንና መሰሎቹ ወደ ኮፐላንድና መሰሎቹ፥ ከኮፐላንድና መሰሎቹ ወደ የኛዎቹ ኃይሉ ዮሐንስና መሰሎቹ የመጣ ድውይ ትምህርት መሆኑን አይተናል።

ቀጥሎ ይህ፥ 'ሰው መንፈስ ነው' የሚለውን ስሕተት ሁለት ትልልቅ አደጋዎች እንመልከት፤

## አደጋ አንድ፤ መንፈስ ስለሆንን አንረክስም

የመጀመሪያው አደጋ፥ 'ሰው መንፈስ ከሆነ በሥጋው ከሚያደርገው ርኩስት መንፈሱ የታተመች ናትና አያገኛትም፤ አትረክስም።' የሚል ግንዛቤ ነው። ይህንን አንዳንዶቹ አያስተምሩትም። አንዳንዶቹ ደግሞ በገሃድ አያስተምሩትም፤ በተግባር ግን ይኖሩታል፤ ያደፋፍሩታልም። ሲያፋጥጧቸውም ፈጽሞ አያምኑትም። ገና ከመጀመሪያው ምዕት ዓመት ጀምሮ የነበረ ግኖስቲሲዝም የተባለ፥ ሥጋና ነፍስን ወይም ሥጋና መንፈስን (አካላዊና መንፈሳዊውን ማንነት ማለት ነው) ነጣጥሎ በማየትና በማሳየት የሠለጠነ ትምህርት ነበረ። አካላዊውን ክፉ፥ ረቂቁንና የማይታየውን በጎ የማድረግ፥ ሰውን በተመለከተም ሥጋን ርኩስ፥ ነፍስና መንፈስን በጎ የማድረግ ትምህርት ነው።

ግኖስቲኮች ለተለያዩ ነገሮች የየራሳቸው ትምህርቶች አሏቸው፤ ከተርታው፥ ከመደዴው ሰው የላቀ ልዩ እውቀትን የተቀዳጁ እንደሆኑም ያስተምራሉ።

ግኖስቲኮች ሰውን በተመለከተ ትምህርታቸው፥ መለኮታዊው ብልጭታ ወይም መንፈስ በዚህ ቁሳዊው፥ ሥጋዊው አካል ውስጥ ሆኖ፥ ልክ ግዞት ቤት ወይም መጎኒ ቤት ውስጥ እንዳለ ሆኖ ተጠምዶ፥ ታግቶ፥ ታስሮ ተቀምጧል፤ ከዚህ ክፉ ግዞት ወይም ወኅኒ ቤት ውስጥ ሊወጣም ይጥራል፤ የሚል ዓይነት ነው። እንደ ግኖስቲሲዝም ትምህርት ነፍስና መንፈስ መልካም፥ ሥጋ ርኩስ ናቸው። በዚህም ኃጢአትን የሥጋ ብቻ የማድረግ አባዜ አላቸው።

ከላይ እንዳልኩት የዘመናችን አዲሶቹ ግኖስቲኮች የኃጢአት ልቅነትን አንዳንዶቹ አያስተምሩም፤ አንዳንዶቹ በገሃድ አያስተምሩትም፤ ግን የሚያስተምሩቱ ሰዎች ወይም የሚያስተምሯቸው ሰዎች አመላለሳቸው ትምህርታቸውን ይገልጠዋል። ፩ኛው የዮሐንስ መልእክት የተጻፈው ለዚህ ኑፋቄ፥ ለሁለቱም ዘርፎች ስሕተቶች ምላሽ እንደሆነ ይታመናል። በ፩ኛ ዮሐንስ ውስጥ ዮሐንስ እነዚህን ሁለት ነገሮች፥ እውቀት ስለሚሉት ነገርና ኃጢአትን በተመለከተ አሳምሮ ነው የጻፈባቸው። እውቀት አለን እያሉ እንዳይኩራሩና ኃጢአትን ደግሞ እተተዳፈሩ እንዳያደርጉ፥ እንዳይለማመዱ አጥብቆ ያሳስባቸዋል። እነዚህን ሁለት ቃላት <u>እውቀት ወይም ማወቅ እና ኃጢአት</u> የሚሉትን ቃላት በዚህ መልእክት ውስጥ ብንፈትሽ በሰፊው የተነገረበት ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን።

ሰው መንፈስ ነው የሚሉ ሰዎች አደገኛ ትምህርት መንፈስ ስለሆንን በሥጋ ለሚደረግ ኃጢአት ፈቃድ የመስጠት ዝንባሌ ነው። ይህ ሥጋን ቀፎ ወይም ጊዜያዊ አድራሻ ብቻ አድርጎ ማስተማር አንዳንዶቹን የቃል-እምነት ተከታዮች ሰውነት ማደሪያ ብቻ ነው፤ ተሸካሚ ብቻ ነው፤ ድንኳን ብቻ ነው፤ ጊዜያዊ መጠለያ ብቻ ነው፤ የምንቆሸሽበት ቱታ ነው፤ በቱታው ሆነን ስንንደባለል ሥጋችን አይቆሸሽም ይላሉ። በሥጋ የምናደርገው ኃጢአት ሥጋችንን ያረክሰዋል፤ ነፍሳችንን አይበክላትም፥ በተለይም መንፈሳችንን አይነካትም፤ መንፈሳችን ለቤዛ ቀን የታተመች ናትና አትገኝም፤ አትደረስም፤ ወደሚል የድፍረት ኃጢአትም ይጋብዛቸዋል። ኃጢአትን ይዳፈራሉ፤ ያዳፍራሉ። ይህ የዚህ ጠማማ ትምህርት አንድ መዘዝ ነው። በአደባባይ ቢያስተምሩት በገሐድ ስለሚወገዙ በተግባር ነው ሌሎች ለቀቅ፥ ፈታ ዘና ያለ ሕይወታቸውን ምሳሌነት በማየት የሚከተሏቸው።

ይህ ግን ለቀቅ ማለት ሳይሆን ልቅ መሆን ነው። ፈታ ዘና ማለት ሳይሆን ስድ መሆን ነው። 2ጴጥ፤ 2፥18-19 *ከንቱና ከመጠን ይልቅ ታላቅ የሆነውን ቃል ይናገራሉና፥ በስሕተትም ከሚኖሩት አሁን የሚያመልጡትን በሥጋ ሴሰኛ ምኞት ያታልላሉ።*

*ራሳቸው የጥፋት ባሪያዎች ሆነው፦ አርነት ትወጣላችሁ እያሉ ተስፋ ይሰጡአቸዋል፤ ሰው ለተሸነፈበት ለእርሱ ተገዝቶ ባሪያ ነውና።* የሚለው የነዚህን ዓይነት ሐሰተኛ አስተማሪዎች ነው። ዓለምንና ሥጋን የማይሰናበቱ ብዙ ወጣቶች በቀላሉ የሚከተሏቸው በዚህ የወረደ ልቅ የአኗኗር ዘይቤያቸው እየተሳቡ ነው። እነዚህ ሰዎች ዓለምን ስለመካድ፥ ለሥጋ ፈቃድ ስላለመገዛት፥ ስለ ቅድስና፥ ራስን ስለመካድ፥ መስቀልን ስለመሸከም፥ ስለ ደቀ መዝሙርነት፥ ስለ ኃጢአት፥ ወዘተ፥ የማይሰብኩት ስለዚህ ነው።

እርግጥ ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስ ሥጋችንን ማደሪያና ቤተ መቅደስ ይለዋል፤ ድንኳንም ይለዋል፤ ያ ማለት እንደ ሜካኒክ ቱታ ነው ማለት ግን አይደለም። ሜካኒክ ቀኑን ሁሉ ሲሠራ ውሎ ቱታው ቆሸሾ የውስጥ ልብሱ ሳይቆሸሽ፥ ወይም አካሉ ሳይቆሸሽ ወደ ቤቱ ሊመለስ ይችላል። ኃጢአት ግን በሥጋ ይገለጣል እንጂ ምንጩ ሥጋ አይደለም። ከውስጥ ከልብ ነው የሚመነጨው። *ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው፥ ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ።* ፩ዮሐ. 3፥15። ቱታ አይጠላም፤ የሚጠላው ከቱታው በታች ያለው ማንነት ነው። ልብ የሚባለው ነገር ነው። ማቴ 5፥28 *እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።* ካለ ከማመንዘር በፊት የሆነ ነገር አለ። ማየትና መመኘት። ቱታ አይመኝም። የሚመኘው ከቱታው በታች ያለው ማንነት ነው። ስለዚህ ሥጋ የሜካኒክ ቱታ አይደለም።

ኃጢአት ከቱታ ወደ ሰውነት ሳይሆን እንዲያውም ከሰውነት፥ ከውስጥ፥ ከልብ ወደ ቱታው የሚመጣ ነገር ነው። ማር. 7፥20-23 *እርሱም አለ፦ ከሰው የሚወጣው ሰውን የሚያረክስ ያ ነው። ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ መጎምጀት፥ ክፋት፥ ተንኰል፥ መዳራት፥ ምቀኝነት፥ ስድብ፥ ትዕቢት፥ ስንፍና ናቸውና፤ ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል ሰውን ያረክሰዋል።* ይላል። እነዚህ ነገሮች ሁሉ ከውስጥ መንጭተው በተግባር በአካልና በሥጋ ይገለጣሉ። የቱታው መቆሸሽ ብቻ ሳይሆን ቱታውንም የሚያረክሰው ጉዳይ ነው ጉዳዩ። 'ከሰው ልብ የሚወጣ' ብሎ ይጀምርና፥ 'ሰውን ያረክሰዋል' ብሎ ይጨርሳል። ስለዚህ ኃጢአት የሚኖረው በምናችን ነው ሲባል ምንጩንም መድረሻውንም መንካት ተገቢ ነው።

በሕይወት በሥጋ እስከኖርን ድረስ ኃጢአት በሁለንተናችን ሊኖርና ሁለንተናችንን ሊበክል ይችላል። ቅድስናም እንዲሁ። ፩ቆሮ. 6፥19-20 ወይስ *ሥጋችሁ* ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ። ይላል። ደግሞም ፩ተሰ. 5፥23 የሰላምም አምላክ

ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ *መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ* ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ። ይላል። *ሥጋችን፥ መንፈሳችን፥* ነፍሳችን ነቀፋም ቅድስናም ሊኖርባቸው ይችላል።

መጽሐፍ ቅዱስ፥ በተለይ አዲስ ኪዳን፥ *ሥጋ* ሲል ከአጥንትና ጅማት፥ ከደምና ሌሎች ብልቶቻችን ያለፈ ነገርን መናገሩ ነው። ለምሳሌ፥ ገላ. 5፥17 *ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም።* ሲል ወይም ኤፌ. 2፥3 *በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን።* ሲል የሥጋ ብልቶችን ሳይሆን *ሥጋዊ* አስተሳሰብን መግለጡ ነው።

'ሰው መንፈስ ነው' የሚሉ አንዳንዶች *ሥጋችን* አይረከስም እና ኃጢአት ብናደርግም እውነተኛ ማንነታችንን (ማለትም፥ እንደ እነርሱ ትርጉም መንፈሳችንን) አይነካምና አንረክስም የኃጢአት የፈቃድ ወረቀት አድርገው ሊጠቀሙባት ይሞክራሉ። ነገር ግን ይህንን ለማድረግ ሲጋብዙና ሲጋበዙ፥ *ሥጋቸው* ኃጢአት እንዲያደርግ ምንጫቸው የረከሰ መሆናቸውን ከስር፥ ከውስጥ፥ ከምንጭ የሆነ መበላሸታቸውን ይመሰክራል።

ስለዚህ ኃጢአትም ቅድስናም በምናችን ውስጥ ይኖራል? ቢባል፥ መልሱ ሁለቱም የማያቋርጥ የመሰጠት ሂደቶች ናቸው። ለኃጢአት ከተሰጠን ኃጢአት በሁለንተናችን ሊሰለጥን ይችላል፤ መንፈስ ቅዱስም ሁለንተናችንን ሊገዛውና ሊቆጣጠረው ከሰጠነው ሁለንተናችን ይቀደሳል። ፈቃዱ በእጃችን ነው ያለው።

*ሥጋችን ድንኳን ነው? አዎን።ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ፥ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንጻ እንዳለን እናውቃለንና። በዚህ ውስጥ በእውነት እንቃትታለንና፥ ከሰማይም የሚሆነውን መኖሪያችንን እንድንለብስ እንናፍቃለንና፤ ለብሰን ራቁታችንን አንገኝም። በእውነትም የሚሞተው በሕይወት ይዋጥ ዘንድ ልንለብስ እንጂ ልንገፈፍ የማንወድ ስለ ሆነ፥ በድንኳኑ ያለን እኛ ከብዶን እንቃትታለን።* 2ቆሮ. 5፥1-4። ግን ይህ ድንኳንና መቅደስ የቅዱሱ ማደሪያ ነውና ብልቶቻችን ለዓመጻ የጦር ዕቃ ሆነው መጠቀሚያ መሆን የለባቸውም። በተቃራኒው ነው ቃሉ የሚያስተምረን፤ *ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፥ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፥ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ።* ሮሜ 6፥13።

*የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችሁ።* 1ቆሮ. 3፥16-17። እናንተ ያለው 'ቢያፈርስ' የተባለውን የሚፈርሰውን *ሥጋም* ጨምሮ ሁለመናችንን እንጂ መንፈሳችንን ብቻ አይደለም። በሌላ ቦታ ይህን ይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል፤ *ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።* 1ቆሮ. 6፥19-20። እዚህ *ሥጋችን* ነው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ የተባለው።

ስለዚህ *መንፈሳችን ታትማለች* አትቆሽሽም እያሉ ኃጢአትን በግልጥም በስውርም እንደ ጨው የሚያልሱ ሰዎች ወደ እርድ ቦታ ሊወስዱን ነው። ለሌላ አይደለም። ኃጢአት *ሥጋችንን*፥ ነፍሳችንን፥ *መንፈሳችንንም ሁለመናችንን* ነው የሚያረክሰው። ከዚያም ይመነጫል። ይህ 'ሰው *መንፈስ* ነው' ስለዚህ *በሥጋ* የሚደረግ ነገር *መንፈሳችንን*፥ ማለትም እኛነታችንን አያረክስም የሚለው አሳች ትምህርት አንደኛው አደጋ ነው።

## አደጋ ሁለት፤ እኛ አማልክት ነን

ሁለተኛው የ'ሰው *መንፈስ* ነው' ስሕተት ትልቅ አደጋ፥ ሰው አምላክ ነው ማሰኘቱ ነው። እንዴት ነው የሚያሰኘው? ቢባል፥ እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር *መንፈስ* ነው፤ ሰውም *መንፈስ* ነው። እግዚአብሔር *መንፈስ* ከሆነ፥ ሰውም *መንፈስ* ከሆነ፥ ሰው እግዚአብሔር ነው ማለት ነው። ይህ ነው አደጋው። እኛ ትንንሽ እግዜሮች ነን፥ ትንንሽ አምላኮች ነን፥ አማልክት ነን የሚሉት ለዚህ ነው። ኃይሉ ዮሐንስ፥ እያፌዘም ቢሆን፥ 'ትንንሽ አይደለም፤ ትልልቅ በሚለው ይስተካከልልኝ' ብሏል። ኃይሉ ዮሐንስ እና የዚህ አሳች እኩይ ትምህርት ተከታዮች ማወቅ ያለባቸው የቃሉ እውነት፥ እነሱም ሆኑ ማንም ሰው ትልልቅም፥ ትንንሽም አማልክትም እንዳይደሉ ነው። እነርሱ ሰዎች ብቻ ስለሆኑ አምላክነት ሲያምራቸው ይቅር። ጣዖት ሊሆኑ ይችሉ ይሆናል እንጂ አምላክነት አይታሰብም። አምላክ አንድ ብቻ ነው፤ የአምላክነት ቦታው ተይዟል። ለአምላክነት የተከፈተ ክፍት የሥራ ቦታ የለም።

እንግዲህ፥ ትንንሽም ይሁን ትልልቅ አማልክት ነን የሚሉት ከዚህ '*መንፈስ* ነን' ከሚለው ትምህርት ጋር የተያያዘ ነው። የቃለ እምነት ትምህርት የሚሉትም ከአምላክነት ጋር የተቆራኘ ነው። 'እግዚአብሔር በቃሉ ከፈጠረ እኛም በቃላችን

መፍጠር እንችላለን፤' የሚል ነው። እግዚአብሔር እምነቱን ካመነ፥ እኛም እምነታችንን ማመን እንችላለን። እግዚአብሔር ፈጣሪ፥ እኛም ፈጣሪ ነን፤ እኔና እግዚአብሔር አንድ ነን፤ እኛ የእግዚአብሔር class ነን፤ የእግዚአብሔር kind ነን፤ ይላሉ። እንጀራ አባቶቻቸው እንግሊዝኛ ተናጋሪ ስለሆኑ ነው kind እና class የሚሉት፥ የእግዚአብሔር ዓይነት ነን ማለታቸው ነው። ዓይነት! እግዚአብሔርን፥ 'ዓይነት' ሲሉት አፋቸው ተብተብ አይልም፤ አይፈሩም። እግዚአብሔር ዓይነት አይደለም። እርሱ ከብዙዎች መካከል አንዱ አይደለም። እርሱ ከብዙዎች ጋር የሚመሳሰል አይደለም። እርሱን የሚመስል ሌላ የለም። ከማንም ጋር አይመሳሰልም፤ አይተያይም። በአምሳሉ ከፈጠረን ከኛም ጋር አይተያይም።

'እኛ መንፈስ ነን' ካልን ግን ይህንን ብቻ ሳይሆን ሌላም ማለት እንችላለን፤ እኛ የእግዚአብሔር ዓይነት ነን ብቻ ሳይሆን ቀጥለን፥ እግዚአብሔር የኛ ዓይነት ነው ለማለትም ደፋሮች እንሆናለን። ስነ መለኮቱን እንገለብጠዋለን። ሰው እግዚአብሔር ነው ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ሰው ነው ወደ ማለትም እንገለብጠዋለን።

ሰው የእግዚአብሔር መልክ ነው ማለት መንፈስ ነው ማለት ነው? እናም፥ እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ ሰውም መንፈስ ነው፤ ስለዚህ፥ ሰው እግዚአብሔር ነው ማለት ነው? በዘፍ. 1፥26-27 *እግዚአብሔርም አለ፦ <u>ሰውን</u> በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዛ። እግዚአብሔርም <u>ሰውን</u> በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።* ካለ ሰው በእግዚአብሔር መልክ ተፈጠረ ስላለ በግልባጩ የእግዚአብሔር መለኪያና ትርጉም ሰውን በማድረግ እግዚአብሔር ሰውን ይመስላል፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ሰው ነው ልንል ነው? በሂሳብና በግመታ ሳይንስ Extrapolate ማድረግ ወይም Extrapolation የሚሉት ነገር አለ። ግራፍን ወይም ቁጥርን አስረዝሞ ቀጣዩን መልክ ማሳየት ማለት ነው። በዚህ ሰው መንፈስ ነው በሚለው የስሕተት ትምህርት ላይ ያንን ስናደርግ ወይም ብናደርግ የምናገኘው ይህ ነው። ሰው መንፈስ ነው ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ሰው ነው ወደሚል ድምዳሜ ያደርሰናል።

ጠማማው የቃል-እምነት ትምህርት፥ 'እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ ሰው የእግዚአብሔር መልክ ከኖረውና እግዚአብሔር መንፈስ ከሆነ ሰውም መንፈስ ነው ማለት ነው።' የሚል ነው። የዚህ የቃል-እምነት ትምህርት አካሄድ ግብ ያ ነው። ግን ከዘፍ. 1 ወደ 2 ስናልፍ የሰውን አፈጣጠር እናያለን። ዘፍ. 2፥7 *እግዚአብሔር አምላክም <u>ሰውን</u> ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት <u>ሰውም</u> ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።* ይላል። ማንን ነው ያበጀው? <u>ሰውን።</u> ከምን? ከምድር አፈር። የተበጀው ምንድር ነው? <u>ሰው።</u> የሕይወት እስትንፋስ እፍ ሲባልበት

ምን ሆነ? ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ። ሳይባልበትስ? <u>የተበጀ ሰው ነበር እንጂ መንፈስ አልነበረም።</u> ገና ሕያው ያልሆነ የተበጀ ሰው። በመንፈሱ ውስጥ አይደለም የሕይወት እስትንፋስ እፍ የተባለበት። ግልጽ ነው መወሳሰብ የለበትም! ከምድር አፈር የተበጀው ሰው ነው፤ መንፈስ አይደለም። መንፈስን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር አላለም። *በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት <u>ሰውም</u> ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።* እንጂ፥ *<u>መንፈስም</u> ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።* አልተባለም።

ሰው ሕያው የሆነው የሕይወት እስትንፋስ እፍ ሲባልበት ነው፤ መንፈስ እና ነፍስ በሰው ውስጥ የሚኖሩ ነገሮች ናቸው። *ነገር ግን <u>በሰው ውስጥ መንፈስ አለ፥</u> ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ማስተዋልን ይሰጣል።* ኢዮ. 32፥8። ሰው ሁለንተናው፥ ሥጋው፥ ነፍሱ እና መንፈሱ ነው እንጂ ሰው መንፈስ ብቻ አይደለም። 1ተሰ. 5፥23 *የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ።* ይላል።

እነዚህ፥ 'Kind ነን' የሚሉት ሰዎች እንጀራ አባቶቻቸው እንግሊዝኛ ተናጋሪ ስለሆኑ ነው ብያለሁ። Kind ነንን ብቻ ሳይሆን ጠቅላላውን ኮሮጆ ወይም ፓኬጅ የሸመቱትም ከእነሱ ነው። ይህ ሰው መንፈስ ነው የሚባለው ትምህርት አገራችን ውስጥ ዋልድባ ገዳም ወይም አዋሳ አዲስ ከተፈለፈሉት ፍልፍሎች ቤት የተፈጠረ ትምህርት አይደለም። እነዚህ አዳዲስ ፍልፍሎች ብቻ ሳይሆኑ የፍልፈል ሥራ ሠራተኞችም ናቸው። በሥራቸው፥ በተግባራቸው ፍልፈሎች ናቸው። ፍልፈልን ገጠር ያላደጉ አያውቁም። ፍልፈል ማለት እንደ አይጥ ወይም አይጠ መጎጥ ያለ ሆኖ መሬት ውስጥ ጉድጓድ ቆፍሮ ውስጥ ለውስጥ እየሄደ ስራስር የሚበላ ነው። እኔ ባደግኩበት አካባቢ ገበሬዎችን በጣም የሚረብሽ ፍጡር ነው። ድንች፥ ስኳር ድንች፥ ቦዬ የሚሉት ልሌላ ተክል ስራስር፥ በተለይ የእንሰት ስርን እንክት አድርጎ ይበላል። የእንሰት ተክል ውስጥ መግባቱ የሚታወቀው እንሰቱ በቁሙ መድረቅ ሲጀምር ነው። አንዳንዴ በቁሙ ይወድቃል፤ ወይም ሄደው ገፉ ሲያደርጉት እንሰቱ በቁሙ ይወድቃል። ሐሰተኛ አስተማሪዎችም እንደ ፍልፈል ናቸው ስል ስራችንን በልተው ከላይ ያደርቁናል ማለቴ ነው። ሲገፉን እንወድቃለን።

የነዚህ እኛ መናፍስት ነን የሚሉ ሰዎች ትምህርት አገራችን የተወለደ ትምህርት አይደለም ብያለሁ። አሜሪካ ውስጥ ተፈጭቶ ተቦክቶ የተጋገረ መርዝ ነው። አንዳንዶቹ ሲኮርጁ ምኑንም ሳያስቀሩ ነው የሚኮርጁት፤ እንደ ሰነፍ ተማሪ። አንድ ሰነፍ ተማሪ ኮርጆ ፈተናውን ሠራና ሰጠ አሉ። ወረቀት በሚመለስበት ቀን አስተማሪዎቹ ለተማሪዎቹ ሁሉ ሰጠ። ይህ ልጅ ደግሞ ሳያፍር፥ 'ቲቸር! የኔ የፈተና ወረቀቴ አልተሰጠኝም።' ብሎ ሲጠይቅ፥ 'ይሄ ያንተ ነው? አለው ውጤቱን ብቻ

አሳይቶ፤ 'አዎ፤ ሄይ!' ሲል፥ 'ይሄ ስም ያንተ ነው?' ሲለው ኩም! ለካስ፥ name ከሚለው ቀጥሎም የራሱን ስም በመጻፍ ፈንታ የሚኮርጀውን ልጅ ስም ጽፎ ነበር። የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ሲኮርጁ ልክ እንደዚያ ናቸው። ምንም ሳያስቀሩ ነው የሚኮርጁት።

በ2017 አንድ መጽሐፍ ገዝቼ ነበር። መጽሐፍ ስገዛ እንደማደርገው ቆሜ በገጾቹ እሮጥበታለሁ። ብሔራዊ ቴያትር አጠገብ የተለጠፉት ሱቆችጋ ሄጄ በኢትዮጵያኝነት ጉዳይ ላይ ስለጻፍኩና ስለምጽፍም አንዱን እንድገዛ የተነገረኝን መጽሐፍ ሳልገዛው ማንበብ ጀመርኩ። *የኦሮሞ እና የአማራ እውነተኛ የዘር ምንጭ* የሚል በፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ የተጻፈ መጽሐፍ ነው። ገና ሳነብበው ተረት ተረት ነበር የሸተተኝ። ቢሆንም ገዛሁት። መጽሐፉ ሦስት ክፍሎች ሲኖሩት የመጀመሪያው ትንሽ ሆኖ ክፍል ሁለትና ሦስት ሰፋፊ ናቸው። ክፍል ሁለትን እያነበብኩ የግርጌ ወይም ዋቢ ማጣቀሻዎችን ሄጄ ሳይ አማን በላይ የሚል አንድ ስም ከምንም በላይ ተደጋግሞ ተጠቅሶአል። [4] አማን በላይ ገጽ . . . አማን በላይ ገጽ . . .።

የመጽሐፉ ክፍል አንድ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ የኦሮሞን አበርክቶት የሚናገር ሆኖ ጥቂት ማጣቀሻ ብቻ ያለው አጭር ክፍል ነው። በክፍል ሁለት ከ63 የግርጌ ማስታወሻዎች አማን በላይ 31ዱን ይዞአል። ግማሽ በግማሽ ማለት ነው። በክፍል ሦስት ደግሞ ከ56ቱ ማጣቀሻዎች 31ዱን ይዞአል። 55% ማለት ነው። የአማን በላይን መጽሐፎችም አይቼ ነበር፤ ግን፥ 'ይህስ የሚነበብ አይደለም፤ ይህ ደግሞ በእርግጥም ምንጭ የሌለው ተረት ነው፤ ይህ ጥሬ ኢትዮጵያኛ ሥራ ነው' እያልኩ ተውኳቸውና ሳልገዛ ቀረሁ። በኋላ ገዛሁት። ይህን ከላይ የጠቀስኩትን መጽሐፍ ለመጥቀስ ብቻ ነው ያነሣሁት እንጂ ላሔስ አይደለም፤ ትዝብቴ ግን፥ ሒስም ከሆነ ሒሴ፥ የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር የሆነ ሰው፥ ከአንድ መጽሐፍ ብቻ 50% ወይም 62 ጊዜ ከጠቀሰ፥ ያውም ምንጩ ከመደፍረሱ የተነሣ የማይታይ መጽሐፍ ከጠቀሰ ያስፈራል። ተረቶችን ዋቢ አድርጎ እንደ ምሑራዊ ጽሑፍ ተነባቢ ካደረገ አዝማሚያችን ያስደነግጣል። የምንቀዳባቸው ምንጮች ከተበላሹ ፈሳሹ ጅረት በምንም ሂሳብ ጤና ሊሆን አይችልም። ይህ የአማራ ኦሮሞ ጉዳይ ሌላ ዘውግ ነው፤ ከብዙዎቻችን ክልል ውጪም ነውና ይህንን ለማንሣት ወዳነሣሳኝ የእኛ ወደሆነው ልምጣ።

ስሕተቶችን ለመንቀስ ወይም ስሕተትነታቸውን ለማሳየት ወደ ምንጩና ወደ አመንጪዎቹ መሄድ አማራጭ የሌለው የሕያሴ ሥራ ነው። ልክ አንድ ተረት የተረት

---

[4] ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ፥ *የኦሮሞ እና የአማራ እውነተኛ የዘር ምንጭ*፥ Nebadan Publications 2008 ዓ. ም. አዲስ አበባ፤ ገጽ 140-44 እና 268-71።

አባት ሲናገረው ተረት ይመስልና፥ አንድ ምሑር በቆነጀ፥ በሰለጠነ ቋንቋ ሲናገረው እውነት ሊመስል ይችላል። በመንፈሳዊው ረገድም ተመሳሳይ ነው። አንድ ጠንቋይ የተናገረው ነገር የጥንቆላ ነገር መምሰል ብቻ ሳይሆን መሆኑን ለማወቅም አይከብደንም። ያንኑ ነገር ግን አንድ ሰባኪ ከመጽሐፍ ቅዱስ በወጡ ቃላት ሽቃቅጦ፥ ቀያይጦ፥ ቀባብቶ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ አስመስሎ ሲያቀርብ ወይም ቢያቀርብ በቀላሉ ልንታለልና ልንስት እንችላለን።

አንዳንድ የስሕተት ትምህርቶችን ስንፈትሽ፥ ስናሔስ ቅርንጫፎቹን ከመመልመል ተሻግረን ወደ ግንዱ መሄድና መግለጥ አለብን። ቅርንጫፎቹን መመርመር ፍሬያቸውን ያሳየናልና ያም ጥሩ ነው፤ መደረግ አበት። ግን፥ ወደ ግንዱ መሄድ የአንዱን ቅርንጫፍ ብቻ ሳይሆን የቅርንጫፎቹን ሁሉ ባሕርይ እና ምንነታቸውን ያሳየናል። ስሕተቶችን የመንቀፍና የመንቀስ ሥራ ቀላል አይደለም። ያታክታል፤ ያሳምማል፤ ያስከስሳል፤ ያስኮንናል ግን መደረግ አለበት። ስሕተቶችን የመንቀስ ሥራ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ እንዳልኩት ልክ ዐዛባ እንደ መዛቅ ዓይነት ነው። ያቆሽሻል፥ ያከረፋል። ግና ምን ያረጉታል? መደረግ አለበት፤ መዝዛቅ አለበት።

ሰው መንፈስ ነው? ወይስ ሰው ነው? የሚለውን ይህንን አሳብ ስናይ፥ በእነዚህ የስሕተት አስተማሪዎች ዘንድ እንደ አዝማች የሚደጋገም አንድ ዐረፍተ ነገር አለ፤ ያም፥ 'ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ በሥጋ ውስጥ ያድራል' የሚለው ነው። የኮረጁት ነው። "You Are a Spirit Being; You Possess a Soul & Just Live in a Body." (John Hamel) የሚለው ነው። Hamel ከብዙዎቹ ቃል-እምነተኞች አንዱ ነው። በቃል-እምነት አስተማሪዎች ዘንድ ይህ፥ 'ሰው መንፈስ ነው፥ ነፍስ አለው፥ በሥጋ ውስጥ ያድራል' የሚለው አባባል፥ ሙሉ ተቀባይነት ያገኘ፥ የተቀዳጀ የስሕተት ትምህርት ነው። ተቀባይነት አገኘ ማለት ግን ስሕተትነቱን አይቀይረውም። ስሕተቱ ሰውን ሰው ሳይሆን መንፈስ ማድረጉ ነው። ሰው መንፈስ ከሆነ፥ ሰው = መንፈስ ወይም ሰው እኩል ነው ከመንፈስ ጋር ማለት እንችላለን ማለት ነው። ሰው የሚለውን ቃልም መንፈስ በሚለው ያለ ምንም ችግር መለወጥና መተካት እንችላለን ማለት ነው። ምክንያቱም፥ a = b ካልን፥ b = a ማለት እንችላለን። የግድ a bን ባይሆንም፥ a ከb ጋር እኩል ወይም እኩያ ነው ማለት ይቻላል።

እነዚህ አሳች ሰዎች፥ 'እኛ አማልክት ነን ወይም ትንንሽ አማልክት ነን' የሚሉት በመዝ. 82፥6 እኔ ግን፦ አማልክት ናችሁ፥ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ፤ ተብሎ ስለተጻፈ ሳይሆን፥ ጥቅሱን እንመለከተዋለን፤ እውነተኛ ምንጩ መንፈስነታቸው፥ ማለትም መንፈስ ነን ማለታቸው ነው። እግዚአብሔር መንፈስ፥ እኛ መንፈስ፤ ስለዚህ እኛ እግዚአብሔር።

ትንንሽ አማልክት ነን የሚለውን አጠራር እኛ አይደለንም የሰጠናቸው ራሳቸው ናቸው ያሉት። Little gods with little 'G' የሚሉት ራሳቸው ናቸው። ይህ የኛ ፈጠራ አይደለም። እንደዚህ ያሉ ብዙ ናቸው፤ አንዱ ክሬፍሎ ዶላር የተባለው ያለውን መስማት በቂ ነው፤ ይህንን ያለው በጉባኤው ውስጥ ነው። ከቪድዮው በቀጥታ የወሰድኩትን ከነትርጉሙ ልጻፈው፤

> Creflo Dollar "everything reproduces after its own kind"...
> Dollar: "If horses get together, they produce what?"
> Congregation: "Horses!"
> Dollar: "If dogs get together, they produce what?"
> Congregation: "Dogs!"
> Dollar: "If cats get together, they produce what?"
> Congregation: "Cats!"
> Dollar: "So if the Godhead says 'Let us make man in our image', and everything produces after its own kind, then they produce what?"
> Congregation: "gods!"
> Dollar: "gods. Little "g" gods. You're not human. Only human part of you is this flesh you're wearing."[5]
>
> ትርጉም፤ እንግዲህ ሁሉም እንደየወገኑ ነው የሚወልደው፤ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር (ሲያመርት) እናያለን። ታዲያ እግዚአብሔር ሰው ከፈጠረና ሌሎቹ ነገሮች እንደየወገናቸው ከወለዱ፥ ፈረሶች ሲገናኙ ምን ይወልዳሉ? ፈረሶች! ውሾች ሲገናኙ ምን ይወልዳሉ? ውሾች! ድመቶች ሲገናኙ ምን ይወልዳሉ? ድመቶች! እግዚአብሔር ደግሞ አንድ ላይ ሆኖ ሰውን እንፍጠር ሲሉ ምን እየፈጠሩ ነው? እግዜሮች! እግዜሮች እየፈጠሩ ነው። እናንተ እግዜሮች ናችሁ ትንንሽ እግዜሮች (Little 'G')። እናንተ እግዜሮች ናችሁ ምክንያቱም እናንተ የመጣችሁት ከእግዚአብሔር ነው። እናንተ ሰዎች አይደላችሁም፤ ከእናንተ ሰው የሚባለው ነገር ይህ የምትኖሩበት አካላችሁ ብቻ ነው። ብሏል።

Little 'G' የሚሉትን ሌሎቹም ይሉታል። እና ይህ የኛ ቃል አይደለም፤ የራሳቸው ነው። ትንንሽ አምላኮች ነን ያስባልናቸው እኛ አይደለንም፤ እነሱ ናቸው Little 'G' በሉን ያሉት። ኃይሉ ዮሐንስ ትልልቅ በሉኝ ብሎ መልሶ እየቀለድኩ ነው እንደዚያ ያልኩት ብሏል። ይቀልድም አይቀልድም፥ Little 'G'ም እንበለው፥ ንዕሽተ አምላኽ በለው፤ ሺማ ማጋኖ በለው፥ ወይም ጢቆ ዋቆ እንበለው፤ ልዩነት የለውም፤ ሰው ሰው ነው፤ ኃይሉ ዮሐንስም፥ ኃይለኛው ዮሐንስም፥ ኮሳሳው ዮሐንስም፥ ሰው ነው፤ ሰው አምላክ አይደለም። ሰው አምላክ ነው ተብሎ አልተጻፈም። አራት ነጥብ።

---

[5] "Suffer the Children" *(DVD)* a Trevor Glass film, 2006; Accessed from Spiritwatch Ministries on YouTube: https://www.youtube.com/watch?v=2X5dpfzXUus)

ኃይሉ ዮሐንስም ይህንኑ የክሬፍሎን አባባል ብሎታል፤ 'አምላክ ምንድነው ሚወልደው? አማልክትን ነው።' ብሏል በአንድ ቃለ ምልልስ።[6] መልሶ ስለመምሰልም ይናገራል። በቃላት ቁማር መጫወት አንዳንዴ ሊያበላ ይችል ይሆናል፤ ግን መበላትም አለ። መምሰልና መሆን የተለያዩ ናቸው። እኔ Little 'G' god ነኝ ማለትና እኔ ፈጣሪዬ በአምሳሉ የፈጠረኝ አምላክ ያልሆንኩ ሰው ነኝ ማለት የተለያዩ ናቸው። Little 'G' godም የትኛው 'G' godም ማናችንም አይደለንም። ሰው ነህ፤ ሰው ነሽ፤ ሰው ነን። እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ።

መምሰልን ከወሰድን፥ መምሰልማ በመልኩ እንደ ምሳሌው ነው እኮ የተፈጠርነው። ሰውየው ነው ግን በመልኩ እና በምሳሌው የተፈጠረው፤ አምላክ ወይም መንፈስ ሳይሆን። ዘፍ. 1፥26። ኃይሉ ዮሐንስ ከላይ ባልኩት ቃለ ምልልሱ መምሰል መግዛት መሆኑን ተናግሯል። መምሰል የሰማይ፥ የምድርና የባሕር ፍጥረትን መግዛት ነው ብሏል። ግዛ የተባለው እኮ መንፈስ አይደለም፤ ወይም አምላክ አይደለም፤ ሰው ነው። ሰው እኮ ሲገዛ ኖሯል። ያውም ከመንፈስ ያልተወለደውም ጭምር! ክርስቲያን ሆነ አልሆነ ፍጥረት ለሰው ተገዝቷል፣ ተገርቷል፤ *የአራዊትና የወፎች የተንቀሳቃሾችና በባሕር ያለ የፍጥረት ወገን ሁሉ በሰው ይገራል፥ ደግሞ ተገርቶአል፤* ያዕ. 1፥7። ፍጥረት ሁሉ ለሰው ተገዝቷል፤ ከውድቀት በኋላ እንደ ልቡ ባይገዛለትም፥ ሲገዛዛ ኖሯል፤ ሰውም ሲገዛ ኖሯል! እንዲያው መቀወጥ ሲያምረን እንጂ። ስንፈጠርም ሰው እንጂ አምላክ አይደለንም። አባታችን አዳምም ሰው እንጂ አምላክ አልነበረም! ሊገዛ መፈጠሩማ በግልጽ ተጽፏል፤ ያልተጻፈውና እነዚህ አሳቾች የፈጠሩት መንፈስ መሆኑና አምላክ መሆኑ ነው። እሱ ነው ያልተጻፈው።

እግዚአብሔር ቃላት አጥረውት አይደለም ሰውን ሰው ያለው። ሰውን ሰው ያለው ሰው ሰው ስለሆነ ነው። የቃል-እምነት አስተማሪዎች ሰው መንፈስ መሆኑን፥ ነፍስ ያለው እና በሥጋ ውስጥ የሚያድር መሆኑን ሲያወሳስቡ ከዚያ ለሚቀጥል ሰይጣናዊ ትምህርት ሰውን ሲያዘጋጁ ነው። ያም፥ 'ሰው በእግዚአብሔር መደብ (እነርሱ class ይሉታል) የተፈጠረ ነው' የሚል ነው። ኃይሉ ዮሐንስም፥ 'እኔና አብ አንድ ነን!' ያለው እና ሰው በሥጋ ውስጥ የሚያድር ነፍስ ያለው መንፈስ መሆኑን የተናገረው ከዚህ

---

[6] *ለተነሱብን ጥያቄዎች ምላሽ፤ በሚል ርእስ ባዕድ-ቅይጡ ወንጌል ለተሰኘው ዘጋቢ ቪድዮ ምላሽ ሲሰጥ ባደረገው ቃለ ምልልስ ላይ። ምንጭ፤ https://www.youtube.com/watch?v=uW3bi-uIuus እና https://www.youtube.com/watch?v=wVsAweQt6xY ይገኛል።*

እኩይ ትምህርት ተንደርድሮ ነው። እነ ቤኒ ሂን፥ ኮፕላንድ፥ ሄግን፥ ሮበርትስ፥ ሌሎችም ቀድመውት ብለውታልና ይህ እርሱ ያስተጋባው እርሱ የፈጠረው አዲስ ትምህርት አይደለም። 'የነሱን ትምህርት አላስተምርም፤ የነሱን ወስጄ የራሴን ነው የማስተምረው' ብሏል። መስሎት፤ ወይም ሊያታልል። ሱቁን ነው የቀየረው እንጂ ሸቀጡን አልቀየረም። ከነዚያ፥ Man is a spirit being, has a soul, lives in a bodyን ሰማ፤ በእንግሊዝኛ። ከዚያ፥ ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ በሥጋ ውስጥ ያድራል አለ፤ በአማርኛ። ይህ ነው የራሴ የሚለው። እኔና አብ አንድ ነን ማለትን እየጨመረበት።

አንዴ በኤልሻዳይ ቲቪ ከመጋቢ ተሾመ ዳምጠው ጋር ቀርቦ፥ 'እኔና አብ አንድ ነን አላልኩም፤ ማለቱ ትዝ አይለኝም።' ብሎ ብዙ ሳይቆይ እኔና አብ አንድ ነን አለ። ባዕድ-ቅይጡ ወንጌል ለተሰኘው ዘጋቢ ቪድዮ ምላሽ ሲሰጥም ያንኑ ደገመው። መድገም ብቻ አይደለም እንዲያውም የክርስቲያን አገልጋይ ትክክለኛነት መለኪያ አደረገው። ከአንድ አገልጋይ ነኝ ከሚል ሰው ጋር ቁጭ ብሎ ለማውራት ሲጀመር መስፈርት ያደረገው ምን እንደሆነ ሲናገር፥ ያ ሰው፥ 'ስለ ሰው ምን እንደሚያስብ እጠይቀዋለሁ፤ እኔና አብ አንድ ነን የማይል ከሆነ መንፈሳዊ ነገር ስላልገባው መንፈሳዊ ነገር ከዚያ ሰው ጋር አላወራም፤ ስለ ፖለቲካ ስለ ሌላ ነገር ብቻ አውርቼ እለያያለሁ፤' አለ።[7]

ይህ ሰው፥ 'እኔና አብ አንድ ነን!' ካለ፥ ቀጥሎ፥ 'እኔን ያየ አብን አየ' ማለት ምን ይከለክለዋል? ምንም። ሰውን ወደ እግዚአብሔር መደብ ለማስጠጋት ሰውን ሰው ነው ከማለት ይልቅ መንፈስ ነው ማለት የሚቀለው ለዚህ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር መንፈስ ነውና ሰውም መንፈስ ነው ከተባለ በኋላ፥ 'ሰው እግዚአብሔር ነው' ወይም፥ 'የእግዚአብሔር ዓይነት ነው' ማለት ከባድና ሩቅ አይሆንም። እኔና አብ አንድ ነን ማለት እኮ፥ እኔን ያየ አብን አይቷል ማለት እኮ ሌላ ምንም አይደለም፤ እኔ ክርስቶስ ነኝ ማለት ነው። 'እኔ ክርስቶስ ነኝ' እያሉ በስሙ የሚመጡ መኖራቸው ደግሞ ቀድሞ ተነግሮናል።

'እኔና አብ አንድ ነን' ያለ ከኢየሱስ በቀር ሌላ የለም። ይህን ያለው ደግሞ የሆነው እርሱ ነው። ይህ እውነት ከጳውሎስና ከጴጥሮስና ከዮሐንስ ይህ ተሰወረና፥ ለ2ሺህ ዓመታት ተደብቆ ቆየና እሱና አብ አንድ መሆናቸው አሁን ለኃይሉ ዮሐንስ ተገለጠ? እንደዚህ ያለውን 'እኔና አብ አንድ ነን' እግዚአብሔርን መስደብ በእግሩ ስር ተቀምጦ

[7] እላይ የተጠቀሰው የቃለ ምልልስ ቪድዮ ውስጥ።

የተማረበት አሳዳጊው ኮፐላንድም አልተናገረም። እንዲህ ያለውን፥ ስድብ አያቱ ሄግንም 'I and the Father are one!' ብሎ አልተናገረም።

በዮሐ. 10፥30 ጌታ፥ 'እኔና አብ አንድ ነን' ባለ ጊዜ ምን ነበር የሆነው? በቁ. 31 እንደተጻፈው *አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ።* ነው የተባለው። ለምን? እኔና አብ አንድ ነን ማለት እኔ ያህዌ ነኝ ማለቱ ነው። ምን ማለቱ መሆኑን አሳምረው አውቀውታል። ገብቷቸዋል። እኔና አብ  አንድ ነን ሲል፥ በነሱ ግምት ተሳድቧል። እርሱ ግን አምላክ ነው፤ በሥጋ የመጣ እግዚአብሔር ነው። ሥጋ የሆነ ቃል ነው። በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረ ነው። በመጀመሪያ እግዚአብሔር የነበረ ነው። ዓለማትንና እነዚህን ተሳድበሃል የሚሉትንም የፈጠረው እርሱ ነው። እኔና አብ  አንድ ነን ሲል ለነሱ መሳደብ ነው እርሱ ግን ይህንን ያለውን ነው።

ኢየሱስ ታላቅ ወንድምህ አይደለም፤ እርሱ ጌታህ ነው። እሱ ወንድሞቼ ያለው እንዳላፈረብህ ያሳያል እንጂ አንተ እንድትመጻደቅ አያደርግህም። ወንድሞቼ ያለው በሥጋና ደም ተካፍሎ እኛን የእግዚአብሔር ልጆች ማድረጉንና በትንሣኤም ብኵርናውን ያሳያል እንጂ ከሐዋርያቱና ከደቀ መዛሙርቱ አንዳቸውም፥ 'ታላቅ ወንድማችን' እያሉ አልገለጡትም። ይህ ግልጽ እውነት ነው። ማናቸውም ይህንን አላሉም። በሥጋ ግማሽ ወንድሞቹ የነበሩት ያዕቆብና ይሁዳ እንኳ፥ 'የጌታ ታናሽ ወንድም' እያሉ ሳይሆን፥ 'የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ' እያሉ ነው የጻፉት፤ ሁለቱንም መልእክቶች ተመልከቱ። ያዕቆብ በመግቢያ ቃሉ፥ *የእግዚአብሔርና <u>የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ያዕቆብ</u> ለተበተኑ ለአሥራ ሁለቱ ወገኖች፤ ሰላም ለእናንተ ይሁን።* አለ፤ ያዕ. 1፥1። ይሁዳም፥ *<u>የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ የያዕቆብም ወንድም የሆነ ይሁዳ፥</u> በእግዚአብሔር አብ ተወደው ለኢየሱስ ክርስቶስም ተጠብቀው ለተጠሩ፤* አለ፤ ይሁ. 1። እነሱ ባሪያ ከሆኑ እርሱ ጌታ ነው።

ጌታ ማለት ልጅነትህን አይፍቀውም። 'ታላቅ ወንድሜ' ማለት ግን ባርነትን እንዲፍቀው ሆን ብለው የቀመሯት ቀመር ናት! በእውነቱ፥ የቃለ እምነት አሳኞች፥ 'ባሪያ' የምትለዋን ቃል አይወዷትም። ታላቅ ወንድምህ ከሆነ አቻህ ነው፤ አቻው ነህ፤ ሸርክህ ነው፤ አብረኸው ማኪያቶ ትጠጣለህ፤ አዛዥህ አይደለም፤ ታላቅህ ቢሆንም ባትታዘዘውም ምንም አይደለም፤ ወይም መርጠህ ከታዘዝከው ልታስረዳውና ልታሳምነው ትችላለህ። ታላቅ ወንድምህ፤ ግን ንቀት ነው! ስድብ!

ጌታ፥ 'እኔና አብ  አንድ ነን' ሲል፥ በአይሁድ ግምት ተሳድቧል። እርሱ ግን አምላክ ስለሆነ፥ እግዚአብሔር ስለሆነ፥ በሥጋ የመጣ ቃል ስለሆነ አልተሳደበም። እርሱና አብ አንድ ናቸዋ! ዛሬ ግን ሌሎች ተሳዳቢዎች በቅለውልናል። በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ያልነበሩ፥ እግዚአብሔር ያልነበሩ፥ በሥጋ የተገለጠ አምላክ ያልሆኑ፥ እኔና አብ

አንድ ነን ይሉናል። ኃይሉ ዮሐንስን ተሳድበሃል የሚለው እስካሁን የጠፋ አይመስለኝም፤ አልሰማም እንጂ ከዚህ በፊት ጥቂት ወገኖች ነግረውታል፤ በስሕተቶቹ ላይም ጽፈዋል። አልሰማም እንጂ። እኔም ልበለው፤ ኃይሉ ዮሐንስ እና ይህን መሰል ስድብ በእግዚአብሔር ላይ የምትናገሩ፥ ተሳድባችኋል፤ አንተና አብ አንድ አይደላችሁም። ሌሎችም ካላችሁ፥ እናንተና አብ አንድ አይደላችሁም። እናንተን ማየት አብን ማየት አይደለም። ስድባችሁን አርቁልን።

እነዚህ ከላይ ያየናቸው ሁለቱ ትልልቅ አደጋዎች ናቸው። 1ኛው አደጋ፥ ሰው መንፈስ ከሆነ *ሥጋው* በኃጢአት ቢረከስም መንፈሱ የታተመችና የተጠበቀች ናት የሚል የኃጢአት ፈቃጅነት፥ አለማማጅነትና ተለማማጅነት ሲሆን፥ 2ኛው አደጋ፥ ሰው አምላክ ነው ማሰኘቱ ነው።

## ኮራጆች

ከዚህ ከሁለተኛው አደጋ ጋር ተያይዞ በተለይ ሰው በአምላክ አምሳል የተፈጠረ አምላክ ነው ስለሚሉት አሳብም በትንሹ አይተናል። ይህንን ክፍል ስናይ ይህ ትምህርት በኛዎቹ የኮረጆ፥ በአሜሪካዎቹ አሳቾችና የስሕተት ትምህርት አስተማሪዎች ተቦክቶ የተጋገረ መሆኑም አይተናል። እነሱም ራሳቸው አንዱ ከሌላው እየኮረጁት እያንከባለሉት ነው እዚህ ያደረሱት። ኬነት ሄግን ከኬንየን ኮርጆ የራሱ አድርጎ ያቀረበውን ቃል በቃል የሰረቀው ስርቆት ነው። ኩረጃ ብቻ ሳይሆን ስርቆትም ነው፤ ፕሌጀሪዝም ይባላል በስነ ጽሑፍ ቋንቋ። የማን መሆኑን ሳይናገሩ፥ ምንጩን ሳይጠቅሱ የራስ አስመስሎ ማቅረብ ማለት ነው።

ከኩረጃው ናሙና አንድ ገጽ በቀጣዩ ገጽ ይገኛል። ይህን ኩረጃ በመጀመሪያ D. R. McConnell በጻፈው A Different Gospel በተባለው መጽሐፍ ነበር ያየሁት። ያኔ ከ25 ዓመታት በፊት *መንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶች* የተባለውን መጽሐፌን እየጻፍኩ ሳለሁ ነበር ያነበብኩት። ግርማዊ በጻፈው *የብልጽግና ወንጌል* በተባለ መጽሐፍ ከተቀመጠው ስድስት የኮፒ ገጾች ውስጥ አንዱን ብቻ ብንወስድ ይህን ይመስላል።[8]

---

[8] *የብልጽግና ወንጌል*፤ ግርማዊ፤ ገጽ 156-161።

### የአሳብ ሥርቆት (Plagiarism)

ከነት ሐገን ከከንየን ጽሑፎች ገልብጦ ሲያበቃ የራሱ አስመስሎ ስላቀረባቸው አሳቦች ቀደም ብለን ተነጋግረናል። ይህም ሐገን የከንየንን አሳቦች በመሥረቅ (plagiarism) አግባብነት የጎደለው ተግባር እንደፈጸመ የሚያሳይ ነው። ምንም እንኳ የዚህ ዓይነቶቹ የሥርቆት አሳቦች እጅግ በርካታ ቢሆኑም፥ ለአብነት ያህል የሚከተሉትን አቅርበንላችኋል።

***Kenneth Hagin***

*The 22nd Psalm gives graphic picture of the crucifixion of Jesus_ more vivid than of John, Matthew or Mark who witnessed it.*

*He utters the strange words "But thou art holy." What does that mean? He is becoming sin.... His parched lips cry, "I am a worm and no man." He is spiritually dead_the worm. Jesus died of a raptured heart. When it happened, blood from all parts of His body poured through the rent into the sack which holds the heart. As the body cooled, the red corpuscles coagulated and rose to the top, the white serum settled to the bottom. When that Roman spear pierced the sack, water poured out first, then the coagulated blood oozed out, rolling down his side onto the ground. John bore witness of it. ("Christ Our Substitute," The Word of Faith (Mar., 1975, pp. 1, 4, 5, 7).*

*What does Identification mean?*

*It means our complete union with*

***E. W. Kenyon***

*The twenty-second Psalm gives a graphic picture of the crucifixion of Jesus. It is more vivid than of John, Matthew or Mark who witnessed it.*

*He says the strongest words, "But thou art holy." What does mean? He is becoming sin. Can you hear those parched lips cry, "I am a worm and no man"? He is spiritually dead. The worm. Jesus had died of ruptured heart. When that happened blood from all parts of the body poured in through the rent, into the sack that holds the heart. Then as the body cooled, the red corpuscles coagulated blood oozed out, rolled down His side onto the ground, and John bore witness of it. (What Happened from the Cross to the Throne (Seattle: Kenyon's Gospel Publishing Society, 1969), 44-45).*

*At once you ask, "What does identification mean?"*

156

ሄግን የፈጠረው ሳይሆን የኮረጀው ስሕተት ነው። የኮረጀውም ከኬንየን ነው። ኬንየን ራሱ ከማን ኮረጀ ወይም ከየት አገኘው ስንል ፍተሻው ወደ ወደ ፊኒየስ ኩምቢ፥ ከዚያም ወደ ዲቦ-አካላውያን ትምህርቶች ይወስደናል። ሰዎቹ ሲኮርጁ ጽሑፍ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ነገሮችን ቃል በቃልም ነው። እነ ኃይሉም አንዳንድ ኃይለ ቃሎችን በእንግሊዝኛ የሚናገሩት የኮረጁት ስለሆነ ነው።

ኮፕላንድ ሄግንን ሲኮርጅ ሙልጭ አድርጎ ነው። ሄግን በ120 ዓመቴ እሞታለሁ እያለ ይናገር ነበር፤ 120 አልደረሰም፤ በ86 ዓመቱ ነው የሞተው፤ 34 ሲቀረው። ኮፕላንድም በ120 ነው የምሞተው ይላል፤ ዘንድሮ በ83 ዓመቱ ነው ይህን ያለው። እነዚህ ሰዎች ጳውሎስ እንደናፈቀው ወደ ጌታ መሄድን አይናፍቁም። ከምድር ጋር ከተጠፈርን፥ ከምድር ጋር ከተጣበቅን፥ ከምድር ጋር ከተበየድን፥ መናፈቅ ምን ይሠራል? ምን ይሠራል? Joel Osteen *Your Best Life Now* ብሎ እንደጻፈውና እንዳስተማረው ነው ነገሩ። 'የኔ ምርጡ ሕይወት አሁን እና እዚህ!' የምንል አሁንን እንጂ ወደፊትን የማንናፍቅ ሰዎች ከሆንን እነዚህን ሰዎች መስማት ትክክለኛ ምርጫ ነው፤ ስሟቸው። የኔ ምርጡና የላቀው ሕይወት ገና የሚመጣው ነው የምንል ግን ቃሉን እንመርምር። ኮፕላንድ አሁን 83 ዓመቱ ነው። ከ17 ዓመታት በኋላ መቶ ዓመት ሲሞላው፥ 'እንዴ! እንዴት ነው? ተረሳሁኝ እንዴ?' እንደሚል እርግጠኛ ነኝ። ዕድሜኑም ይኮርጁና 120 የሚል ያለበትን ጥቅስ ፈልገው ይስጉበታል። ይህ መሳግ ወይም ሰጊጎተ ቃል ይባላል፤ ስለ ሰጊጎተ ቃል ኋላ ትንሽ እልበታለሁ።

ኩረጃ እኮ ከሌላው መማር ከሆነ ከፋት የለበትም። ስናድግ ሁላችንም በመኮረጅ ነው የምንማረው። ካደግንም በኋላ በመኮረጅ ብዙ እንማራለን። ልንመስላቸው የምንፈልጋቸውን ሰዎች እንኮርጃለን። ጤናማ መኮረጅ ጤናማ ነገር ነው። ግን ከእገሌ ነው ያገኘሁት ሲባል ምንጩን እንድንፈትሽ ስለሚያደርገን ጥሩ ነው። የስሕተት አስተማሪ ስሕተት ሲኮረጅ ስሕተት መኮረጅ መሆኑ ሳይጠፋን፥ መካድ ደግሞ አላስፈላጊ መሆኑን ማወቅም ጥሩ ነው። የኃይሉ ዮሐንስ ትምህርት የተኮረጀ ነው ሲባል የተኮረጀባቸው ምንጮች መጤን እንዳለባቸው ማመልከቴ ነው። ባለፈው እንዳልኩት፥ ምንጩ ከተበላሸ ጅረቱ የተበላሸ ነው። ስሕተት ሲኮረጅና በሌላ ሰው ሲነገር ወደ ትክክልነት አይለወጥም፤ ያው ስሕተት ነው።

## ስም መጥራት

በዚህ ሥራ ውስጥ ስም ባልጠራ እወድ ነበር። እዚህ ትምህርት ላይ ደጋግሜ የጠራሁትና የምጠራው ስም ኃይሉ ዮሐንስ የሚል ስም ነው። ሌሎች አንዴና ሁለቴ የጠቀስኋቸው ስሞችም አሉ። ስም አለመጥራት መልካም ነበር፤ ግን ምን ይደረጋል? ስም ሳይጠራ ስሕተትና አሳች እንዴት ይገለጣል? ስም ሳልጠቅስ ቪድዮ ብቻ ማሳየትም ቢሆን ያው ነው። ፎቶውን አስቀምጦ ኦዲዮውን ብቻ ማሰማትስ? ያው ነው። 'ተንቀሳቃሽ ወይም የገጽ ምስል ነው ያሳየሁት እንጂ ስም አልጠራሁም' ማለትና መሸሽና ማምለጥ ይቻላል? አይቻልም። ብዙ ጊዜ በሐሰት ትምህርቶችና የሐሰት

ልምምዶች ላይ እጽፋለሁና ስሞች እጠራለሁ። ይህንን የማደርገው በሁለት ምክንያቶች ነው።

1ኛ፥ ሐሰትን ለመግለጥ ከሐሰት ጋር ሐሰተኞችም በጠቀስ አለባቸው። ታሪክም አስተማሪያችን ነው።

በዚህ ጉዳይ ላይ መጀመሪያ የጻፍኩት መጽሐፌን የጻፍኩት ከ25 ዓመታት በፊት ነው። ያኔ በአገራችን ስም ያበቀሉ ገና አልነበሩምና የውጪዎቹን ወንጫፊዎች ነው የጠቀስኩት። ያም ብዙዎችን አስደንጦና አስቆጥቶ ነበር። ከዚያ ወዲህም እየጠቀስኩ እጽፋለሁ። 'ስም አይጠራም፥ ስም አትጥራ፤ እገሌ፥ ማንትስ አትበል' የሚሉኝ ጥቂት አይደሉም። የስሕተት አስተማሪዎች ስም ሲጠራ ስግጥ የሚያደርጋቸው፥ ላለማስከፋት ታጥቀው የቆሙ አስደሳቾችና ስም እንዳይጠራ ተግተው የሚከላከሉ አስናፊዎች ብዙ ናቸው። ስም አለመጥራት መልካም ነበር፤ ግን ምን ይደረግ? ስም ሳይጠራ ስሕተትና አሳች እንዴት ይገለጣል?

ኃይሉ ዮሐንስም በቅርብ ባየኋቸው ሁለት ቪድዮዎቹ ዶ/ር ራቪ ዛካሪያስ የተባለውን መካቴ ክርስትና አድንቆ፥ ዶ/ር ሃንክ ሃነግራፍ የተባለውን ደግሞ አብጠልጥሎ ተናግሯል። ልዩነታቸውን ሲተነትን የመጀመሪያው ስም አለመጥቀሱና ሁለተኛው ስም እየጠራ ስሕተታቸውን መግለጡ ነው። እነዚህ ሁለቱም ሰዎች በአንክሮ የማያቸውና የምማርባቸው ሰዎች ናቸው። ራቪ በቅርብ ወደ ጌታ ተሰብስቧል። ሁለቱም ንጥር የምካቴ ክርስትና አገልጋዮች እና የቤተ ክርስቲያን አንጡራ ሀብቶች ናቸው። አገልግሎቶቻቸውን በቅርብ የሚያውቁ እንደሚያስተውሉት ደግሞ የሁለቱም አቀራረብ የየራሱ መልክ አለው። ኃይሉ ዮሐንስ የሚጠየፈው ሀንክ በስም እየጠቀሰ የሚገልጣቸው ሰዎች በስም ተጠቅሰው ካልተገለጡ በቀር በምንም ሌላ መንገድ መገለጥ አይችሉም።

ሀንክ በሳልና ጠንካራ የምካቴ እምነት ሰው፥ ዕለታዊ የሬድዮ አስተማሪና የብዙ የምካቴ ክርስትና መጻሕፍት ጸሐፊ ነው። ባልና ሚስቱን ኮፐላንዶችን ጨምሮ የ E. W. Kenyon, K. E. Hagin, Benny Hinn, F. K. C. Price, John Avanzini, R. Tilton, Marilyn Hickey, P. Yonggi Cho, Jerry Savelle, Charles Capps, Paul Crouch, Joyce Meyer, Paula White, Joel Osteen እና ሌሎችም የቃል-እምነት ሰባኪዎችን ያገጠጡና ከመጽሐፍ ቅዱስ ያፈነገጡ ስሕተቶችን ሳይደክም የገለጠ ሰው ነው። እጅግ ብዙዎችን ወደዚህ ትምህርት ወጥመድ እንዳይገቡ የረዳ፥ የገቡትም እንዲወጡ የታተረ አገልጋይ ነው። ስንቶች ወጥተዋል? ስንቶች አምልጠዋል? ሀንክ በኃይሉ ዮሐንስ አንደበት ተንቋሾ መብጠልጠል ነበረበት? አዎን፤ ለምን? አባቱ ኮፐላንድ ተነክቷላ! ሃንክ ደጋግሞ ከሚጠቅሳቸው መካከል የኃይሉ አሳዳጊ ኬነት

ኮፐላንድ ይገኝበታል። ምናልባት ያስቆጣው የሱ መጠራትም ሊሆን ይችላል። እነዚህ አሳቾች የሰዎች ደም መጣጮች ናቸው፤ አደገኞች ሳይሆኑ ራሳቸው አደጋዎች ናቸው። አደጋ አይቶ ዝም ማለት አይቻልም። አያችሁ? ስም ከተጠራ ዝም ብሎ ስም አይጠራም፤ ትምህርታቸው መነገር አለበት። ሀንክ ሃነግራፍ የዚያ ዓይነት ሰው ነው።

ኃይሉ ዮሐንስ ስለ ሀንክ ሲናገር ደግሞ በልሳን አይናገርም ብሎ ነበር። የሐሰት ትምህርትን ለመግለጥ ልሳን መለኪያው አይደለም። ልሳንንማ ኩንዳሊኒዎችም ይናገራሉ። በእስታቲስቲክስ ብሄድ እኔ ከማውቃቸው ልሳን የሚናገሩ ሰዎች ከመቶው ውስጥ 99ኙ ወይም 98ቱ ሰምተውና ተለማምደው የሚናገሩ ናቸው። በዚህ ጉዳይ ላይ ሁለት ቪድዮዎች (በመንፈስ ቅዱስ መሞላትና በልሳን መናገር ግንኙነት አለቸው? እንዲሁም፥ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅና በልሳን መናገር ግንኙነት አለቸው? የተባሉ ሁለት ቪድዮዎች አሉና ተመልከቷቸው።[9] ለአንባቢዎች ደግሞ፥ መንፈስ ቅዱስ እና ካሪዝማዊ ቀውሶች ምዕራፍ 2 ከገጽ 88 ጀምሮ እና ምዕራፍ 3 ከገጽ 198 ጀምሮ ተመልከቱት።[10] ለምካቴ ክርስትና በልሳን መናገር ከቶም መለኪያ አይደለም። ልሳን ቢበዛ፥ በጣም ቢበዛ፥ ከጸጋ ስጦታዎች አንዱ ብቻ ነው እንጂ የምካቴ እምነት መለኪያ አይደለም። በተለይ 1ቆሮ. 14ን ያነበበ ሰው ይህን አይልም።

የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችን ስሕተት ለመግለጥና እምነትን በትክክል ለመመከት መሆን ያለብን ነገር የክርስቶስ ደቀ መዝሙርና የቃሉ ኮስታራ ተማሪዎች ብቻ ነው እንጂ አንድ ወይም ሌላ ስጦታ መቀበል አይደለም። ይህ ደግሞ የጊዜ ዋጋ መክፈል የሚወድና ቃሉን በትጋት የሚመረምር ማንም አማኝ መሆን የሚችለውና ሊሆንም የተገባው ኃላፊነት ነው።

ኃይሉ ዮሐንስ አምና የወጣውን ባዕድ-ቅይጡ ወንጌል ዘጋቢ ቪድዮ ነፍሱ አምርራ ስለጠላችው፥ ከዚያ ጋር አያይዞ እኔ የማደርገውን እንዲህ ያለውንም የቪድዮ እና የጽሑፍ የሐሰተኞች መግለጥ ነገር፥ 'የስም ማጥፋት ሚኒስትሪ' ብሎታል። ከአንዴም ሁለቴ እኔን ራሴንም ጠቅሶ የስም ማጥፋት ሚኒስትሪ የለም ብሏል። ስም አለመጥራት መልካም ነበር፤ ግን ምን ይደረግ? ስም ሳይጠራ ስሕተትና አሳች መግለጥ ስለማይቻል ስም ይገለጣል። ስሕተትን መናገርን እንደ ስም ማጥፋት አድርገው የሚያስቡና የሚናገሩ ስላሉ ይህ ራሱ ስሕተት መሆኑን መናገር እፈልጋለሁ።

---

[9] https://www.youtube.com/watch?v=s07c4jE1wDw እና https://www.youtube.com/watch?v=rLfSANxxvVY

[10] መንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶችን በነጻ ከዚህ ማውረድ ይቻላል፤ http://www.good-amharic-books.com/library?id=107

ስሕተትን መናገርና ስም ማጥፋት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። የነዚህን የሁለቱን ልዩነት ለማያውቁም ማሳወቅ እፈልጋለሁ። ስም ማጥፋት ማለት ያላደረጉትን እንዳደረጉ በማለት፥ በውሸት፥ በፈጠራ፥ የሰውየውን ክብር፥ ቤተ ሰባዊ እሴቶቹን፥ ማኅበራዊ መስተጋብሮቹን፥ ሥራውን፥ እና የመሳሰሉትን ስፍራዎቹን ለማስጣል የሚደረግ ውሸት ያለበት አሉባልታ፥ ሐሜት፥ ተንኮል፥ እና ሴራ ነው። ውሸት የሚሆነው ያላደረገውን፥ 'አደረገ፤' ያልሆነውን፥ 'ሆነ፤' ያላለውን፥ 'አለ፤' ስለሚባል ነው። ይህ ስም ማጥፋትና ማጠልሸት ነው።

ስሕተትን መግለጥ ግን የተናገሩትን፥ ያስተማሩትን፥ ቀርጸውና ተቀርጸው አየር ላይ ያደረጉትን፥ የጻፉትን፥ ያሰራጩትን እንደ ማስረጃ እያቀረቡ ይህ ትምህርት ከቃሉ ጋር ይጋጫል፤ ስሕተት ነው፤ ውሸት ነው፤ ቅጥፈት ነው፤ ያስታል፤ ከእውነት ያርቃል፤ ከጌታ መንገድ ያስወጣል፤ ወደ ጥፋት ይመራል ብሎ የማስጠንቀቅ ተግባር ነው። ይህንን ማድረግ ስም ማጥፋት ሳይሆን፥ ይልቁን አለማድረግ ግን አደጋ ነው።

አባቶች እኮ ስም እየጠሩ ሐሳውያንን ገልጠዋል። የቀድሞዎቹ አርዮስ ብለው ስም አልጠቀሱም? ንስጥሮስ፥ መርቅያን፥ ሞንታኖስ፥ ሰባልዮስ፥ አቡልናርዮስ፥ ወዘተ፥ ብዙ ወዘተ፥ አላሉም? ብለዋል። የቅርቦቹና የዘመናችን ደግሞ Joseph Smith, Charles Russel, Herbert Armstrong, Kenneth Hagin, Kenneth Copeland ወዘተ፥ አላሉም? ስም አለመጥራት ጥሩ ነበር፤ ግን ስም ደብቆ ስሕተት መግለጥ አይቻልም። ስም መደበቅና ስሕተት መግለጥ አብረው አይሄዱም። ወይ ዝም ማለት ነው፤ ካልሆነ ደግሞ ማስረጃ ማቅረብ የግድ ነው። ስም መጥቀስ ቀፋፊ ነገር ቢሆንም ትክክለኛ ጉዳይ ነው። አሳቾችንና ሽቃጮችን በስም መጥቀስ ነውር አይደለም። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተደረገ ነገር ነው።

2ኛ፥ መጽሐፍ ቅዱስም ስም ጠቅሰው የተናገሩ አስጠንቃቂዎችንም፥ ስማቸው የተጠቀሰ አሳቾችንም ይነግረናል።

ሐዋርያቱ አሳቾችንና ክፉዎችን በስም ጠርተዋል ወይስ እንዲያው በድፍንፍን ነው ያለፉአቸው? ጠርተዋል፤ ጽፈዋል፤ ሳይንተባተቡ ጠቅሰዋል። ጳውሎስ ሄሜኔዎስና ፊሊጦስ እያለ ስም አልጠራም? ጠርቶአል። 1ጢሞ. 1፥19-20 *እምነትና በጎ ሕሊና ይኑርህ፥ አንዳንዶች ሕሊናን ጥለው፥ መርከብ አለ መሪ እንደሚጠፋ፥ በእምነት ነገር ጠፍተዋልና፤ ከእነዚያም፥ እንዳይሳደቡ ይማሩ ዘንድ ለሰይጣን አሳልፌ የሰጠኋቸው፥ ሄሜኔዎስና እስክንድሮስ ናቸው።* አለ።

በ2ጢሞ. 1፥15 ላይ፥ *በእስያ ያሉቱ ሁሉ ከእኔ ፈቀቅ እንዳሉ ታውቃለህ፥ ከእነርሱም ፊሎጎስና ሄርሞጌኔስ ናቸው።* ይህ ሄሜኔዎስ ከላይ የተጠቀሰው ሰው ነው። ተሳዳቢ፥ አፉ ከልክ በላይ የሚከፈት፥ የሚመራው ሕሊና የሌለው ሕሊናቢስ የሆነ ሰው ነው።

ከሄሜኔዎስ ጋር ተባባሪ የሆነ ሌላ ሰው ተጠቅሷል፤ *የናስ አንጥረኛው እስክንድሮስ እጅግ ከፋብኝ፤ ጌታ እንደ ሥራው ይመልስለታል። አንተም ደግሞ ከእርሱ ተጠበቅ፥ የምንናገረውን እጅግ ተቃውሞአልና።* 2ጢሞ. 4፥14-15። ያላመኑ ሰዎችን አይደለም የጠራው። አምነው የነበሩ ወይም አማኝ መስለው ባመኑት መካከል የሚመላለሱትን እምነት ገልባጮች ስም ነው የጠቀሰው። 'የሆኑ ሁለት ወንድሞች' አላለም። 'አንድ የሆነ ናስ አንጥረኛ' አላለም። ቢል ኖሮ አማኞች ናስ አንጥረኞችን ሁሉ ሊጠረጥሩ ነው።

ዮሐንስ ጋይዮስን፥ ድሜጥሮስን በስም ጠርቶ እንዳመሰገናቸው፥ ዲዮጥራጢስን በስም ጠርቶ አውግዞአል። *ወደ ቤተ ክርስቲያን ጻፍሁ፤ ዳሩ ግን ዋናቸው ሊሆን የሚወድ ዲዮጥራጢስ አይቀበለንም። ስለዚህ፥ እኔ ብመጣ፥ በእኛ ላይ በክፉ ቃል እየለፈለፈ የሚያደርገውን ሥራውን አሳስባለሁ፤ ይህም ሳይበቃው እርሱ ራሱ ወንድሞችን አይቀበልም፥ ሊቀበሉአቸውም የሚወዱትን ከልክሎ ከቤተ ክርስቲያን ያወጣቸዋል።* 3ዮሐ. 9-10።

ጌታ በራእ. 2፥20 *ዳሩ ግን፡- ነቢይ ነኝ የምትለውን ባሪያዎቼንም እንዲሴስኑና ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉ የምታስተምረውንና የምታስተውን ያችን ሴት ኤልዛቤልን ስለምትተዋት የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤* አላለም? ስም ሳይጠቅስ ድርጊቷን ብቻ ቢዘረዝርም ትታወቅ ነበር እኮ! ግን በስም ተጠቀሰች።

እስክንድሮስ፥ ሄሜኔዎስ፥ ፊሊጦስ፥ ፊሎጎስ፥ ሄርዋጌኔስ፥ ዲዮጥራጢስ፥ ኢያኔስና ኢያንበሬስ፥ ኤልዛቤል፥ ወዘተ፥ የመድኃኒት ስሞች ይመስላሉ እንጂ እኮ አይደሉም። አሳቾችን በስም መጥቀስ ነውር አይምሰለን። ጳውሎስ አሳቾችን በስም እየጠቀሰ ከተናገረ እኛም የዘመናችንን አሳቾች በስም የማንጠራበት ምንም ምክንያት የለም። ባህላችን መልካም ሊሆን ይችላል፤ ግን ባህላችንን ሳይሆን ቃሉን እንከተል። ስም አለመጥራት መልካም ነበር፤ ግን ምን ይደረግ? ስም ሳይጠራ ስሕተትና አሳች እንዴት ይገለጣል? የአሳቾችን ስም መጥቀስ ስም ማጥፋት አይደለም።

ስለዚህ ስምን መጥቀስ በክርስትና ታሪክም በቅዱስ ቃሉም የተነገረ ጉዳይ ነውና ስምን እየጠቀሱ ስሕተትን መግለጥ ተገቢ ነው።

## 'አማልክት ናችሁ።'

'ሰው መንፈስ ነው' ለሚለው ሙግት ከሚያቀርቧቸው ጥቅሶች አንደኛውን ምላሽ፥ "እናንተ አማልክት ናችሁ' ይላልና አማልክቶች ነን።' ይላሉ። ኬነት ኮፕላንድ እኔ ትንሽ አምላክ ነኝ ማለት የጀመረው በቅርብ አይደለም፤ ከፖል ክራውች ጋር ካደረገው የቴሌቪዥን ስርጭቶች ከቀደሙት፥ ቆየት ካሉት መካከል በአንዱ ይህንን በግልጽ ተናግሯል።

ቃሉ፥ 'አማልክት ናችሁ' ሲል እግዚአብሔር፥ ትንንሽ እግዜሮች፥ የእግዚአብሔር ዓይነቶች፥ የእግዚአብሔር መደብ ናችሁ ማለቱ ነው? በእውነት ስለ አምላክ፥ ስለ ፈጣሪ አምላክነት ወይም የእርሱ ዓይነትነት እና የእርሱ መደብነት መናገሩ ነው? እዚህ ላይ የቃለ እምነት አሳቾችን ስነ አፈታት ማየት ተገቢ ነው። አሳቾች ወይም የስሕተት ትምህርት አስተማሪዎች በጠቅላላው በቀረቤታ ስናያቸው ጥቅስ ለቃሚዎች፥ ነጣቂዎች፥ ቦጫቂዎች፥ እና መንጣቂዎች ናቸው እንጂ ጥቅስን በዐውዱ ማየት የሚችሉ ሰዎች አይደሉም። ትምህርቶቻቸውን በሙሉ ብትመለከቱ በርእስ ነው የሚያስተምሩት እንጂ ምንባብ በመውሰድና ሰፊውን ዐውድ በማየትና በማሳየት አይደለም። ገላጭ ስብከት ወይም expository preaching / teaching የሚባለውን አያውቁትም፤ አያደርጉትም። አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ በመውሰድ፥ ጀምረው እስኪጨርሱ በዚያ መጽሐፍ ላይ በመቆየት አያስተምሩም።

ገላጭ ስብከት ወደ ፈቲሖተ ቃል (ወይም exegesis) ይመራናል። ወደ ቃሉ ውስጥ ገብተን የቃሉን አሳብ፥ የጸሐፊውን አሳብ ይዘን እንድንወጣ ያደርገናል። ያለዚያ ደግሞ፥ የፈቲሖተ ቃል (ወይም exegesis) ተቃራኒ የሆነውን eisegesis (ወይም ሰጊኅተ ቃል) የሚባለውን በደል እንፈጽማለን። በፈቲሖት ወይም በመፍታት ፈንታ፥ የራሳችንን አሳብ በቃሉ ውስጥ እንዶላለን፤ እንስጋለን፤ የመሳግ ሥራ እንፈጽማለን፤ ሰጊኅት ያልኩት ያንን ነው። መሳግ ማለት ባሕላዊ ቤት ሲሠራ ጣራ ላይ ከምሰሶ ጀምሮ ወደ ግድግዳ የሚወርድ ወራጅ የሚባል እንጨት አለ። በጊዜ ብዛት ቤቱ ያረጅና ጣራው ይዘብጣል፤ ውኃ መያዝና ማፍሰስም ይጀምራል። ያንን ለማጠንከር ተብሎ ወራጅ ይሳግበታል፤ መሳግ ይባላል። የዘበጠ ሊወድቅ ያዘበዘበ ትምህርታቸውን ጥቅስ በመሳግ ሊያጠነክሩ የሚፈልጉ ሰዎች ሰጊኅተ ቃል እየፈጸሙ ነው።

አሳቾች ጥቅስ ይቦጭቃሉ እንጂ መጽሐፍ አያስተምሩም፤ መጽሐፍን ካስተማሩ ራሳቸውን የሚያጮላቸውን ክፍል መሸሽ፥ መዝለል ስለማይችሉ ያንን አያደርጉም። ለምሳሌ፥ ኬኔት ኮፕላንድ ብዙ መጽሐፎች ጽፏል፤ በገላጭ ስብከት መልክ

ያስተማረበት አንድም የመጽሐፍ ቅዱስ የብሉይ ወይም የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ግን የለም፤ አንድም። ከኖረ እታረማለሁ። ከብሉይም፥ ከአዲስ ኪዳንም ምንም የጻፈበት መጽሐፍ የለም።። ነገር ግን ቀደም ሲል እንዳልኩት፥ 120 ዓመት እኖራለሁ ሲል ከዘፍ፣ 6፥3 ወስዶ ነው የሳገው! ያ ጥቅስ ስለ ኮፕላንድ የሚናገር አይደለም። ስለ ሰው ልጆች ሁሉም የሚናገር አይደለም፤ ቢሆን ኖሮ ሰው ሁሉ 120 ዓመት እየኖረ ይሞት ነበር። እነዚህ ሰዎች ጥቅስ በመንጠቆ ነጥቀው ገምደው ማቅረብ ይችላሉ፤ በዐውዱ ቢያጠኑት የማይለውንና ያላለውንም ያስብሉታል። አማልክት ናችሁ የሚለውንም ሲወስዱት ጥቅሷን መንጥቀው ነው ያላለውን የሚያስብሉት።

አማልክት ናችሁ ወደሚለው ጥቅስ ስንመጣ፥ 'አማልክት ናችሁ' የሚለው ሐረግ ለብቻው ከጠቅላላው ምዕራፍ ተነጥቆ መውጣት የለበትም። ከወጣም ቃሉ ምን ማለት ነው? ምንን ይገልጣል? ከነዚያ ከገለጣቸው ነገሮችስ አምላክነት አለበት ወይ? ብሎ መጠየቅ ትክክለኛው መድረሻ ላይ ያደርሳል። በመዝ. 82 ያለው አማልክት የሚለው ቃል אֱלֹהִים ኤሎሂይም የሚለው ቃል ነው። ቃሉ በዋናነት ለእግዚአብሔር መጠሪያነት ቢያገለግልም ለሌሎች ሦስት አካላትም መግለጫነት ውሎአል፤ እነዚህም ጣዖታት፥ መላእክት፥ እና አለቆች የሆኑ ሰዎች ናቸው። ሦስቱንም እንይ፤ ለሦስቱም ሁለት ሁለት ምሳሌዎችም ልስጥ፤

ሀ) ጣዖታትን በተመለከተ ለምሳሌ፥ ዘጸ. 20፥3 ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ ሲል ጣዖታትን ነው። ሲል ሌሎች ኤሎሂይም ነው። ወይም በዘጸ. 32፥1 እና 4 ሕዝቡም ሙሴ ከተራራው ሳይወርድ እንደ ዘገየ ባዩ ጊዜ፥ ወደ አሮን ተሰብስበው፦ ይህ ከግብፅ ምድር ያወጣን ሰው ሙሴ ምን እንደ ሆነ አናውቅምና ተነሥተህ በፊታችን የሚሄዱ አማልክት ሥራልን አሉት። . . . ከእጃቸውም ተቀብሎ በመቅረጫ ቀረጸው፥ ቀልጦ የተሠራ ጥጃም አደረገው፤ እርሱም፦ እስራኤል ሆይ፥ እነዚህ ከግብፅ ምድር ያወጡህ አማልክትህ ናቸው አላቸው። ሲል ኤሎሂይም ነው። እና እዚያ አሮን ጠፍጥፎ የሠራው የወርቅ ጥጃ ኤሎሂይም ወይም አምላክ ነው? ጣዖት እንጂ አምላክስ አይደለም። ሊሆንም አይችልም። ቃሉ አማልክት ስላላቸው፥ አማልክት የተባሉ ሁሉ ትልልቅም ትንንሽም እግዚአብሔር ናቸው ማለት አይደለም።

ለ) መላእክትም ኤሎሂይም ተብለዋል። መዝ. 8፥5 ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስኸው፤ በክብርና በምስጋና ዘውድ ከለልኸው። በሚለው መላእክት የሚለው ኤሎሂይም ነው። እና መላእክት እግዚአብሔር ናቸው? አይደሉም። መዝ. 97፥7 ለተቀረጸ ምስል የሚሰግዱ ሁሉ፥ በጣዖቶቻቸውም የሚመኩ ይፈሩ፤ መላእክቱ ሁሉ፥ ስገዱለት። በሚለው መላእክቱ የሚለው ኤሎሂይም ነው። ሰጋጆቹ መላእክት እግዚአብሔር ናቸው? አይደሉም። አንድ ጨምረን እንይ፤ መዝ. 138፥1 አቤቱ፥

በፍጹም ልቤ አመሰግንሃለሁ፥ የአፌን ነገር ሰምተኸኛልና፤ በመላእክት ፊት እዘምርልሃለሁ። በሚልበት መላእክት የሚለው ኤሎሂይም ነው። መላእክት እግዚአብሔር ናቸው? አይደሉም። ቃሉ አማልክት ስላላቸው፥ አማልክት የተባሉ ሁሉ ትልልቅም ትንንሽም እግዚአብሔር ናቸው ማለት አይደለም።

ሐ) የሰው አለቆችንም አማልክት በማለት ይናገራል፤ ይህ፥ 'ሰው አምላክ ነው' በሚሉ ሰዎች የሚጠቀሰው መዝ. 82ም ስለነዚህ ነው የሚናገረው። ከዚህኛው በፊት ግን ለምሳሌ ያህል አንድ ሁለት እንይ። ዘጸ. 4፥16 እርሱ ስለ አንተ ከሕዝቡ ጋር ይናገራል፤ እንዲህም ይሆናል እርሱ አፍ ይሆንልሃል አንተም <u>በእግዚአብሔር</u> ፋንታ ትሆንለታለህ። ሲል በእግዚአብሔር ፋንታ የሚለው ኤሎሂይም የሚለው ቃል ነው። ሙሴ ወኪሉ ነው እንጂ፥ እግዚአብሔር አይደለም።

ዘጸ. 7፥1 እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፡- እይ፥ እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ፤ ወንድምህም አሮን ነቢይ ይሆንልሃል። ሲል ሙሴ እግዚአብሔር አይደለም፤ ሊሆንም አይችልም። ግን ወኪል ነው፤ አለቃ ነው። ቃሉ ግን ኤሎሂም ነው።

መዝ. 82 አጭር መዝሙር ነው። በመዝ. 82፥6 የተጻፈው አማልክት በስፍራው፥ በዐውዱ ሲጠና ቃሉ አማልክት ቢልም አምላኮች ወይም እግዜሮች መሆናቸውን አይናገርም። አለመናገሩም በግልጽ ይታያል። እነዚያ የተጻፈላቸው አማልክት የተባሉትም አለቆችና መሪዎችን እንጂ አምላኮችን አለመሆኑ ይስተዋላል። ቃሉ አማልክት ስላላቸው፥ አማልክት የተባሉ ሁሉ ትልልቅም ትንንሽም እግዚአብሔር ናቸው ማለት አይደለም። መዝ. 82 በዚህ እይታ ነው መታየት ያለበት እንጂ ተለይቶ አይደለም።

መዝ. 82፥6 እኔ ግን፡- አማልክት ናችሁ፥ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ፤ ባለበት መዝሙር ውስጥ ቁጥር 1 እግዚአብሔር በአማልክት ማኅበር ቆመ፥ በአማልክትም መካከል ይፈርዳል። በማለት ይጀምራል። እዚህ ጥቅስ ውስጥ እግዚአብሔር የሚለው ኤሎሂይም የሚለው ቃል ነው። አማልክት የሚለው ቃል ሁለቴ የተጻፈ ሲሆን የመጀመሪያው አማልክት የተሰኘው ኤል ነው። ኤል የኤሎሂይም ነጠላ ነው። ወይም ኤሎሂይም የኤል ብዙ ነው። ሁለተኛው አማልክት የተባለው ቃል ደግሞ ኤሎሂይም ነው፤ እግዚአብሔር ከሚለው አንድ ነው። ይህ መዝሙር አማልክት ሲል ስለ አምላኮች ሳይሆን ስለ ፈራጆች መናገሩ ነው። ለነገሩ፥ እግዚአብሔር በመካከላቸው የሚቆምበት የአምላኮች ዕድር የለም፤ ኖሮም አያውቅም፤ ሊኖርም አይችልም። ምንም አምላኮች የሉም፤ አምላክ አንድ ብቻ ነው፤ ሌላ የለም፤ ሊኖርም አይችልም። ይህን እናውቃለን። ይህ ክፍል ስለ አለቆች፥ ዳኞች፥ ፈራጆች መናገሩን የምናውቀው ከቀጣዮቹ ጥቅሶች ነው። ከ2-4 እንዲህ ይላል፤ *እስከ መቼ ሐሰትን ትፈርዳላችሁ?*

*እስከ መቼስ ለኃጢአተኞች ፊት ታደላላችሁ? ለድሆችና ለድሀ አደጎች ፍረዱ፤ ለችግረኛውና ለምስኪኑ ጽድቅ አድርጉ፤ ብቸኛውንና ችግረኛውን አድኑ፤ ከኃጢአተኞችም እጅ አስጥሉአቸው።*

ትፈርዳላችሁ፤ ታደላላችሁ፤ ፍረዱ፤ ጽድቅ አድርጉ፤ አድኑ፤ አስጥሉአቸው የሚሉት ቃላት የሚያሳዩት እነዚህ ሰዎች አለቆች፥ ዳኞችና ፈራጆች መሆናቸውን ነው። ያውም በጽድቅ የማይፈርዱ፥ የሚያዳሉ፥ ፍርደ ገምድል ዳኞች፥ የማያድኑ፥ የማያስጥሉ ጨካኞች መሆናቸውን ነው። ደግሞም ቁጥር 7 ላይ፥ *ነገር ግን እንደ ሰው ትሞታላችሁ፥ ከአለቆችም እንደ አንዱ ትወድቃላችሁ አልሁ።* ይላል። መላእክት አይሞቱምና ይህ ስለ ሰው መናገሩ እንደሆነ ይታያል። ስለዚህ፥ መዝ. 82፥6 የሚናገረው ቃሉ፥ 'ኤሎሂይም' የሚለው ሆኖ፥ ስለ አምላክነት ሳይሆን ስለ አለቆችና ፈራጆች ነው። እናም፥ አማልክት ነን በማለት ይህንን ጥቅስ የሚጠቅሱ ሰዎች፥ 'እኛ አለቆች ነን፤ እኛ ፈራጆች ነን' ማለታቸው ከሆነ መልካም ነው፤ መሆናቸውን ያሳዩ፥ የየትኛው ፍርድ ቤት ፈራጆች መሆናቸውን፥ የየትኛው ሸንጎና ችሎት ዳኞች መሆናቸውን፥ የየትኛው ወገን አለቃ መሆናቸውን ይግለጡና ያሳዩ። ስለ አምላክነት ይህንን ጥቅስ መጥቀስ አይችሉም።

ጌታ የጠቀሰውስ? በዮሐ. 10፥32-36 እንዲህ አለ፤ *ኢየሱስ፦ ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳየኋችሁ፤ ከእነርሱ ስለ ማናቸው ሥራ ትወግሩኛላችሁ? ብሎ መለሰላቸው። አይሁድም፦ ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ ስለ ስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት። ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፦ እኔ፦ አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን? መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና እነዚያን የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸው፥ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልሁ እናንተ አብ የቀደሰውን ወደ ዓለምም የላከውን፦ ትሳደባለህ ትሉታላችሁን?* ነበር ያላቸው።

ጌታ ይህንን ያለው፥ 'እኔና አብ አንድ ነን' ሲል ሊወግሩት ድንጋይ ባነሡ ጊዜ ነው። እነዚያ እዚያ የተጠቀሱት ፈራጆች፥ አለቆች፥ ፍርደ ገምድል ሆነው ሳሉ፥ የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸው ሰዎች ስለሆኑ፥ የእርሱ ወኪሎች ስለሆኑ፥ አማልክት ከተባሉ፥ የልዑል ልጆች ከተባሉ፥ እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልሁ፥ አብ የቀደሰውን ወደ ዓለምም የላከውን፦ ትሳደባለህ ትሉታላችሁን? ነው ያላቸው። እንዴት አላዋቂዎች እንደሆኑና ሕጉንና ቃሉን እንደማያውቁ እያሳያቸው እንጂ፥ እነዚያ ወይም እነዚህ አማልክት መሆናቸውን እያመለከተ አይደለም። እዚህ አማልክት የተባለው ቃል ከላይ እንዳየነው ለጣዖታትና ለመላእክት ጨምሮ፥ ለገዥዎችና ለፈራጆች ብዙ ጊዜ የተጠቀሰ ቃል ነው። ስለ እርሱ አምላክነት ደግሞ ይህ፥ እነሱም ምን ማለቱ ስለገባቸው ነው በድንጋይ ሊወግሩት የቃጡትና፥ አምላክነቱ ደግሞ

እውነት ነውና አጠያያቂ አይደለም። እዚህ የኢየሱስ አምላክነት ጥያቄ ውስጥ ስላልገባ መልስ ሊሰጥበት የተገባ አይደለም፤ እዚያ ግን የኢየሱስ አምላክነት ጥያቄ ውስጥ ስለገባ ነው ሊወግሩት የቃጡትና ቃሉን የጠቀሰላቸው። 'እነዚያ ፈራጆች ብቻ የሆኑት ኤሎሂይም ከተባሉ፥ እኔ ልጅ ነኝ ስላልኩ ይህን እንዴት ትላላችሁ?' ነው። ስለዚህ፥ እዚያ የተጠቀሰው ቃል በተጠቀሰበትም፥ ጌታ በተናገረበትም መልኩ ስለ አማልክት ወይም ሰው አምላክ ነው ስለሚሰኝ ስሕተት አይናገርም።

የስሕተት ትምህርቶች አንድ መታወቂያ ስሕተቶቹን የሚያስተምሩት አስተማሪዎች ግልጹን ውስብስብ ማድረጋቸውና የውስብስቡ ልቃቂት ፈቺዎች አድርገው ራሳቸውን ማቅረባቸው ነው። አሳቾች መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብተው የማይማሩት ለዚህ ነው። ከመገለጥ ኮሌጅ ተመረቅን ይላሉ። ከዚያ በኋላ የሆነ ምስጢር የተገለጠላቸው፥ ትርጉሙ እንደ አሸንዳ ውኃ የተደፋባቸው፥ ሌሎች ሊሸከሙትና ሊረድዱት የማይችሉት እውነት የወደቀባቸው አድርገው እየዘላበዱ ያልተማሩትን ሞኞች እያወናበዱ ይኖራሉ። ይህ ቀደም ሲል ያየነው ግኖስቲሲዝም የተባለው ስሕተት አንድ ገጽታ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ የተጻፈላቸው የመጀመሪያ ተቀባዮች ቢኖሩም መለኮታዊ ምንጩ ድንበርና ዘመን ዘለል ያደርገዋልና ይህ ቃል እኛም ታሳቢ ሆነን፥ እኛም ታስበን የተጻፈ ቃል ነው። ለኛ ምስጢርና ድፍን ሆኖ ለነሱ የትርጉም ምንጭ የፈሰሰባቸው አድርገው ሊያሳዩ ቢጥሩም እውነቱ ግን ያ አይደለም። ግኖስቲኮች 'እውቀት አለን' የሚሉት በሌሎች ላይ የራሳቸውን ስሕተት ለመጫን ነው። ማንም በእግዚአብሔር መንፈስ ዳግም የተወለደ አማኝ በእጁ ያለውን ቃል፥ በውስጡ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ሊያስረዳው ይቻለዋል። ቃሉ ደግሞ ጥምዝምዝና ውስብስብ፥ ጥልፍልፍና ቁልፍልፍ ሳይሆን ግልጽ ነው። የተጻፈው ቃል ስሜት የሚሰጥ ከሆነ ሌላ ስሜት ልንፈልግለት የተገባ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ከምናስበውና ከምንገምተው በላይ ግልጽ ነው። ለምሳሌ፥ ይህ እዚህ የምነጋገርበት 'ሰው መንፈስ ነው ወይም ሰው አምላክ ነው' የሚሉት ስሕተት፥ ስላወሳሰቡትና ስላጠላለፉት መልስ የምንሰጥበት ጉዳይ ሆነ እንጂ ግልጽ ነው፤ ሰው አምላክ ሳይሆን ሰው ነው። ሰው መንፈስ ሳይሆን፥ ሰው ሰው መሆኑ በጣም ግልጽ እውነት ነው።

ሰው በሥጋ ውስጥ የሚያድር ነፍስ ያለው <u>መንፈስ</u> ቢሆን ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ከማለት ምንም የሚያግደው ነገር የለም። እነሱ አሁን እንደሚሉት አድርጎ ሊያቀርበው ይችል ነበር። ሲፈጠር ሰው በማለት ፈንታ በመጀመሪያም 'መንፈስ' ይለው ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ምንንም ነገር ሳይደብቅ የሚነግረን ቃል ነው። ሰው በሚለው ቃል ፈንታ መንፈስ ማለት ይችል ነበር። ነገር ግን፥ ሰውን ሰው አለው። ሰው ነዋ! ሰው መንፈስ ኖሮ ቢሆን ሰውን መንፈስ እያለ ለመጥራት ማንም የማይከለክለው ባለ

ሥልጣን ቃል ነው። ሰው ሲጀመርም ሲጨረስም ሰው እንጂ መንፈስ አይደለም። ስለዚህ ነው ሰውን ሰው የሚለው።

'እናንተ አማልክት ናችሁ' የሚለው በቃሉ ውስጥ የተጻፈ ነው። የተጻፉት ነገሮች ሁሉ ግን ስለተጻፉ ብቻ ሁሌም የተጻፉትን ናቸው ማለት አለመሆኑን ለማወቅ የቃሉን አገባብ እና ዐውዱን ማወቅን የግድ ይላል። ለምሳሌ፥ በመዝ፣ 22፥6 ዳዊት፥ እኔ ግን ትል ነኝ ሰውም አይደለሁም፤ ይላል። ኢሳ. 41፥14 ላይም ተመሳሳይ አሳብ እናገኛለን። ዳዊት ትል ነው ወይስ ሰው ነው? ትል ነኝ ሲል በእውነቱ ምን እያለ መሆኑን ለመረዳት ዐውዱ መታየት ይኖርበታል። መዝ. 139፥14 ላይ ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ፤ ይላል። የሚቀጥለው ጥቅስ ላይ፥ አጥንቶቼ ከአንተ አልተሰወሩም። ይላል። ትል ደግሞ አጥንት የለውም። ስለዚህ ትል ነኝ ሲል ትል ነው? አይደለም። የተጻፈው በጥንቃቄና በዐውዱ መታየት አለበት። ጌታ፥ በዮሐ. 15፥5 እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ሲል ሁላችንም፥ እሱም እኛም እንጨቶች ነን ማለት ነው? አይደለም። ለዚህ ነው የተጻፉት ነገሮች ሁሉ ስለተጻፉ ብቻ ሁሌም የተጻፉትን ናቸው ማለት ያልሆነው። የተጻፈውን አሳብ ለማወቅ የቃሉን አገባብ እና ዐውዱን ማወቅ የግድ አስፈላጊ ነው። ከዐውዱና ከአገባቡ ውጪ የሚያቀርቧቸው ሌሎች ሁለት መሚገቻ ጥቅሶች አሉ። አንዱ የመለኮት ባሕርይ ተካፋይነት ነው።

## የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ መሆን መለኮት ያደርገናል?

ይህ የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ ነን የሚለው አሳብ ሰው መንፈስ ነው ወይም ሰው አምላክ ነው የሚሉ ሰዎች ስሕተት ዋቢ ሆኖ የሚቀርብ ሌላ መሚገቻ። ሰው መንፈስ ነው የሚሉ ሰዎች፤ እኛ አምላክ ነን ይላሉ። እንዴት? የመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ ነኝና አምላክ ነኝ ወይም መለኮታዊ ነኝ ይላሉ። ዋናው ጥቅስ 2ጴጥ. 1፥4 ነው፤ *ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ* <u>*ተካፋዮች*</u> *በተስፋ ቃል እንድትሆኑ፥ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን።* ይላል። በጴጥሮስ መልእክት ውስጥ የተጻፈው ባሕርይ የሚለው ቃል በሌሎች ቦታዎች ፍጥረት ወይም ተፈጥሮ የሚለው አሳብ ነው። እዚህ እየተነጻጸረ ያለው ደግሞ የዓለም ክፉ ምኞት እና የእግዚአብሔር ባሕርይ በኛ መገለጥ ነው። አሳቡን ለመጨበጥ ምዕራፉም ከመጀመሪያው ጀምሮ እንየው። 2ጴጥ. 1፥1-4

*የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያና ሐዋርያ የሆነ ስምዖን ጴጥሮስ፥ በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ካገኘነው ጋር የተካከለ የክብር*

*እምነትን ላገኙ፤ የመለኮቱ ኃይል፥ በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ፥ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን፥ በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ እውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ። ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተሰፋ ቃል እንድትሆኑ፥ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን።*

ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች የሚለውን ቃል በትነን ሦስቱንም ትልልቅ ቃላት ለየብቻ እንመልከታቸው። ሦስቱም ቃላት ትልልቅ ናቸው። እነዚህ ሦስት ትልልቅ ቃሎች፥ ባሕርይ፥ ተካፋዮች ወይም መካፈል፥ እና መለኮት ናቸው። ቃል እንደምናውቀው የአሳብ ተሸካሚ ነው። አሳብ በቃል ነው የሚገለጠው። ቃሉን ካላወቅን አሳቡን ላንጨብጠው እና ስተን ልናሳስት እንችላለን፤ ወይም ቃሉን አውቀን ሆን ብለን ያላለውን ልናስብለው እንችላለን። አሳቾች ብዙ ጊዜ የሚያደርጉት ይህን ሁለተኛውን ነው። ሆን ብለው ቃሉ የማይለውን እንዲል ያደርጉታል። ከሦስቱ ቃላት የመጀመሪያው መለኮት ነው።

## ሀ. መለኮት ወይም የመለኮት ባሕርይ

ይህንን አሳብ ባሕርይ በሚለው ስርም ከመለኮት ባሕርይ ጋር አያይዘን እንደገና እናየዋለን። መለኮት አምላክነት ወይም አምላካዊነት ነው። የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ መሆን የመለኮት ወይም የእግዚአብሔርነት ተካፋይ መሆን አይደለም፤ ወይም መመልኮት አይደለም። እኛ መለኮት አይደለንም፤ መለኮትም አንሆንም። ሞርመኖች እንደሚሉት ወደ መመልኮት የምናድግም አይደለንም። እኛ ሰዎች ነን፤ ግሩምና ድንቅ ሆነን የተፈጠርን ሰዎች ነን። ሰው መሆን ፍጥረታችን ነው። ሰውነት ልካችን ነው። በልካችን እንደተሰፋ ልብስ፥ የሚያምርብን ማንነታችን ነው፤ ሰው-ነት።

እግዚአብሔር መደብ ወይም አሳቾቹ እንደሚሉት፥ class ያለው እና እኛ ወደዚያ የምንደርስበት ዓይነት አይደለም። እርሱን የሚመስል ሌላ የለም። ሌላው ሁሉ ነገር ፍጡርና ፍጥረት ነው። ስለዚህ መለኮትን ስናስብ ፈጣሪነትን እናስብ። እኛን ስናስብ ደግሞ ፍጡርነትን እናስብ።

ከመለኮት ባሕርይ ተካፋይ መሆን እንደ ቃሉ ተካፋይ፥ ተሳታፊ፥ የተሰጠንን ተቀባይ መሆን እንጂ ያንን የተካፈሉትን ነገር ራሱን መሆን አይደለም። ለምሳሌ፥ ሰው ዘላለማዊ አይደለምና በራሱ ሕይወት የለውም፤ ዘላለማዊ አይደለምና የሕይወት

ምንጭ አይደለም። ፍጡር መሆኑ ከአምላክነት ተርታ እንዳይደርስ ያደርገዋል። አምላክ ደግሞ ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አይደለም። እግዚአብሔርም እንኳ ዘላለማዊ በመሆኑ ምክንያት በአንድ ጊዜ ፈጣሪም ፍጡርም አይሆንም። ይህ በራሱ መሆን የማይቻል ነገር ነው። ቃል ሥጋ ለበሰ ወይም ቃል በሥጋ መጣ ማለት ተፈጠረ ማለት አይደለም። አምላክ በማንነቱ ላይ፥ በመለኮቱ ላይ ሥጋን ወሰደ፥ ሥጋን ያዘ፥ ሥጋን ጨመረ፥ በሥጋ መጣ ማለት እንጂ ተፈጠረ ማለት አይደለም። አንድ ፍጡር ከተገኘ፥ ካለመሆን ወደ መሆን፥ ካለመኖር ወደ መኖር ከመጣ፥ ከተፈጠረ፥ ቀድሞ ያልነበረ ነው ማለት ነው። ቀድሞ ካልነበረ የተፈጠረ ነው፤ ከተፈጠረ ደግሞ አምላክ አይደለም፤ አምላክ አይፈጠርም። አምላክ ከተፈጠረ ያልነበረበት፥ ያልተፈጠረበት ጊዜ ነበረ ማለት ነው።

ሌላ ምሳሌን፥ ከመለኮት ባሕርያት አንዱን፥ በሁሉ ቦታ መገኘትን ብንወስድ፥ ይህ መለኮታዊ ባሕርይ ነው። ከእግዚአብሔር ብቻ በቀር በሁሉ ቦታ መገኘት የሚችል ፍጡር የለም። መላእክትም መንፈሳውያን ፍጡራን ሆነውም፥ በአንድ ጊዜ በአንድ ቦታ እንጂ በሁሉ ቦታ፥ ወይም በጥቂት ወይም በሁለትም እንኳ ቦታዎች በአንዴ አይገኙም። አይችሉም። ሰማያትና ምድር ራሳቸው የተፈጠሩ የቦታ መገኛና ድንበር ናቸው። ፍጡር ከተፈጠረ በኋላ ከነዚህ ቦታዎች በአንድ ቦታ ብቻ ነው የሚገኘው። እንኳን በሁሉ ቦታ፥ በብዙ ቦታም መገኘት አይችልም። እንኳን በብዙ ቦታ፥ በሁለት ቦታ ብቻም መገኘት አይችልም። በምድር ከሆነ በሰማይ መሆን አይችልም። በምድርም እንኳ በአንድ ቦታ ከተገኘ በሌላ ቦታ መገኘት አይችልም። ከትንሣኤ በኋላም፥ በመንፈሳዊ አካል ስንሆንም በሁሉ ቦታ መገኘት ልንሆነው የማንችለው ነገር ነው። ምን ብንበጣጠስ፥ ብንበጣጥቅ በሁሉ ቦታ መገኘት አንችልም። ሌሎች ባሕርያትንም፥ ሁሉን ማወቅንም፥ ሁሉን መቻልንም ብንወስድ እንደዚያው ነው። እነዚህ የእግዚአብሔር የብቻው ባሕርያት ናቸው። የማይሻገሩ፥ የማይተላለፉ፥ የብቻው መለኮታዊ ባሕርያት ናቸው።

ተሻጋሪዎቹን ባሕርያት ግን እዚህ ሆነንም፥ በዚህ ሥጋ ውስጥ እያለንም እንድንለማመድ ተነግሮናል። ተካፋይነታችን እዚህ ላይ ነው። ለምሳሌ፥ እዚህ ጴጥሮስ እየተናገረበት ያለው ጉዳይ ቅድስና ነው። ንጽጽሩ በዓለም ያለው ጥፋትና ክፉ ምኞት በወዲህ ከሆነ በወዲያ በመለኮት ወገን ያለው የዚህ ተቃራኒ ነው። ያም እግዚአብሔርን የመምሰል ጉዳይ ነው። የቅድስና ጉዳይ ነው። ቅድስና ከተሻጋሪ ባሕርያቱ ነውና እግዚአብሔርን የምንመስለው በተቀደሰና እርሱን በሚያንጸባርቅ አኗኗር መሆኑን ጠቅላላውን ምዕራፍ፥ እና ጠቅላላውን መጽሐፍም በማንበብ እንገነዘባለን። የባሕርይ ተካፋይነት ሰዎች ሳለን እርሱን የመምሰል ሂደት እንጂ አምላክ

የመሆኑ ጉዳይ አይደለም። ሦስቱንም ቃላት በዝርዝር እንዳየናቸው፥ የመለኮት ባሕርይ ተካፋይነት ይህ ነው።

## ሰ. ባሕርይ

የባሕርይ ተካፋይ መሆን ማለት በ2ጴጥ. 1፥4 እንደተጻፈው፥ ከፍጡርነት ወደ ፈጣሪነት የሚደረግ እመርታ ወይም የመመልኮት ወይም መለኮት የመሆን ሂደት አይደለም። ሲጀመር መፈጠራችን ብቻውን አምላክ አያደርገንም። መፈጠራችን ከፈጣሪነት ሜዳ ያስወጣናል። መፈጠራችን ብቻውን፥ 'ፍጡር እንጂ አምላክ አይደላችሁም' ይለናል። አምላክ ይፈጥራል እንጂ አይፈጠርም። ስለዚህ አንድ ነገር፥ አንድ ፍጥረት፥ አንድ ፍጡር፥ ፍጡር ከሆነ፥ ፍጡር መሆኑ ብቻ አምላክነትን ወይም ፈጣሪነትን ይሰርዘዋል። ሲጀመርም፥ ስንፈጠርም በባሕያችንር ፍጡር ስለሆንን አምላክ አይደለንም፤ ልንሆንም አንችልም፤ አምላክ አይፈጠርም።

ባሕርይ የማንነት መገለጫ ነው። ባሕርይ ለሚለው ቃል በጥቅሉ የምንጠቀመው የእንግሊዝኛ ቃል nature ወይም character ሲሆን ይህ ምንነትን፥ ፍጥረትን ወይም መገለጫ ጠባይን የሚያሳይ ነው። ጠባይ ስል፥ ጠባይ ሁለት ትርጉም አለው አንዱ ዐመል ነው። ያንን ማለት አይደለም። ሌላውን ትርጉም ከደስታ ተክለ ወልድ መዝገበ ቃላት ልውሰደውና ልፍታው። እንዲህ ይላል፤ 'ጠባይ (ዮች)፤ ጠብዐ፥ ጠባይዕ፤ የፍጥረት ኹሉ ሥር፥ መሠረት፤ ባሕርይ፥ ባሕሬ፤ መሬት፥ ውሃ፥ ነፋስ፥ እሳት።' ይላል።[11] ባሕርይ ማለት የፍጥረት ሥር፥ መሠረት ነው። ስንሠርራ፥ ስንፈጠር የኖረን፥ የተሠራንበት፥ የተፈጠርንበት ነገር ማለት ነው ባሕርይ።

ባሕርይ ከእግዚአብሔር ጋር ሲያያዝ የምንጠቀምበት የእንግሊዝኛ ቃል፥ እና የነገረ መለኮት ቃል attribute የሚል ነው። በአማርኛ ለዚህም ተመሳሳይ ቃል ነው የምንጠቀመው፤ ያው ባሕርይ የሚባል ቃል። መለኮታዊ ባሕርይን ከላይ የጠቀስኩት የደስታ ተክለ ወልድ መዝገበ ቃላት እንዲህ ይተረጉመዋል፤ 'ባሕርይ፤ (ህላዌ መለኮት)፤ ያልተፈጠረ፥ የማይመረመር፥ የማይታወቅ፥ ኀቡእ፥ ረቂቅ፤ ቅድስት ሥላሴን አንድ የሚያደርግ፥ በሥርው፥ በጉንድ፥ በነቅዕ፥ የተመሰለ የፈጣሪ ባሕርይ፤ አምላክነት።' ይለዋል።[12] የመለኮት ባሕርይን ህላዌ መለኮት ይለዋል። ህላዌ በርካታ

[11] ደስታ ተክለ ወልድ፤ ገጽ 535።
[12] ከላይ የተጠቀሰው፤ ገጽ 162።

ትርጉሞች አሉት፤ ይህኛውን የተመለከተውን አለቃ ኪዳነ ወልድ ሲፈቱት፥ 'ህላዌ፤ አካል ገጽ፥ አቋቋም፥ ቁመት፥ አኳኋን፥ ኹነታ።' ይሉታል።[13] የባሕርይ ትርጉም ይህ ነው።

ሮሜ 1፥20-21 ስለዚህ የአምላክ በሕርይ ሲናገር፥ *<u>የማይታየው ባሕርይ</u> እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም <u>አምላክነቱ</u> ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን አያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ፤ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ።* ይላል። <u>የማይታየው ባሕርይ</u> የሚለው ውስጥ ባሕርይ የሚለው ቃል የለም። የማይታየው ነገር እንደማለት ነው ቃሉ። <u>አምላክነቱ</u> የሚለው ግን (θειότης) መለኮት የምንለው ነው፤ አምላክነት ነው። ጴጥሮስ የጻፈው ቃል ይቀራረባል እንጂ ከዚህ አንድ አይደለም። ይህኛው ቃል እዚህ ብቻ እንጂ ሌላ ቦታ የማይገኝ ቃል ነው። ልክ ሰውን ወይም የሰውን ማንነት፥ 'ሰው-ነት' እንደምንለው ያለ ቃል ነው፤ አምላክ-ነት ማለት ነው። አምላክ የመሆን መገለጫ ማለት ነው።

ባሕርይ የውስጥ፥ የራስ፥ የግል፥ የማንነት መገለጫን አመልካች ቃል ነው። የሰው ባሕርይ ሰብአዊ ባሕርይ እንደሆነ ሁሉ፥ የእግዚአብሔር ባሕርይ የመለኮት ባሕርይ ነው። መለኮት የእግዚአብሔር ወይም እግዚአብሔራዊ ማለት ነው። ስለዚህ የመለኮት ባሕርይ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው። የመለኮት ባሕርይ የእግዚአብሔር ባሕርይ ከሆነ እግዚአብሔር ያልሆነ ሌላ ማንም ያ ባሕርይ ሊኖረው አይችልም ማለት ነው። እግዚአብሔራዊ ባሕርያት የምንላቸው ነገሮች የእግዚአብሔር የራሱ የብቻው የሆኑ የማንነቱ መገለጫዎች ናቸው።

እግዚአብሔር በአምሳሉ ሲፈጥረን፥ የሕይወትን እስትንፋስ እፍ ሲልብን፥ እርሱን የምንመስልባቸው፥ <u>የምንሆንባቸው ሳይሆን የምንመስልባቸው፥</u> እርሱ ያጋራን፥ ያካፈለን ባሕርያት አሉ። እኛ ባሕርያችንን፥ ወይም የፍጥረት ሥር መሠረታችንን ለሌላው የምናጋራው በውልደት ነው። እኔ ከአባቴ ወይም ልጄ ከእኔ ጋር የምንመሳሰልባቸውም የምንለያይባቸውም ነጥቦች አሉ። ይህ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ የመጣ የባሕርይ መዋረስ ወይም ተካፋይነት ነው። እኔና አባቴ ወይም እኔና ልጄ እንመሳሰላለን እንጂ አንድ አይደለንም። እኔና የሥጋ አባቴ እንመሳሰላለን እንጂ አንድ አይደለንም፤ ልንሆንም አንችልም። ስለ ባልና ሚስት አንድ ሥጋ መሆን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ያንን ሲልም እንኳ፥ በጋብቻ አንድነት የሚገኘውን ስሜታዊ፥

---

[13] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤ ገጽ 371።

አካላዊና ወሲባዊ አንድነትን መናገሩ እንጂ የባሕርይ መወራረስን ወይም ከሌላው ጋር መጋራትን አይደለም።

ኢየሱስ፥ 'እኔና አብ አንድ ነን' ሲል ግን እንመሳሰላለን ወይም አንዱ አንድ ባሕርይን ከሌላው ይወርሳል ወይም ይቀበላል ማለት ሳይሆን በእርግጥ፥ በትክክል፥ በፍጹም አንድ ነን ማለቱ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር አንድ ነው፤ ስለዚህ፥ አብና ወልድ ሁለትም ሆነው አንድ ናቸው። አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ፥ ሦስት አካላት ወይም ማንነቶች ሆነውም አንድ ናቸው። ያ መሆን ነው፤ መምሰል አይደለም። የኛ የባሕርይ ተካፋይነት ግን የመምሰል ነው። ስንፈጠርም በመምሰል ነው፤ በመልኩና በምሳሌው። የተጠራነውም ደግሞ ለመምሰል ነው፤ ልጁን ለመምሰል። ኢየሱስ፥ 'እኔና አብ አንድ ነን' ሲል አንድ ነው። እግዚአብሔር አንድ ስለሆነና እርሱ የሥላሴ አንድ አካል ስለሆነ። ኃይሉ ዮሐንስ፥ 'እኔና አብ አንድ ነን!' ሲል ግን የአሳች ስሕተት ነው። እርሱ የሥላሴ አካል አይደለምና እርሱና አብ፥ ኢየሱስ እና አብ አንድ በሆኑበት ልክም ሆነ መልክ አንድ አይደሉም።

እግዚአብሔር ከመለኮታዊ ባሕርይው ካጋራን፥ ካካፈለን፥ የተጋራናቸው፥ የተካፈልናቸው ባሕርያት አሉ ማለት ነው። አንዳንድ መለኮታዊ ባሕርያት ተሻጋሪ ወይም ተላላፊ ሲባሉ አንዳንዶች ደግሞ የራሱ የብቻው ባሕርያት ናቸው። ለምሳሌ፥ በሁሉ ቦታ መገኘት፥ ሁሉን ማወቅ፥ ሁሉን መቻል የእግዚአብሔር የብቻው የራሱ ብቻ ንጥር ማንነቱ፥ አንጡራ ሀብቱ የሆኑ መገለጫ ባሕርያት ናቸው። ሙሉ እውቀት ሳይሆን ከፊል እውቀት፥ በሁሉ ቦታ መገኘት ሳይሆን በአንድ ብቻ ቦታ መገኘት፥ ሁሉን መቻል ሳይሆን ትንሽ ችሎታ፥ ፍጹም ቅድስና፥ ፍጹም ፍቅር፥ ፍጹም ገዢነት ሳይሆን አንጻራዊና የተቀበልነው፥ የተሰጠን ቅድስና፥ ፍቅር፥ ሥልጣን እና የመሰሉት ደግሞ ያጋራን ባሕርያቱ ወይም በመልኩ በምሳሌው በመፈጠራችን በኛም ውስጥ የሚገኙ ባሕርያት ናቸው። እግዚአብሔር ያፈቅራል፤ አንተ ታፈቅራለህ፤ ትንሽ። እግዚአብሔር ያውቃል፤ አንተም ታውቃለህ፤ ሚጢጢ። እርሱ ቅዱስ ነው፤ አንተም ቅዱስ ነህ፤ ከእርሱ የተነካ። እርሱ ገዢ ነው፤ አንተም ገዢ ነህ፤ በትንሹ፤ በልኩ። ከራስህ የሆነ ቅድስና የለህም፤ የተሰጠህ እንጂ። ለምን? አምላክ ስላልሆንክ። ሰው ሰው እንጂ፥ የከበረ ሰው እንጂ፥ ግሩምና ድንቅ ፍጡር እንጂ፥ አምላክ አይደለም።

ሰው ምን ቢከብር፥ ሌላው ቀርቶ፥ አምላክ እርሱን ሊያድነው ሰው ቢሆንለትም እንኳ እርሱ የዳነ ወይም የሚድን ሰው እንጂ አምላክ አይሆንም። ሲፈጠርም ሥሪቱ አምላክ ሆኖ ወይም ሊሆን ሳይሆን ሰው ሆኖ ነው የተፈጠረው። ሞርመኖች እንደሚሉት ሰው አድጎ፥ ተመንድጎ፥ ሠልጥኖ፥ በቅቶ ወደ አምላክነት ማዕረግ ከፍ አይልም። 'እግዚአብሔር አንዴ እንደኛ ነበረ፤ እኛም አንድ ቀን እንደ እርሱ እንሆናለን' ይላሉ። አምላክነት ሰልጥነውት፥ ሕግጋት ጠብቀው፥ ሥርዓት ፈጽመው፥ የሚደርሱበት

እርከን፥ የሚበቁት ብቃት አይደለም። አምላክን አድገው አይሆኑትም። አምላክነት የአምላክ ብቻ ባሕርይ ነው።

ባሕርይ የአንድን ነገር ማንነት ወይም ምንነት ለይቶ የሚገልጥ የዚያ ነገር መታወቂያው ነው። አንድ ፍጥረት ወይም ፍጡር ከሌሎች ነገሮች ወይም ፍጥረታት ጋር የሚገናኝበት፥ የሚመሳሰልበት ነጥቦች ሊኖሩ ይችላሉ። ያ ማለት ታዲያ ያ ነገር ሌላውን ነው ማለት አይደለም። ሰው ነፍስ ወይም ሕይወት አለው፤ በግም፥ አሞራም ነፍስ ወይም ሕይወት አለው። ይህ ሕይወት ተመሳሳይ ተፈጥሯዊ ባሕርይ ነው። አንዳቸው ግን ሌላውን አይደሉም። ሰው በግ፥ ወይም በግ አሞራ አይደሉም። ሌላ ምሳሌ ብንወስድ፥ ሰው ቦታ ይይዛል፤ ግመልም፥ ድንጋይም፥ ወንዝም ቦታ ይይዛሉ። ቦታ መያዝ ተፈጥሯዊ ባሕርይ ነው። ግን አንዱ ሌላውን አይደለም። ሰው ወንዝ፥ ወይም ግመል ድንጋይ አይደሉም። ደግሞም ሁሉም የተሰጣቸው ቁሳዊ፥ አካላዊ የመሆናቸው ተፈጥሯዊ ባሕርይ ነው ያላቸው። አንዱ ሌላውን ግን አይደሉም። ሕያዋን የሆኑ ፍጥረታት የራሳቸውን ፍጥረታዊ ባሕርይ ለዘራቸው ያሳልፋሉ። ስለዚህ ልጅ የወላጆቹን የተፈጥሮ ባሕርይ ይዞ ይወለዳል። የተወለደውም ለቀጣዩ ትውልድ ተመሳሳይ ባሕርይን ያስተላልፋል።

ወደ መለኮታዊ ባሕርይ ስንመጣ ግን ይህ ተፈጥሯዊ ባሕርይ አይደለም። እግዚአብሔር የተፈጠረ ስላልሆነ የተፈጥሮ ባሕርይ የለውም። መለኮታዊ ባሕርያት የመለኮት ባሕርያት እንጂ የፍጥረት ባሕርያት ስላልሆኑ በውልደትም የሚተላለፉ ባሕርያት አይደሉም። እኔ የመለኮቱ ተካፋይ ስለሆንኩ ከኔ የሚወለደው ልጅ በእኔ ምክንያት የመለኮት ተካፋይ አይሆንም። ምክንያቱም መለኮት የተፈጥሮ ባሕርይ አይደለምና። እኛ የእግዚአብሔር ልጆች የምንሆነው ጌታን በመቀበል፥ ዳግም በመወለድ ግንኙነት ወይም ልጅ በመደረግ ነው እንጂ የሚተላለፍ፥ የሚወረስ ልደትን በመቀበልና ቀጥሎም ያንን እኛ ለሌሎች በማቀበልና በማቀባበል የምናስተላልፍ በመሆን አይደለም። ይህ ባሕርይ የሚለው የመጀመሪያው ቃል ነው። ባሕርይ የማንነት፥ የምንነት መገለጫ፥ መታወቂያ ነው። መለኮታዊ ባሕርይ አለ፤ ሰብአዊ ባሕርይ ደግሞ አለ። ሁለተኛው ቃል ተካፋይነት ነው።

## ሐ. ተካፋይ

በመጀመሪያ ማስተዋል ያለብን፥ 'ተካፋዮች ሆነናል' ነው እኮ ቃሉ የሚለው። ተካፋይ ከሆንክ ካለው ነገር ነው የምትካፈለው። ዋናው አለ፤ ከዚያ ነው ተሰጥቶህ

የምትካፈለው፥ የምትሳተፈው፥ የምትቋደሰው። ይህ ቃል፥ (አሳቾቹ ያው ከእንግሊዝኛ ተናጋሪዎች አይደል የሚስሙትና እንደ በቀቀን የሚደግሙልን?) እንግሊዝኛውንም ስናየው partaker ነው የሚለው። የዚህ partaker የተባለው የእንግሊዝኛው ቃል ትርጉም እንዲህ ይላል፤ Have some of the qualities or attributes of something. 'የአንድን ነገር ጥቂት ወይም የተወሰኑ ባሕርያት ወይም መገለጫዎች መያዝ፥ መቀበል' ነው ይለናል።

ወደ ምንጩ ቃል ደግሞ፥ ጴጥሮስ ወደጻፈበት እንሂድ። እዚህ ተካፋይ የሚለው ቃል አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ቋንቋ፥ ኮይኖኖስ የሚል ነው፤ κοινωνός። ቃሉ እንደ ስምም፥ እንደ ግሥም ይሆናል። እንደ ስም ሲወሰድ ባልንጀራ፥ ማኅበረተኛ ማለት ነው። እንደ ግሥ ደግሞ መካፈል ወይም ተካፋይ መሆን፥ ሱታፌ ማድረግ፥ ተሳታፊ መሆን፥ የሚለውን አሳብ ሲያሳየን፥ ካልለው የሚቀበል ወይም የሚካፈል ማለት ነው። ጥቂት ጥቅሶችን እንይ። በመጀመሪያ ጴጥሮስ ነው ይህን ቃል የጻፈውና ራሱ ጴጥሮስ በሌላ ቦታ ይህንን ቃል እንዴት እንደጠቀሰ እንይ፤

1ጴጥ. 5፥1 *እንግዲህ እኔ፥ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ የክርስቶስም መከራ ምስክር ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንሁ፥ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤* ይላል። ይህ እዚህ ተካፋይ የሚለው ቃል ነው ኮይኖኖስ። ሊገለጥ ያለ ታላቅ ክብር አለ፤ ያ ክብር የጴጥሮስ ክብር አይደለም፤ ወይም ጴጥሮስ ያንን ክብር በሙሉ የወሰደ አይደለም። ጴጥሮስም ያንን ክብር አይደለም፤ የዚያ ሊገለጥ ያለው ክብር ገላጭም አይደለም፤ ገላጩ ሌላ ነው። በዚያ ውስጥ ግን ድርሻ አለው። ተሳታፊ ወይም ተፋታች ነው። ተፋታች መፈተት ከሚለው ቃል የወጣ ነው፤ ተካፋይ ባለ ድርሻ ማለት ነው።

ጳውሎስ በ2ቆሮ. 1፥7 *ተስፋችንም ስለ እናንተ ጽኑ ነው፤ ሥቃያችንን እንደ ተካፈላችሁ እንዲሁም መጽናናታችንን ደግሞ እንድትካፈሉ እናውቃለንና።* ይላል። ሥቃዩ የነጳውሎስ ነው፤ ጠቅላላውን ምዕራፍ ማንበብ የበለጠ የስቃያቸውን ምንነት ያሳየናል። ግን በአካልም ባይሆኑ፥ በአካል የስቃዩ ተቀባዮች ባይሆኑም፥ በሩቅም ቢሆኑ የቆሮንቶስ ሰዎች በመንፈስ አብረውት ሆነው ተሳትፈዋል፤ አሁንም በመጽናናታቸው ተካፋዮች ሆነዋል። ተካፋዮች ሆነዋል፤ ከዋናው ተሳታፊዎች።

ማቴ. 23፥30 *በአባቶቻችን ዘመን ኖረን በሆነስ በነቢያት ደም ባልተባበርናቸውም ነበር ስለምትሉ፥ ወዮላችሁ።* ይላል። ተካፋይ የሚለው መተባበር የሚለው ቃል ነው። እዚህ ስለ መጥፎ ድርጊት እና ስላለመተባበር ነው የሚናገረው። ሆኖም፥ አድራጊዎቹ አሉ፤ ተባባሪዎቹ ደግሞ አሉ። ተባባሪዎቹ ከአድራጊዎቹ እኩል አይደሉም። ከክፍሉ እንደምናገኘው እንዲያውም በስፍራውና በጊዜውም ያልነበሩ ናቸው።

ጳውሎስ በሮሜ 11፥17 ያለውንም እንመልከት፤ *ነገር ግን ከቅርንጫፎች አንዳንዱ ቢሰበሩ አንተም የበረሀ ወይራ የሆንህ በመካከላቸው ገብተህ ከእነርሱ ጋር የወይራ ዘይት ከሚወጣው ሥር ተካፋይ ከሆንህ፥ በቅርንጫፎች ላይ አትመካ፤* ይላል። ቅርንጫፍ ሆነህ፥ ያውም፥ ከሌላ ቦታ መጥተህ ገብተህ፥ ከስሩ፥ ከግንዱ የሚመጣው ባሕርይ፥ የወይራው ዘይት ተካፋይ ከሆንክ አትመካ። ተካፋይ ነህ፤ የባሕርይው፥ የዘይቱ ተካፋይ ነህ፤ ተቀባይ ነህ። አንተ ስሩ ወይም ግንዱ አይደለህም። ስለዚህ ልትመካ አትችልም። አንድ ከሆንክማ ልትመካ ትችላለህ። አንድ ዓይነት ነሃ! አንድ ነሃ!

'እኔ የታላቅ ወንድሜ ዓይነት ነኝ' እንደሚሉት ማለት ትችላለህ። ታላቅ ወንድሜ የምትለው እርሱ ፈጣሪ ነው፤ አንተ ፈጣሪ አይደለህም፤ ስለዚህ ያካፈለህን ያህል ትመስለዋለህ እንጂ የታላቅ ወንድምህ ዓይነት አይደለህም። ተካፋይነት ይህ ነው። እርሱ አምላክ ሳለ በዓላማ ሰው ቢሆን፥ ሥጋን ወስዶና ሥጋን ይዞ ነው። በመለኮት ላይ ሥጋን ጨምሮ ነው። እኛ ግን በሥጋ ወይም በሰው-ነት ባሕርያችን ላይ መለኮትን መደረብ አንችልም። እርሱ እኛን ሆነ ማለት እኛ እርሱን ነን ማለት አይደለም።

በ2ጴጥ. 1፥1-4 ጴጥሮስ ስለ ምን እየተናገረ እንደሆነ ለመረዳት ያንን ክፍል ብቻ ሳይሆን ጠቅላላውን ምዕራፍ እና ጠቅላላውንም መጽሐፉን ማየት ይኖርብናል። በክፍለ ምንባቡ እንኳን የሚናገረው እርሱን በማወቅ እርሱን ለመምሰል፥ በኑሮ፥ በተለይም ከዓለም ምኞት እና ጥፋት አምልጠንና ርቀን በቅድስና እርሱን ለማሳየት የሚያስፈልገንን እንደሰጠን የሚናገር ነው። ባሕርይን አየን፤ ተካፋይነትን አየን፤ ሦስተኛው መለኮት ነው።

'ሰው መንፈስ ነው' ባዮች ሦስተኛው እና የመጨረሻ ሙግታቸው፥ 'ከመንፈስ ተወልጃለሁና መንፈስ ነኝ፤ ስለዚህም መንፈስ ከሆንኩ መለኮት ወይም ትንሽ እግዚአብሔር ነኝ' የሚለው ነው። ቀጥሎ ይህንን እናያለን።

## ከመንፈስ መወለድ መናፍስት ያደርገናል?

ባለፈው በክፍል ሁለት ከሬፍሎ ዳለር፥ *"ፈረሶች ሲገናኙ ምን ይወልዳሉ? ፈረሶች! ውሾች ሲገናኙ ምን ይወልዳሉ? ውሾች! ድመቶች ሲገናኙ ምን ይወልዳሉ? ድመቶች! እግዚአብሔር ደግሞ አንድ ላይ ሆኖ (ሥላሴን ማለቱ ነው) ሰውን እንፍጠር ሲሉ ምን*

*እየፈጠሩ ነው? እግዜሮች! እግዜሮች እየፈጠሩ ነው። እናንተ እግዜሮች ናችሁ ትንንሽ እግዜሮች (Little 'G')። እናንተ እግዜሮች ናችሁ ምክንያቱም እናንተ የመጣችሁት ከእግዚአብሔር ነው።"* ብሏል። ለነዚህ ሰዎች ከሰው መወለዳቸው ሰው መሆናቸው የመሆኑን ያህል ከእግዚአብሔር መወለድ እግዚአብሔርነት ነው። ኃይሉ ዮሐንስም፥ 'አምላክ ምንድነው ሚወልደው? አማልክትን ነው።' ብሏል። ከአገራችን ሌሎችም ይህንን ያሉ አሉ።

'ሰው መንፈስ ነው' የሚሉ ሰዎች ይህን ሲሉ ሰው አምላክ ነው ማለታቸው ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ *እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።* ዮሐ. 4፥24። እግዚአብሔር መንፈስ ከሆነ፥ እነሱ ከእግዚአብሔር ከተወለዱ፥ መንፈስ ናቸው። መንፈስ ከሆኑ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ነውና እነሱም መንፈስ፥ ስለዚህም እግዚአብሔር ናቸው። የሰው አምላክነት አመክንዮው ይህ ነው።

ሰው አምላክ ነው ሲሉ (በእነርሱ ቋንቋ ትንንሽ እግዜሮች (ወይም little g–god) ሲሆኑ፥ እንደ ኢየሱስ ሳይሆን ከዚያም በላይ መሆናቸው ነው። ከኢየሱስ በላይ፥ ማለትም፥ ንጥር አምላክ መሆናቸውን መናገራቸው ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ ሙሉ አምላክ ሳለ ሙሉ ሰው ነው። ሙሉ ሰው። እነዚህ ሰውነታቸውን የካዱና መንፈስ የሆኑ ከሆኑ፥ መንፈስ ሲሉ ደግሞ አምላክ ከሆኑ፥ ሰውነት የሌለበት አምላክ መሆናቸው ነው። ከኢየሱስም በላይ የመሆን ሙከራ ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ ሰውና አምላክ ነው፤ ወይም ሰው የሆነ አምላክ ነው። እነዚህ ሰው ካልሆኑ ሰው ያልሆኑ አማልክት ናቸው ማለት ነው። ንጥር አምላክ ናቸው፤ ወይም አምላክ ብቻ ናቸውና፥ ስለዚህ ከኢየሱስም በላይ ናቸው ማለት ነው።

ይህ በእውነቱ፥ እነ ኃይሉ ዮሐንስ ወይም ኮፐላንድ፥ እነ ሄግን ወይም ኬንየን አምጠው የወለዱት አፍ እላፊ ስሕተት ሳይሆን ሰይጣን በዔድን ገነት ለሔዋን ያቀበላት መርዝ ነው። ገዳይ መርዝ። ዘፍ. 3ን አንብቡት። ዘፍ. 3፥5 ላይ ያለው፥ እንደ እግዚአብሔርም እንድትሆኑ መልካምንና ክፉን የምታውቁ የሚለው፤ (በዕብራይስጡ አጣጣል እንደዚያ ነው፤ *וִהְיִיתֶם כֵּאלֹהִים יֹדְעֵי טוֹב וָרָע׃* ዊህዪይቴም ኬእሎሂይም ዮድዔይ ቶውብ ዋራዕ።) ይህ የስሕተት ትምህርት የሰውን ዘር ዕድሜ ያህል አሮጌ ስሕተት ነው። ምንጩም ሰይጣን ነው። እነ ኃይሉ ዮሐንስ ወይም ኬነት ኮፐላንድ ይህንን የሰይጣን ትውከት ካቀረቡልን ከየት እንዳመጡት ለምን ይጠፉናል?

ከእግዚአብሔር መወለዳችን እግዚአብሔር የማያደርገን ከእግዚአብሔር የተወለድነው ከሥጋ እንደምንወለደው ስላልሆነ ነው። ከሥጋ አቤል ወይም ቃየን ከአዳም እና ከሔዋን እንደተወለዱት፥ ወይም እኔ ከወላጆቼ ከመንግሥቱና ከአልማዝ

እንደተወለድኩት፥ ወይም አንተና አንቺ ከአባታችሁና ከእናታችሁ እንደተወለዳችሁት ያለ የሁለቶች መጣመር መወለድ አይደለም። ከመንፈስ መወለድ፥ በዝርዝር እንደምናየው ልጅ መደረግ ነው። ልጅ ተደርጎ መወሰድ ነው። ከመንፈስ የተወለደ ማለት ልጅ የተደረገ ማለት ነው። ሲደረግ ሆኗል፤ ከመሆኑ በፊት ግን ተደርጓል። ይህ አይጥፋን።

በገላ. 3፥7 እንኪያስ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም ልጆች እንደ ሆኑ እወቁ። ይላል። ከእምነት የሆኑት ማለት እንደ አብርሃም የሚያምኑቱ ወይም አብርሃም እንዳመነው ዓይነት እምነት የሚያምኑት ማለት ነው፤ በሚያጸድቅ እምነት የሚያምኑ የአብርሃም ልጆች ናቸው። ስለዚህ የአብርሃም ልጆች ነን? ናችሁ ነው የሚለው ጳውሎ የገላትያን ሰዎች፤ እና እኛንም ጭምር። ግን ከአብርሃም ተወልደናል? በሥጋ አልተወለድንም። በእምነቱ ስለመሰልነው ልጆቹ ነን።

እዚያው ገላ. 4፥1-7ን ተመልከቱ የተያያዘ ክፍል ስለሆነ፤ ግን ቁጥር 4-5ን ብቻ ብናይ፤ *ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ፥ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ።* ይላል። የኛ የልጅነታችን መልክ ይህ ነው። ቃሉ υἱοθεσία ዊዮቴሲያ ልጅ መደረግ፥ ልጅ ተደርጎ መወሰድ ማለት ነው። ልጁ የተላከው፥ በሥጋ የመጣው እኛ ልጆች ተደርገን እንድንወሰድ ነው። በሕጉም በባሕሉም ከሄድን የጉዲፈቻ ልጅ ከልጅ ቅንጣትም የማይተናነስ ልጅ የተደረገ ልጅ ነው። ግን በሥርዓቱ ይወለዳል። በሌላ ባህል ብንሄድ፥ የጡት ልጅ ጣት ይጠባና የጡት ልጅ ይሆናል። የክርስትና ልጅ፥ አበ ልጅ የሚባልም ልጅነት አለ። በአይሁድ መካን ሴት ከባሪያዋ የሚወለድ ሕጻን የሷ እንዲሆን ጭኗ ላይ ይወለዳል። በየባሕሉ እንዲህ ያለ ነገር አለ። እስከ ዘመናችንም የዘለቀ ባህል ነው።

'ከመንፈስ መወለድ' የሚባለው ሐረግ፥ 'ሰው መንፈስ ነው ወይም ሰው ትንሽ አምላክ ነው' የሚሉ ሰዎች የሚጠቅሱት ሌላው መደበኛ መሟገቻ ነው። ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው የሚለው አሳብም ቀደም ሲል ካየነው መለኮታዊ ባሕርይን ከመካፈል ጋር የተቆራኘ አሳብ አለው። ቀድሞ ያልነበርነው ነና አሁን የሆንነው። ጴጥሮስ በ1ጴጥ. 2፥10 እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ፤ ይላል። ወገን ያልሆንነው፥ ቤተ ሰብ ያልሆንነው፥ በተጻፈበት ቋንቋ ቃሉ ሕዝብ ነው የሚለው፤ እና ሕዝብ ያልነበርነው ነን ሕዝብ የሆንነው። እንዴት? ወገን በመደረግ። ልጅ ስንደረግ፥ ልብ እንበል፤ የሚያደርገን ነው የሚያደርገን እንጂ፥ እኛ ሄደን፥ 'ከዛሬ ጀምሮ የዚህ ቤተ ሰብ አባል ነኝ' አንልም። ቢሆን ኖሮ ብዙ የቤተ ሰብ ልውውጥና በየጊዜውና በየሰበቡም መለዋወጥ ይደረግ ነበር።

'ሰው መንፈስ ነው' የሚሉ ሰዎች፥ 'ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስ የተወለደ ደግሞ መንፈስ ነው። አይልም ወይ? ስለዚህ ሰው መንፈስ አይደለም እንዴት ይባላል? ነው እንጂ፥ ቃሉ ስለሚል፤' ይላሉ። ከመጀመሪያ ጀምሮ እንዳየነው፥ ሰው ሲፈጠርም፥ ሥሪቱም፥ አፈጣጠሩም መንፈስ ሳይሆን ሰው ነው። ይህንን ለአፍታም ቢሆን አንርሳ።

ወደሚጠቅሱት ወደ ዋናው ጥቅስ ስንሻገር፥ በዮሐ. 3፥6 ቃሉ የሚለው፥ 'ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው።' የሚለው የሚጋጭ ይመስላል። እዚህ ላይ ቆም በማለት፥ 'ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ በሥጋ ውስጥ ያድራል' የሚሉትን ሰዎች ሁለት ግልጽ ጥያቄ መጠየቅ አለብን?

አንደኛው፥ ከሥጋ የተወለደው ምን? ምኑ ነው ሥጋ? ከመንፈስ የተወለደው ምን? ያ የሚወለደው ወይም የተወለደው ምንድን ነው? መልሱ ግልጽ ነው፤ ሰው ነው። ሰውየው በመጀመሪያ ሰውየው መሆኑን መቀበልን ይጠይቃል። 'እኮ ሰውየው ነው መንፈስ ነው የሚለው እኮ!' ሊሉ ይችላሉ። ሰውየው ሰው መሆኑን ከተቀበልን መንፈስነት ይሻራል። ሰውየውን፥ 'ሰው' ያልን ጊዜ መንፈስነት ይሰረዛል። ካላሉ ደግሞ ምንድርን ነው ያ ነገር ታዲያ የሚለውን መመለስ ይጠበቅባቸዋል።

ሁለተኛው ጥያቄ፥ ሰው መንፈስ ነው ሲሉ፥ ሰው ሁሉ ነው መንፈስ? ወይስ 'የተወሰኑት መናፍስት ናቸው፤ የተወሰኑት ግን ሰዎች ናቸው፤' ነው የሚሉት? እነዚህ ሰዎች መነሻቸውና መሪ ጥቅሳቸው፥ 'ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው' የሚለው ከሆነ (እንመለከተዋለን ይህን ጥቅስ)፥ ሰው መንፈስ ነው ማለት አይችሉም። 'ክርስቲያን መንፈስ ነው' በሚለው ለመለወጥ ይገደዳሉ። ግን እነዚህ አሳቾች አንድም ቀን፥ 'ክርስቲያን መንፈስ ነው' ሲሉ ተደምጠው አያውቁም። ሁሌም የሚሉት፥ 'ሰው መንፈስ ነው' ነው። ሲሉም ሰውን ሁሉ ማለታቸው መሆኑ ገሃድ ነው። የሚናገሩት ስለ ሰው መንፈስነት ከሆነ ደግሞ፥ ሲጀምርም ዮሐ. 3፥6ን መጥቀስ አይችሉም። ራሳቸውን እየተቃረኑ ስለሆኑ። ይህ ጥቅስ ዳግም ስለመወለድ ስለሚናገር ስለተወሰኑት እንጂ ስለ ሰው ሁሉ አይናገርም። 'ሰው መንፈስ ነው' ሲሉ፥ 'ክርስቲያን መንፈስ ነው' ማለታቸው ከሆነም ቃሉን፥ ጥቅሱን በዐውዱ መፍታትና ማየት እንችላለን። ሰው መንፈስ ነው፤ ወይም ሰው እግዚአብሔር ነው ማለቱ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በሥፍራው ማየት እንችላለን።

ዮሐ. 3፥6 ያንን ይላል? ማለት፥ ሰው መንፈስ መሆኑን ይናገራል? አይናገርም። ጌታ እዚያ የሚናገረው ስለ ዳግም ልደት ስለሆነ ዳግም በመወለድ የእግዚአብሔር ልጅ ስለመሆን ነው። ይህ ቃል የተነገረው ለኒቆዲሞስ ነው። የጥቅሱን አሳብ ለማግኘት ዮሐ. 3፥6ን አሳቾች ሁሌም ጥቅስ ቦጭቀው እንደሚያነብቡት ነጥለን ሳይሆን ክፍለ ምንባቡን ወይም ጠቅላላውን ምዕራፍ በሙሉ ማየት ተገቢ ነው። ኒቆዲሞስ ማን

ነው? 1፥ *ከፈሪሳውያንም ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፤ እርሱም በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ፦* ይላል። የአይሁድ አለቃ ነው፤ ደግሞ ፈሪሳዊ ነው። የጠራ አይሁዳዊ ነው ማለት ነው። በዚያ ላይ ሰው መሆኑን እንዳንረሳ፤ 'ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ' ነው የተባለው። ኒቆዲሞስ የዘር ብቻ ሳይሆን የሃይማኖት ጉዳይን በተመለከተም አንዳች ጥያቄ የሌለበት አይሁዳዊ ነው። ፈሪሳውያን ማለት አይሁድ ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ የተጀመረ የአይሁድ ሃይማኖታዊ ማኅበር ሆኖ የወግ ቅድስናና የሕግ አጠባበቅ ላይ ያተኮረ ቡድን ነው። አለቅነቱ ሕዝባዊና ማኅበራዊ መታወቂያው ሲሆን ፈሪሳዊነቱ ደግሞ ሃይማኖታዊ መታወቂያው ነው።

ደግሞም፥ መንፈሳዊ መረዳትን ያገኘ ወይም ማወቅን ያወቀ ሰውም ነው። 2፥ *መምህር ሆይ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ <u>እናውቃለን</u> አለው።* ያለው ይህንን ማወቅ ያሳያል። ማወቁ ግን ኢየሱስ መምህር ሆኖ ከእግዚአብሔር ዘንድ መምጣቱን ነው። በቃ ይኸው ነው። በኒቆዲሞስ እይታ ኢየሱስ ከቀደሙት ነቢያት ጋር እኩያ ብቻ እንጂ ሌላ አይደለም። ኢየሱስ ግን መምህር ብቻ ሳይሆን መሢሕ እና በሥጋ የመጣ አምላክ ነው። ስለዚህ እውቀቱ ጎዶሎ ነው።

ይኸኔ ነው፥ 3፥ *ኢየሱስም መልሶ፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው።* ያለው። ቁም ነገሩ ያለው እዚህ ዳግመኛ መወለድ ላይ ነው። ዳግመኛ መወለድ ኋላ፥ 'ከመንፈስ መወለድ' በማለት የገለጠው ነው። ከመንፈስ መወለድ እና ዳግመኛ መወለድ አንድ ናቸው። ይህ ዳግመኛ መወለድ ለኒቆዲሞስ አልገባውም። ስለዚህ ጠየቀ፤ 4፥ *ኒቆዲሞስም፦ ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? አለው።* አለ። መወለድን የተረዳው በሥጋ እንደመወለድ ነው። መጀመሪያ በሥጋ እንደተወለደው ሁለተኛም ደግሞ በሥጋ እንደ መወለድ ነው የተረዳው። ለዚህ ነው ወደ ማኅጸን ገብቶ ከመወለድ ጋር ያቆራኘው። ምንም እንኳ ፈሪሳዊና የአይሁድ አለቃ ቢሆንም፥ ኒቆዲሞስ ዳግም መወለድ የሚባል ነገር፥ ወይም በዚያ መልኩ የተለመደ ትምህርት ስላልኖረ፥ ዳግም መወለድን አያውቀውም። ስለዚህ ኢየሱስ አብራራለት፤ 5፥ *ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።* አለው። ከመንፈስ መወለድ ያለው በቁጥር 3 *ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ* ያለው ነው። እዚያ ዳግመኛ መወለድ የሚለው እና ቁጥር 5 ላይ፥ *ከመንፈስ ካልተወለደ* የሚለው ሁለቱም ወደ እግዚአብሔር

*መንግሥት መግቢያ መንገዶች* ናቸው። *ዳግመኛ መወለድ* እና *ከመንፈስ መወለድ* የተባለው ነው ቁጥር 6 ላይ፥ *ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው።* የሚለው የተነገረው። ከውኃ መወለድን አንዳንዶች ከውኃ ጥምቀት፥ አንዳንዶች ከቃሉ የማንጻት ሥራ ጋር ያቆራኙታል። ምናልባት የሚያነጻው ቃሉ ሥራ ሳይሆን አይቀርም።

አይሁድ በመጀመሪያ ልደታቸው (በሥጋ የአብርሃም ልጆች በመሆናቸው) እጅግ የሚኩራሩ ሰዎች ናቸው። በትውፊታቸው እንዲያውም የአብርሃም ልጆች ስለሆኑ ብቻ መንግሥተ ሰማያት እንደሚገቡ የተረጋገጠ በመሆኑ አብርሃም አባታቸው በሲኦል ደጅ ሆኖ አንድም አይሁዳዊ በስሕተት ወደ ሲኦል እንዳይሄድ ይጠብቃል ይላሉ።[14] አንዳንድ ትውፊት የተረት ታላቅ ወንድም ነው። አብርሃም ሲኦል ደጅ ቆሞ አይሁድ የሆነና ያልሆነን የሚመረምር መሆኑ ለአይሁድ ኩራት ትልቅ የስነ ልቡና እረፍት ሊሰጥ ይችል ይሆናል፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ግን አይደለም። በቃሉ ውስጥ ይህንን ነገር ከሩቅ እንኳ የሚመስል ነገር የለም። የአብርሃም እቅፍ (ሉቃ. 16፥ 23) የተባለው ከዚህ ሊቆራኝ ይችል ይሆናል፤ ግን ያ ስፍራን እንጂ የአብርሃምን ሚና የሚያሳይ አይደለም። ለአይሁድ የመጀመሪያ ልደታቸው ኩራት ወይም የማን ልጆች የመሆናቸው ጉዳይ እጥግ የደረሰ ነው። ዮሐ. 8፥33-40 'የአብርሃም ዘር ነን . . . አባታችንስ አብርሃም ነው . . .' የሚሉት ይህንን ያስረዳናል።

በዚህ በዮሐ. 8 ክፍል ቁጥር 41 ላይ፥ *እናንተ የአባታችሁን ሥራ ታደርጋላችሁ* ሲላቸው፥ *እኛስ ከዝሙት አልተወለድንም አንድ አባት አለን እርሱም እግዚአብሔር ነው አሉት።* በሚለው የእግዚአብሔር ልጅነት እና የኢጋንንት ልጅነት በተግባራዊ መልኩ ተነጻጽረዋል። ቁጥር 44 ላይ ይህንን ሲያደምቀው፥ *እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና።* አለ። ልጅነት ከዚህ እንደምንረዳው የአባትን ፈቃድ ወይም ምኞት ማድረግ ነው። *እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ።* ሲል ልጅ የአባቱን ፈቃድ ይፈጽማል፤ ያም የልጅነት መታወቂያ ነው ማለት ነው። ልጅነት በተግባር ነው የሚታየው።

ጌታ ለኒቆዲሞስ በሥጋ መወለዱና የአብርሃም ልጅ መሆኑ ሳይሆን፥ *ዳግመኛ መወለዱ*፥ ከውኃና ከመንፈስ መወለዱ ብቻ ወደ እግዚአብሔር *መንግሥት መግቢያው* እንደሆነ ነው የነገረው። *ከመንፈስ መወለድ ዳግመኛ መወለድ* ነው።

---

[14] David Guzik's *Commentary on the whole Bible*; electronic version.

ስለዚህ ሰው ሁሉ መንፈስ አለመሆኑን ራሱ ይህ፥ 'ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው' የሚለው ቃልም ይመሰክራል። ከላይ እንዳልኩት፥ 'ሰው መንፈስ ነው' ከማለት ይልቅ፥ 'ክርስቲያን መንፈስ ነው' ቢሉ ከዚህ ጥቅስ ጋር የሚቀራረቡ ሊሆኑ ይችላሉ።

'ሰው መንፈስ ነው' የሚሉ ሰዎች 'መንፈስ የሆነው ሰው' ወይም 'ሰው መንፈስ ነው' ሲሉ፥ ሰው ሁሉ ነው መንፈስ? ወይስ የተወሰኑት መናፍስት ናቸው የተወሰኑት ግን ሰዎች ናቸው ነው የሚሉት? የሚለው ጥያቄ በግልጽ ሊመልሱት የተገባ ነው ብዬ ነበር። ይህንን ግልጽ አያደርጉትም። ሆን ብለው ያድበሰብሱታል። ለምን ቢባል፥ 'ሰው መንፈስ ነው' ሲሉ ሰውን ሁሉ ከሆነ ከዚህ እንደ ባንዲራ ከፍ አድርገው ከሚያነሡት ጥቅስ ከዮሐ. 3፥6 ጋር ይጋጭባቸዋል። ምክንያቱም ይህኛው ከመንፈስ ስለተወለዱት ብቻ ነው የሚናገረው። ከመንፈስ ያልተወለዱ ከሥጋ የተወለዱ በመሆናቸውና ይህ ደግሞ በግልጽ ስለተነገረ ሥጋ ናቸው እንጂ መንፈስ ሊሆኑ አይችሉም። እንደነሱ ትምህርት ደግሞ አዳም መንፈስ ነው። አዳም መንፈስ ከሆነ ከአዳም በኋላ ያሉት ሰዎች ሁሉ፥ የአዳም ልጆች ናቸውና፥ ሁሉም መናፍስት መሆናቸው ነው። እንግዲህ ከሁለት አንዱን ሊቀበሉ ግድ ይሆናል። የሰው መንፈስነት ሁሉን አቃፊ ነው ወይም መናፍስት የሚሆኑት ከመንፈስ የተወለዱት ብቻ ናቸው።

መልሳቸው ከሁለት አንዱን ነው የሚሆነው። ወይም መንፈስነት ለሁሉም የሰው ልጅ ነው ይላሉ፤ ወይም ዳግም የተወለዱት ብቻ ናቸው ከሰውነት ወደ መንፈስነት የሚያልፉት ይላሉ። ከመንፈስ የተወለዱት ብቻ ከሆኑ ደግሞ፥ 'ሰው መንፈስ ነው' ማለት አይችሉም። ዳግም ያልተወለደ መንፈስ ሊሆን ስለማይችል። በሁለቱም ከሄድን ስሕተት ናቸው። እነዚህ፥ 'ሰው መንፈስ ነው፤ እኛም መናፍስት ነን' ብለው የሚያስተምሩት ሰዎች ሁሉ፥ የዳኑም፥ ያልዳኑም መንፈስ እንደሆኑ ነው የሚናገሩት። ከሆነ ያልዳኑትም በእግዚአብሔር መደብ መሆናቸውን ይቀበላሉ ማለት ነው። ከሆኑ ለነዚህ ሰዎች ስለ ድነት፥ ስለ ወንጌልን መንገር ተገቢነት አይኖረውም። ሁሉ ይድናሉ ብሎ ወደማስተማር ወይም ዩኒቨርሳሊስት የሚሆኑት ከዚህ የተነሣም ነው። አንዳንዶቹ በግልጽ ዩኒቨርሳሊስት መሆናቸውን ሳይደብቁ ተናግረዋል።

መናፍስት የሚሆኑት የዳኑት ብቻ ከሆኑ፥ ያልዳኑት ሰዎች መንፈስ ሲሆኑ ከመዳናቸው በፊት የነበሩትን ከሥጋ የተወለዱበትን ሥጋ-ነት ወይም ሰው-ነት ወይም ሰው መሆን ምን ያደርጉታል? የዳኑት ሰዎች መንፈስ የሆኑት ልክ ሲድኑ ነው ማለት ነው? ከዳኑ በኋላስ? ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ተብሏልና፥ ከሥጋ መወለዳቸው ይሰረዛል? ተሰረዘ? ሥጋ መሆናቸው ቀርቶ መንፈስ ብቻ ሆኑ? ከሆኑ ሥጋ የለም? ሥጋዊነትስ የለም? ከሥጋ የተወለደ ሰው ከመንፈስ ሲወለድ ከሥጋ መወለዱ ይቀራል? ወይስ በሥጋ የተወለደ ሰው ሰው ሆኖ ሳለ ነው ከመንፈስ የሚወለደው?

ኒቆዲሞስን ራሱ ብንወስደው፥ ኒቆዲሞስ ከጌታ ጋር ሲነጋገር ሥጋ ነው ወይስ መንፈስ ነው? ሰው መሆኑ ገሃድ ነው። ሰው ስለሆነ መንፈስ ነው? ወይስ አይደለም? ኒቆዲሞስ ከሥጋ ተወልዶአል ወይስ አልተወለደም? ተወልዶአል፤ ስለዚህ ሥጋ ነው። ከዮሐ 7 እና 19 እንደምንረዳው የጌታ ተከታይ ሆኖአልና ይህንን ዳግመኛ መወለድን እንደተወለደ ይታያል። የጌታ ተከታይ ሆኖአልና፥ ዳግም ተወልዷልና፥ መንፈስ ሆኗል ማለት ነው፤ ከሥጋ የተወለደው ሰውነቱ ምን ሆነ? እነዚህ ሁሉ እዚህ የጠየቅኳቸው ጥያቄዎች፥ 'ሰው ትንሽ እግዜር ነው፤ ምክንያቱም ሰው መንፈስ ነው፤' የሚሉ ሰዎች ሊመልሷቸው የተገባቸው ጥያቄዎች ናቸው።

እንግዲህ ምንድን ነው ከመንፈስ መወለድ? ከመንፈስ መወለድ፥ ዳግመኛ መወለድ ወይም ከውኃና ከመንፈስ መወለድ ነው። ይህም ከእግዚአብሔር በመወለድ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ነው። ዳግም ልደት በሥጋ የመጀመሪያ ልደት ከሥጋ እንዳገኘን ከእግዚአብሔር በመወለድ የምናገኘው ሁለተኛ ልደት ነው። በሥጋ የወላጆቻችን ወይም የአዳም ልጆች እንደሆንን፥ ከእግዚአብሔር ስንወለድ ልጆቹ ሆነናል፤ ይህ ጌታን በመቀበል ቅጽበት የሆነ ነው፤ ያኔ የልጅነት ሥልጣን እናገኛለን። ከእርሱ ተወልደናልና ልጆቹ እንሆናለን። *የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።* ዮሐ. 1፥11-13።

ጌታን ስለተቀበልነው ልጆች ሆነናል። ልጆች ሆነናል ሲባል ከሰውነት ወደ መለኮትነት ተላልፈናል፤ ተሻግረናል ማለት አይደለም። በዚህ በተወለድንበት መንፈስ እንመርራለን፤ ይህ የልጅነት መንፈስ በውስጣችን በመኖሩም እግዚአብሔርን አባ አባት ብለን መጥራት እንችላለን፤ ምስክሩም በውስጣችን አለ፤ *በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና። አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል።* ሮሜ 8፥14-16።

## ከመንፈስ መወለድ ዳግም ልደት እና መንፈሳዊነት ነው

ይህ ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ መሆን ታዲያ ምንድርን ነው? ከመንፈስ መወለድ መንፈስ ነው ሲል መንፈሳዊ ማንነትን ያላብሰናል፤ የእግዚአብሔር ልጆች ያደርገናል፤

በመንፈስ እንድንመላለስ ያደርገናል፤ ቃሉ ለኒቆዲሞስ እንደተነገረው ደግሞ፥ ከአብርሃም ልጅነት፥ ከሥጋ ልጅነት ወደ እግዚአብሔር ልጅነት፥ ወደ መንፈሳዊ ልጅነት ያሻግረናል ማለቱ ነው። ስለ ልጅነትና ስለ መንፈሳዊነት መናገሩ ነው። ዮሐ. 3፥6 ላይ ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው የሚለው፥ እዚህ ከእግዚአብሔር የተወለዱ ከሥጋና ከደም አልተወለዱም ከሚለው አሳብ ጋር አንድ ነው። የተቀበሉት የእግዚአብሔር ልጆች ይሆናሉ። ለምን? ዮሐ. 1፥13 እንደሚለው *ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ፤* ከእግዚአብሔር ተወለዱ ማለት እግዚአብሔር ሆኑ ማለት አይደለም። የእግዚአብሔር ልጆች ሆኑ እንጂ! ልክ እንደዚሁ፥ ከመንፈስ ተወለዱ ማለትም መንፈስ ሆኑ ማለት አይደለም፤ የመንፈስ ልጆች ሆኑ፤ የመንፈስ ቅዱስ ልጆች፥ የእግዚአብሔር ልጆች፥ በመንፈስ የሚመርሩ፥ መንፈሳውያን፥ እግዚአብሔራውያን ሆኑ ማለት ነው።

ይህን ዳግም መወለድ በሌሎች ቦታዎችም እናገኛለን። 1ጴጥ. 1፥3-4 *ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፥ እድፈትም ለሌለበት፥ ለማያልፍም ርስት እንደ ምሕረቱ ብዛት ሁለተኛ* <u>*የወለደን*</u> *የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤ ይህም ርስት በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል።* ይላል። እዚያው 1ጴጥ. 1፥23 *ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።* ይላል። ያዕ. 1፥18 *ለፍጥረቱ የበኩራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ ወለደን።* ይላል። ይህም መወለድ ዳግም መወለድን የሚናገር ነው። ቲቶ 3፥5 ደግሞ አዲስ ልደት ይለዋል፤ *እንደ ምሕረቱ መጠን* <u>*ለአዲስ ልደት*</u> *በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፥ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም፤* ይላል። ይህ ሁሉ የሚያሳየን ዳግም መወለድን፥ መንፈሳዊ መወለድን ነው። መንፈሳዊ መወለድ መንፈሳውያን ያደርገናል እንጂ መንፈስ አያደርገንም።

ጳውሎስ በሮሜ. 8፥5-6 እንደጻፈው ነው፤ *እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና፥ እንደ መንፈስ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ። ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው።* መንፈሳዊነት ለመንፈስ ቅዱስ ፈቃድን ማስገዛት ነው።

መንፈሳዊነት በመንፈስ ቅዱስ መመራት ነው። ሮሜ 8፥14 *በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።* ከላይ ዮሐ፣ 3፥6 እና 1፥11-13ን እንዳየነው፥ ከእግዚአብሔር የተወለዱ ናቸው። ከዚህ የጳውሎስ ቃል እነማን ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች? የእግዚአብሔር ልጆች በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመርሩ ናቸው። እኛ ልጆች የሆንን፥ የልጅነት መንፈስ ያለን ነን እንጂ መንፈሶች አይደለንም።

እኛ እግዚአብሔርን አባ፥ አባት የምንጠራ ነን እንጂ የእግዚአብሔር ክላስ ወይም መደብ የሆንን እግዜሮች አይደለንም።

መንፈሳዊነት በመንፈስ መሆን ወይም በሥጋ አለመሆን ነው። እዚያው ሮሜ 8፥9 *እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም።* በመንፈስ መሆን የእርሱ ወገን መሆን ነው። ወገንነት ነው፤ ልጅነት ነው። *የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም* አለ እንጂ መንፈስ እንጂ ሥጋ አይደለችሁም አላለም። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችን መንፈስ አያደርገንም፤ መንፈሳውያን ግን ያደርገናል። 'በመንፈስ ናችሁ እንጂ' እንደተባለ፥ በመንፈስ እንድንሆን ያደርገናል።

መምሰልና መሆንን አምታትቶ ማቅረብ ማሳት ነው። ጳውሎስ እኔን ምሰሉ ሲል አካላዊ መምሰልን አይደለም። መሆንን አይደለም። የቅድስና፥ ዋጋ የመክፈል፥ የመሰጠት፥ የመቆረስ፥ የዝቅታ፥ አመላለስን፥ በፊል. 2፥ 5 *በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን።* ያለውን፥ አሳብ ነው። መምሰል መሆን አይደለም።

ይህ ማንነታችን ነው ክርስቶስን ሊመስል የተወሰነው፤ *ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ <u>እንዲመስሉ</u> አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና፤* ሮሜ 8፥29። ይህ እርሱን የምንመስልበት ዳግም የተወለደ ማንነታችን ነው። ሰዎች እኛን ሲያዩ የእርሱ ነጸብራቆች መሆናችን ይስተዋላል? እዚህ መምሰል የተባለው ቃል እዚህና ፊል. 3፥21 ብቻ ይገኛል። በፊልጵስዩስ የተጻፈው፥ *እርሱም ሁሉን እንኳ ለራሱ ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሠራር፥ ክቡር ሥጋውን <u>እንዲመስል</u> የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል።* የሚል ነው። መምሰል መሆን አይደለም።

ዮሐንስ፥ *ወዳጆች ሆይ፥ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፥ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን።* ፲ዮሐ. 3፥2። ይህንን የ፲ዮሐ. 3፥2 ጥቅስ ኃይሉ ዮሐንስ ሲተረጉም፥ 'በግሪክ No future surprise ነው የሚለው፤ ብሏል። No - future - surprise እንግሊዝኛ መስሎኝ! ፲ዮሐ. 3፥2 በግሪክ ይኸው። ያንን አይልም።

Ἀγαπητοί, νῦν τέκνα Θεοῦ ἐσμεν, καὶ οὔπω ἐφανερώθη τί ἐσόμεθα· οἴδαμεν δὲ ὅτι ἐὰν φανερωθῇ, ὅμοιοι αὐτῷ ἐσόμεθα, ὅτι ὀψόμεθα αὐτὸν καθώς ἐστι.

በግሪክ፥ No - future - surprise *ያለውን ኃይሉ* ዮሐንስ ከነኮፐላንድ የተማረውን የአሜሪካ southern accent ከሆነ እየቆየ ሲመጣ ልዩነቱን ማወቅ እየተሳነው መጥቷል ማለት ነው። ካልሆነ ደግሞ፥ ወይ የሚናገራቸውን ሰዎች ይንቃቸዋል ማለት ነው፤ ወይም ይህንን ቃልም ከመጠን በላይ ይንቀዋል ማለት ነው። ቃሉን የሚሰሙትን ሰዎቹንም፥ ሰዎቹ የሚሰሙትን ቃልም ይንቃል። ይህ ደግሞ ደግ አይደለም። ኮፐላንድ ሲናገርም እንዲህ ያለ ጥሬ ቀልድ ቀልዷል፤ 'እግዚአብሔርም፥ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር አለ፤ ብሎ፥ (እንደ ውሻ፥ ውፍ! ውፍ! ውፍ! ውፍ! ብሎ) አላለም እንደዚያ!' ብሎ ነበር። ቃሉ ለነዚህ ሰዎች መቀለጃ ነው። በቃሉ እያፌዙ ቃሉን እናስተምራለን ሲሉ ማፌሪያ መሆን ነው።

ሰዎች ሆነን በመልኩና በምሳሌው መፈጠራችን ከቀድሞም ጀምሮ እኮ የተነገረን ነገር ነው። ያልሆንነው አምላክነትን ነው። ስንፈጠር በምስሉ ነው የተፈጠርነው፤ እንመስለዋለን። ውድቀት ያጠለሸው፥ ያበላሸው ምስል አለ። ተበላሽቶም ግን ምስል ነው። እንመስለዋለንም፥ እንድንመስለው የተወሰነውንም እንሆናለን። ዳግም ስንወለድ መንፈስ ቅዱስ ወደ ውስጣችን መጥቶ በቲቶ 3፥5 እንደተጻፈው፥ *እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፥* እንደተባለው፤ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን የሚያድሰው ይህ አዲስ ልደትን ያገኘ ማንነት አለ።

በመንፈስ መወለድ አዲስነት እና በአዲስ ኑሮ መመላለስ ነው። ቆላ. 3፥9-10 የአሮጌውን ሰው መገፈፍ እና የአዲሱን ሰው መለበስ ይናገራል፤ *እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፥ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና፥ የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል፤* ይላል፤ የተገፈፈ ማንነት አለ። የተለበሰ ማንነት አለ። አሮጌው ሰው ክርስቶስን ከማወቃችን፥ የእግዚአብሔር ልጆች ከመሆናችን በፊት ያለው ማንነታችን ነው። አሮጌውን ሰው በተመለከተ ጳውሎስ በሌሎች ቦታዎችም ተናግሯል፤ ሮሜ 6፥6 ላይ፥ *ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን፤ የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቋልና።* ይላል። አስቀድሞ የሆነ ነገርን ነው የሚናገረው፤ የኃላፊ ጊዜ ግስ ነው። ኤፌ. 4፥22 ላይ ደግሞ፥ *ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፥* ይላል። ይህ ደግሞ የአሁን ጊዜ ነው። ተገፍፏል፤ ተሰቅሏል፤ ገና ደግሞ ይወገዳል። አዲሱ ሰው ደግሞ ተለብሷል፤ ይለበሳልም። ቆላ. 3፥9-10 ባነበብንበት ለብሳችሁታል ይላል። የኃላፊ ጊዜ ነው። ኤፌ. 4፥24 ላይ ደግሞ፥ *ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ።* ይላል። የአሁን ጊዜ ነው።

ይህ አዲሱ ሰው የሚባለው፥ ወይም አዲስ ፍጥረት የሚባለው በክርስቶስ ስንሆን የምንሆነው ማንነት ነው። 2ቆሮ. 5፥17 ያንን ነው የሚለን፤ *ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።* ጳውሎስ በቆላስይስ የሚነግረን ይህ አዲስ ሰው አዲስ ብቻ ሳይሆን የሚታደስም መሆኑን ነው የሚነግረን። የሚታደሰውም እርሱን ለመምሰል እውቀትን ለማግኘት ነው። እውቀት ማግኘት እርሱን ከመምሰላችንና ከእርሱ ጋር ግንኙነት ከማድረጊያ መሠረታውያን ንጥረ ነገሮች አንዱ ነው። እርሱን መምሰላችን እንግዲህ ዳግም በመወለድ ሰው ሲፈጠር የታለመለትን የቅድስና፥ የግንኙነት፥ የኅብረት፥ ማንነት መቀዳጀት ነው። ከሥጋነት ወደ ምንፍስና መሻገር (ይህ ከቶውኑም የማይሆን ነገር ነው፤ የተፈጠርንበት ሥሪት ስላልሆነ) ምንፍስና ሳይሆን፥ ሳይሆን በዚህ ሥጋ ሳለን የምንለማመደው እርሱን መምሰል ነው። የእርሱ ምሳሌ መሆናችን ያም ነው።

ምስል ወይም ምሳሌ መሆንና መምሰል ይቀራረባሉ እንጂ አንድ አይደሉም። ምስል የፍጥረታችን ኹነት ነው። መምሰል ደግሞ ሂደት ነው። አሁን እና እዚህ እንድንመስል የተነገረን ቃል አለን። ገና አልመሰልነውም፤ ወይም መስለነው አላለቅንም፤ በመምሰል ሂደት ላይ ነን። ወደፊት እንመስለዋለን። *እርሱን እንድንመስል እናውቃለን።* ያም አስቀድሞ የታቀደልን መምሰል፥ የተበላሸው መምሰል፥ ፍጹም ሲሆን ነው። ዮሐንስ ስለ ወደ ፊቱ ነው እየተናገረ ያለው። ወደ ፊት በትንሣኤ አካል ስንሆን የተነሣውን እርሱን እንመስላለን። ያኔም ሰው-ነታችን ወይም ሰው መሆናችን ይቀጥላል እንጂ፥ ያም አምላክ አያደርገንም። ግን መንፈሳዊ አካል ለብሰን እንነሣለን። ክርስቶስ ከሞት ሲነሣ እንደለበሰው ያለውን የማንገፈፈውን፥ በውርደት ተዘርቶ በክብር የሚነሣውን አካል እንለብሳለን። ድንኳኑ ከብዶን የምንቃትተው ለዚህ ነው። መምሰል እንግዲህ ይህ ነው። ከመንፈስ መወለድም መንፈሳዊነት እንጂ መንፈስነት አለመሆኑን፥ ዳግም በመወለድ እንደ ልጆች መመላለስ፥ እንደ ሥጋ ፈቃድ ሳይሆን እንደ መንፈስ ፈቃድ መመላለስ መሆኑን ነው ያየነው።

ሰው ጠያቂ ፍጡር ነው፤ ይጠይቃል። መሠረታዊ ጥያቄዎችን ይጠይቃል፤

- 'ከየት መጣሁ? ምንጬ ምንድር ነው?' ይላል። የምንጭ ጥያቄ ነው፤ የመሠረት።
- 'እኔ ማን ነኝ?' ወይም፥ 'እኔ ምንድር ነኝ?' ሕይወት ምንድር ነው? ይላል። የማንነትና የምንነት፥ የትርጉም ጥያቄ ነው።
- 'እዚህ ለምን አለሁ? የመኖር ምክንያቴ፥ ዓላማዬ፥ ግቤ፥ ምንድር ነው? ማን ፈጠረኝ? ከፈጣሪዬ ጋርስ ምን አለኝ? መልካምና ክፉ የሚባል ነገር አለ?' ይላል፤ የዓላማ ጥያቄ ነው።

- ‘ፍጻሜዬስ? ስሞት ሕይወት ይህችው ብቻ ናት ወይስ ከዚያ በኋላ ቀጣይ ናት? ቀጣይ ከሆነች የት? እንዴት?’ ይላል። የመድረሻ አድራሻ ጥያቄ ነው።




አሁን እዚህ እየተመለከትን ያለነው ሁለተኛው፥ ‘እኔ ማን ነኝ?’ ወይም፥ ‘እኔ ምንድር ነኝ?’ የሚለው ነው። እነዚህን የአራት ጥያቄዎች አሳብ ያገኘሁት ከራቪ ዛካሪያስ አንድ ትምህርት ነው። ራቪ እነዚህን ነጥቦች በአራት ቃላት ያስቀምጣቸዋል፤ Origin, Meaning, Morality, Destiny ይላቸዋል።

እና ሰው ጠያቂ ነው። እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጡራን እንደዚህ የሚጠይቅ ሌላ ፍጡር የለም። ምናልባት መላእክት ይጠይቁ ይሆን? አላውቅም። ግን እንደ ሰው፥ እኔ ማን ነኝ? ብሎ የሚጠይቅ ሌላ ፍጡር በምድር ላይ የለም። ሰው ምንድር ነው? የሚለው ከነዚህ መሠረታዊ የሆኑ አራት ጥያቄዎች አንዱ ነው።

ይህንን ጉዳይ ወይም፥ ‘ሰው ምንድር ነው?’ የሚለውን ጥያቄ እዚህ እየተመለከትን ያለነው፥ ‘ሰው መንፈስ ነው’ ወይም፥ ‘ሰው ትንሽ እግዜር ነው’ ለሚለው የስሕተት ትምህርት መልስ ለመስጠት ቢሆንም ይህንን ትምህርት ስንጨርስ ጠቅለል ያለ ግንዛቤ እንዲኖረን ነው ይህንን አሳብ ያመጣሁት። ማንነታችንን ማወቅ ልካችንን እንድናውቅ፥ ከልካችን እንዳናልፍም፥ እንዳናንስም ያደርገናል።

ትክክለኛውን የሰውን ማንነት ማወቅ አለ ቅጥ ተለጥጠን ያልሆንነውን እንዳንሆን ያደርገናል። አለማወቅ ደግሞ ያስተናል። አምላክ ሳንሆን አምላክ ነን እንድንል ያደርገናል። ወይም በተቃራኒው ከሆንነው በታች ተጨራምተን ራሳችንን እንድንጥል

ያደርገናል፤ እኔ ትል እንድንል ያደርገናል። በፍልስፍና ረገድ ከሄድን፥ ለምሳሌ፥ አገራችን ለብዙ ዓመታት የተጫነባት ማርክሳዊ ፍልስፍና ነበረ። እንደዚህ ፍልስፍና ትምህርት ሰው የዝግመታዊ ለውጥ (ወይም ኢቮልዩሽን) ውጤት የሆነ የባዮሎጂያዊ አጋጣሚዎችና የዕድሎች ግኝትና ምርት ብቻ ነው። እንዲህ ከሆነ ለሰው ያለን ግምት የወረደ ነው። ይህ ከሆነ በሰዎች ላይ የሚደረጉ ነገሮች ሁሉ፥ ውርጃ በሉት፥ የዘር ማጽዳት በሉት፥ ጀነቲክ ምህንድስና በሉት፥ የምሕረት ግድያ - ዩተኔዥያ- (euthanasia ወይም mercy killing ይሉታል) በሉት፥ ሌሎችም እንደ ሰው እይታ ብቻ የሚታዩ ቀላልና አማራጭ ነገሮች ናቸው። አንድ ሰው ሌላውን ሰው ቢገድል፥ ወይም አንድ ጎሳ ሌላውን ቢያጸዳ እንደ ትልቅ ነገር አይቆጠርም። ሰው ከእንስሳ መደብ ነዋ!

እነዚህ ሰውን ከእንስሳ መደብ ያደርጉታል፤ እነዚያ እስካሁን ስናያቸው የነበሩት ደግሞ ከእግዚአብሔር መደብ ወይም class ያደርጉታል። ማንነታችንን ካላወቅን ሌሎች የሚሉንን ሆነን ለመገኘትና የሚሰጡንን መታወቂያ ለማሳየት በጣም ቀላል ነው። ነህ የሚሉህን፥ ነሽ የሚሉሽን ትሆናላችሁ፤ እንሆናለን። መንፈስ ነህ ሲሉን መንፈስ ነን ካልን፥ አምላክ ነህ ሲሉን አይደለሁም አንልም። እንስሳ ሲሉን ነን፤ ትል ነህ ሲሉንም እንቢ አንልም። ሰይጣን ነህ ሲሉንም አይከብደንም። ኢየሱስ ሰየጠነ የሚሉት እኮ እኛ ሰይጣኖች ስለሆንን ነው ነው የሚሉት። ሰውን ለማዳን ሰው እንደሆነው፥ ሰይጣንን ለማዳን ሰይጣን መሆን አለበት ነው ትምህርታቸው። ሰውየው የትኛው፥ ሰይጣንየው የትኛው መሆኑን ለመንገር አይሞክሩም እንጂ!

አስጠንቃቂ የመሆኑ ተገቢነት እዚህ ላይ ነው። እውነተኛ ማንነታችንን ወይም ስንፈጠርም፥ ስንኖርም፥ ስንሞትም ሰዎች መሆናችንን ካልተገነዘብን ሌሎች ስለኛ በሚሰጡት ትርጉም ውስጥ ማንነታችንን እናጣውና ለመፈለግ እንባዝናለን። ከዚያም የሚያቀብሉንን ለመቀበል እንገደዳለን። ስለዚህ የሆንነውን ሳንሆን፥ ያልሆንነውንና ልንሆን ያልተገባንን፥ ወይም ልንሆን የማንችለውን ልንሆን በመሞከር ክቡር ዘመን ያልፍብናል። የኪሳራ ዘመን። ያልሆንነውን ላንሆን፥ የሆንነውንም ሳንሆን በፎርፌ ተሸንፈን ከዚህች ምድር እናልፋለን።

ሰይጣን ስለመሆን ካነሳን ይህንን ልጨምር፤ የቃል-እምነት አስተማሪዎች ሰውን ሲፈልጉ ያመለኩታሉ፤ ሲፈልጉ ያሰየጥናሉ። ኢየሱስ ሰየጠነ የሚሉት ሰው ሰየጠነ ስለሚሉ ነው። የመጀመሪያው ሰው አዳም ስለሰየጠነበት ሁኔታ፥ ኮፐላንድ ሲናገር፥ "When Adam committed high treason [sinned] against God and bowed his knee to Satan, spiritual death - the nature of Satan - was lodged in his heart." ትርጉም፤ አዳም በእግዚአብሔር ላይ ከፍተኛውን ክህደት በፈጸመና ለሰይጣን ጉልበቱን ባንበረከከበት ጊዜ መንፈሳዊ ሞት፥ ማለትም፥ ሰይጣናዊ ባሕርይ

በልቡ ውስጥ ተተከለ። ብሎአል።[15] ሰው በወደቀ ጊዜ የሰይጣንን ባሕርይ ተካፈለ፤ ማለት፥ ሰይጣን ሆነ ይላሉ። ኮፐላንድ የአዳምን ከእግዚአብሔር መለየት ወይም መንፈሳዊ ሞት የሰይጣን ባሕርይን መካፈል ብሎ ሰይሞታል፤ God was not referring to physical death. He meant that Adam would die spiritually—that he would take on the nature of Satan which is spiritual death. ትርጉም፤ "[እግዚአብሔር ለአዳም ስለ ሞት በሚናገርበት ጊዜ] ስለ ሥጋዊ ሞት መናገሩ አልነበረም። አዳም መንፈሳዊ ሞትን እንደሚሞት መናገሩ ነበር። ያም መንፈሳዊ ሞት የሰይጣንን ባሕርይ መውሰድ ነው።"[16] ብሏል። ሰው ብቻ ሳይሆን የሰየጠነው፥ ኢየሱስም የሰየጠነ ሰውን ለማዳን ሲል ሰየጠነ ይሉናል።

ቃለ እምነቶች በሰው በኩል ምድርን ሊገዛ አስቦ የነበረው እግዚአብሔርም ምድርን የሚገዛበትን ሕጋዊ መጫሚያ የሆነውን ሰውን በማጣቱ ከስሮ ቀረ ይሉናል። እንደነዚህ ሰዎች ትምህርት እግዚአብሔር በዚህች ምድር ላይ ባለቤትነት የለውም፤ በምድር ላይ መጫሚያ ለማግኘት እና ምንም ነገር ለማድረግ የኛን ፈቃድ ማግኘት እንዳለበት ይነግሩናል። ምድርና ሞላዋ የእርሱ ናት ማለትም ስሕተት ነው፤ ሁሉን የሚገዛ ብሎ ስለ እግዚአብሔር መናገርም፥ መዘመርም አይቻልም፤ ምድርን አይገዛማ! እነዚህ ሰዎች ሰውን (አዳምን) ብቻ ሳይሆን ኢየሱስንም አሰይጥነዋል። ይህንን የቀደመ ሙብቱን እንደገና እንዲቀዳጅ ኢየሱስ ወደ ሲዖል ወርዶ፥ የሰይጣንን ባሕርይ ተካፍሎ፥ ጋኔኖች አጎሳቁለውት፥ ከዚያ ዳግም ተወልዶ ከሞት ተነሣ ይሉናል። መሳትና ማሳት በየፈርጁ ማለት እንዲህ ነው!

## ሰው አምሳለ አምላክ፥ መልክዓ አምላክ ነው።

ሰው ሰው ተደርጎ የተፈጠረ ፍጡር ነው። *እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤* ዘፍ. 1፥26። እግዚአብሔር ሰውን ወይም አዳምን በመልኩ ፈጠረ። ሰው የሚለው ቃል አዳም የሚለው ቃል ነው፤ አዳም ማለት ሰው ማለትም አፈር ማለትም ነው። አዳም ሰውነቱ፥ ማንነቱ ነው። አፈር ሥሪቱ ነው። በመልኩ መፈጠሩ ሕያውነቱና ፈጣሪውን በሚመስልባቸው ረገዶች እርሱን የሚመስል ማንነቱ ነው። አዳምን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር። በዕብራይስጥ፥

---

[15] *Copeland, K. Our Covenant with God, Harrison House, Tulsa OK. 1976. p. 9.*
[16] *እላይ የተጠቀሰው ገጽ 10።*

*וַיֹּאמֶר אֱלֹהִים נַעֲשֶׂה אָדָם בְּצַלְמֵנוּ כִּדְמוּתֵנוּ* (ዋዮእሜር ኤሎሂይም ናዓሤህ አዳም ብጻልሜኑ ኪ ድሙውቴኑ) እግዚአብሔርም አለ፤ እንፍጠር [እንሥራ] ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን። 'እንፍጠር' የሚለው ቃል እንሥራ ማለት መሆኑን እና ሰው የሚለው ቃል እና አዳም የሚለው ቃልና ስም ተመሳሳይ መሆናቸውን ልብ እንበል። ሰው የተፈጠረው፥ (ሰው ነው የተፈጠረው፤ መንፈስ አይደለም፤) ሌሎቹ በተፈጠሩበት የአፈጣጠር መልክ አይደለም። ለሰው የተነገረው ቃል ለፍጥረት ከተነገረው የተለየ ነው። በዘፍ. 1 ፈጠረ የሚለው ቃል ባራእ ነው፤ እዚህ ግን ናዓሤህ አለ፤ እንሥራ። ሰው ልዩ ፍጡር ስለሆነ። መፈጠርም ሆኖ በመደረግ ወይም በመሠራት ነው የተፈጠረው። ሰው በእግዚአብሔር የተፈጠረ፥ የተሠራ ፍጡር ነው። ሰው ሆኖ፥ ሰው ተደርጎ የተሠራ ፍጡር ነው።

ሰው ምንድር ነው? ሰው አምሳለ አምላክ፥ መልክዓ አምላክ ነው፤ እናም ክቡር ፍጡር ነው። ሰውን ስለ አለመግደል መጽሐፍ ቅዱስ ዋና ምክንያት አድርጎ የሚጠቅሰው ጉዳይ መልክዓነት፥ አምሳልነት ነው፤ *የሰውን ደም የሚያፈስስ ሁሉ ደሙ ይፈስሳል፤ ሰውን በእግዚአብሔር መልክ ፈጥሮታልና፤* ዘፍ. 9፥6።

ሰው መከበር እንጂ መገደል የሌለበት መልክዓ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው። መልኩና ምሳሌው መለኮት አለበት ወይ? ብለን ብንጠይቅ ምንም መለኮትነት የሌለበት ቃል ሆኖ እናገኘዋለን። መልክና ምሳሌ ለሰው ከእግዚአብሔር የተሰጠው እግዚአብሔርን ማንጸባረቅ የሚችል መንፈሳዊ ማንነትን መቀዳጀት ነው። ደሙ እንዳይፈስስ ከተባለ፥ እንዳይገደል፥ እንዳይሞት ከተባለ አምላክ አይደለም ማለት ነው፤ አምላክ ደም የለውም፤ መንፈስ ነው። ኢየሱስ ደም የኖረው ሰው ስለሆነ ነው። ሰው የሆነውም ደም እንዲኖረው ነው፤ የማስተስረያ ደም። የሞተውም ሰው ስለሆነ ነው። ስለዚህ፥ መልክዓነት መንፈስነትም፥ አምላክነትም አይደለም።

ይህ *በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤* በሚለው ውስጥ ያለው መልክና ምስል የሚሉት ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሌሎች ብዙ ቦታዎች የአካል ምስልን፥ መልክን፥ ጥላን፥ ቅርጽን፥ ወዘተ እንጂ ያንን ምሳሌና ጥላ የሆነውን ነገር ወይም አካል የሚያሳይ አይደለም። ሲጀመር የእግዚአብሔር ዓይነት፥ የእግዚአብሔር 'ክላስ'፥ የእግዚአብሔር መደብ ብሎ ነገር የለም። ለእግዚአብሔር ምድብ ለመሥራት፥ እግዚአብሔርን 'ዓይነት' ብሎ ለመመደብ እንዴት ተደፈረ? የሚቻለን ቢሆንና በእጃችን ጠፍጥፈን ልክ እኛን የሚመስል ነገር ብንሠራ ያ ነገር የኛ ሥሪት እንጂ እኛን አይደለም። የኛ ክላስም አይደለም። የእግዚአብሔር ሰውን መፍጠር እኛ ጠፍጥፈን ከምንሠራው የተለየ መሆኑ ግልጽ ነው። የሕይወትን እስትንፋስ በሰው እፍ ማለቱ ሰውን ሕያው ነፍስ ወይም ሕያው የሆነና ሕይወት ያለው ሰው አደረገው እንጂ

አምላክ ጨርሶ አላደረገውም። በጊዜ ሂደት ብዛትም ያ ፍጡር ከሰውነት ወደ አምላክነት አያድግም። ባለፉት ትምህርቶች እንዳየነው ሞርመኖች እንደሚሉት እግዚአብሔር አድገውት የሚሆኑት ማንነት አይደለም።

## ሰው በስዕላዊ ሞዴል ሲታይ

ሰው አካላዊ እና መንፈሳዊ (ወይም ቁሳዊ እና ኢቁሳዊ) ፍጡር ነው። መንፈሳዊውን ማንነቱን ነፍስ ወይም ነፍስና መንፈስ ብለው የሚከፍሉ አሉ። ወይም በደፈናው ሁለቱንም በአንድ ወስደው አካላዊና አካላዊ ያልሆነው ማንነቱ፥ ወይም ቁሳዊና መንፈሳዊ ማንነቱ፥ ወይም ግዝፍ እና ረቂቅ ብለው የሚወስዱም አሉ። የተለያዩ ሞዴሎች አሉ ለማስረዳት የምንጠቀምባቸው።




ሞዴል አንድ፤ ሰው (ቁሳዊና ኢቁሳዊ) *ሥጋ*ና ነፍፈስ የሚያሰኝ ነው። ነፍፈስ ነፍስና *መንፈስ* አንድ ላይ ማለት ነው። ይህ ሰውን ሁለትዮሽ አድርጎ የሚያቀርበው ሞዴል ነው። አካላዊው ማንነቱ *ሥጋ* ሲባል ረቂቁ ወይም ቁሳዊ ያልሆነው ማንነቱ ደግሞ በጥቅሉ ነፍስና *መንፈስ* ወይም ነፍፈስ ይባላል።




ሞዴል ሁለት፤ ሰው ሦስት ነው፤ ሦስትዮሽ ነው። ሰው *ሥጋ*፥ ነፍስ፥ *መንፈስ* ነው፤ እኛ ድንበር አበጀንላቸው እንጂ ድንበራቸውን በውል አናውቅም፤ ግን አንዱ ከሌላው *ጋር* የተገናኙ ናቸው።




ሞዴል ሦስት፤ ሰው *ሥጋ*፥ ነፍስ፥ *መንፈስ* ሆኖ አንዱ በሌላው ውስጥ ይገኛል፤ የሚል ነው። *መንፈስ* ከነፍስ *ጋር* ይነካካል፤ ነፍስም ከ*ሥጋ* *ጋር* ይነካካል፤ *ሥጋ* ደግሞ ከውጪያዊው ዓለም *ጋር* ይነካካል። ይህ የእርስ በርስና ከሌላው *ጋር* ያለው መስተጋብር ነው።

ሞዴል አራት፤ ሰው ሥጋ፥ ነፍስ፥ መንፈስ ሆኖ ነፍስና መንፈስ የተቆራኙና አንዱ ሌላውን የሚጋራ የሰው ክፍሎች ናቸው። ሁለቱም ከሥጋ ጋርም ግንኙነት ቢኖራቸውም እርስ በርሳቸው የሚገናኙበት፥ አንዱ ከሌላው የሚጋራው ማንነትም ያለበት ናቸው።




ሞዴል አምስት፤ ሰው ሥጋም መንፈስም ነፍስም ሆኖ ነፍስ የሥጋና የመንፈስ ቅይጥ ናት ከሁለቱ ከአንዱ ትወግናለች የሚል ነው። የአእምሮና የእውቀት፥ የስሜቶችና የፈቃድ ስፍራ በመሆን የሰውን ሁለንተና በአንድ ወይ በሌላ አቅጣጫ እንዲጓዝ አቅጣጫ አስያዥ ናት።




ሞዴል ስድስት፤ ሰው ሥጋ፥ ነፍስ፥ መንፈስ ሆኖ እነዚህ ሦስቱ የየራሳቸውም፥ አንዱ ከሌላው ወይም ከሁለቱም ጋር የሚጋራቸው ክፍሎች ያሉት ማንነት ነው የሚል ነው። አንዳቸው ከአንዳቸው ብቻ ሳይሆን ከሁለቱም፥ ሁለቱ እርስ በርስም ከአንዱ ጋርም መስተጋብራዊ ግንኙነት አላቸው።




በሁሉም ሞዴሎች ወይም ከሁሉም በአንዱ በጣም እርግጠኛ ሆነን ይህ ነው ማለት አንችልም። ቆርጠን በየብልት መትረን ማሳየት የምንችለው ሥጋን ብቻ ነው። ሥጋዊነትንም ከሥጋ ውስጥ አውጥተን ማሳየት አንችልም። ይህ ልብ ነው፤ ይህ ሳንባ ነው ብለን በልተን እንደምናሳየው ይህ ነፍስ ነው፤ ነፍስ ውስጥ እነዚህ ነገሮች አሉ፤ ይህ መንፈስ ነው፤ መንፈስ ደግሞ በነዚህ ነገሮች የተያዘ ነው ማለት አንችልም።

አንጎልን ከፍቶ ማየት ይቻላል፤ እዚያ ውስጥ ያለውን አሳብ ማየት ግን አይቻልም። 'ይህ ልብ ነው' ማለት እንደሚቻል፥ 'ይህ ልቡና ነው' ማለት አይቻልም። የሚታይ ማንነት እንዳለን ሁሉ የማይታይ ማንነትም አለን። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን፥ በየትኛውም ሞዴል፥ ሰው መንፈስ ነው ማለት አንችልም። ሰው መንፈስ አይደለም። ሰው የሁለቱም፥ የሚታየውም፥ የማይታየውም ማንነቱ አንድነት ነው። 'ሰው መንፈስ ነው፤ ሰው እግዜር ነው' የሚሉ አሳቾች ከነዚህ ሞዴሎች የትኛውንም ተጠቅመው ሰው መንፈስ ነው የሚለውን ማስረዳት አይችሉም። ምናልባት የራሳቸው የተለየ ሞዴል ሳይኖራቸው አይቀርም።

መጽሐፍ ቅዱስ ሰውን በሁለትዮሽም፥ በሦስትዮሽም ያቀርበዋል። አካላዊው ማንነቱ የሚታየው የሚዳሰሰው ግዝፍ ማንነቱ አካሉ ሲሆን ረቂቁ ወይም በሥጋ ዓይን የማይታየው ማንነቱ ደግሞ ነፍስ ወይም መንፈስ ወይም ነፍስ እና መንፈስ ነው። እነዚህን ሁለቱን አያይዘውም ለያይተውም የሚያቀርቡ አሉ። ለያይተው፥ ነጣጥለው የሚወስዱት በተለይ 1ተሰ. 5፥23 እና ዕብ. 4፥12ን ይጠቅሳሉ። *ሥጋ* (σῶμα)፥ ነፍስ (ψυχή) እና *መንፈስ* (πνεῦμα) ናቸው። በነዚህ ጥቅሶች እነዚህ ሁለቱም ለየብቻቸው ተጠቅሰዋል። በሌላ ስፍራ ግን ሰውን በጥቅሉ *ሥጋ*ና ነፍስነቱን ወይም ግዝፍ እና ረቂቅ ማንነቱን ከሁለቱ አንዱ ቃል ብቻ ሲወክልም ይታያል። ለምሳሌ፥ ማቴ. 10፥28 *ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ።* ይላል። ሰውን ነፍስና *ሥጋ* ይለዋል። በማቴ. 16፥26 *ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?* ይላል። ሰውና ነፍስ ይለዋል። ማቴ. 27፥50 *ኢየሱስም ሁለተኛ በታላቅ ድምፅ ጮኾ ነፍሱን ተወ።* ይላል። እዚህ የኋለኛው ጥቅስ ላይ ነፍሱን የሚለው *መንፈስ* (πνεῦμα) የሚለው የግሪክ ቃል ነው።

ሰው ሰው ነው። በዚህ ሰው በተባለ አካል ውስጥ *ሥጋ*፥ ነፍስ፥ *መንፈስ* ይገኛሉ። ነፍስና *መንፈስ* የማይታየው፥ ረቂቁ ማንነታችን ነው። *ሥጋ* የሚታየው ፍጥረታዊ አካላችን፥ ግዝፍ ማንነታችን ነው። ስንሞት ረቂቁ ማንነታችን ኅልውናው ይቀጥላል። በትንሣኤ ቀን ይህ የሞተው አካል (*ሥጋ*) የማይሞት፥ የበሰበሰው የማይበሰብስ ሆኖ ይነሣል። መንፈሳዊ አካል ሆነንም ለዘላለም እንኖራለን። 1ቆሮ. 15፥44 *ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፥ መንፈሳዊ አካል ይነሣል። ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ።* ይላል። የትንሣኤ አካል አካል ነው፤ መንፈሳዊ አካል። ያ መንፈሳዊ አካልም ሰው ነው የሚባለው።

## ሰው ሁለንተናው ነፍስ ወይም መንፈስ ሲባል ምን ማለት ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ ሰውን በሕያውነቱ ወይም በሕያው ማንነቱ ሲገልጠው ነፍስ እያለ ያቀረበባቸው በርካታ ስፍራዎች አሉ። ሰው ነፍስ ተሰኝቷል። ሰው መንፈስ ነው የሚሉ ሰዎች፥ 'ሰው ነፍስ አለው' ሳይሆን፥ 'ሰው ነፍስ ነው' ቢሉ ይህ እውነት ሊሆን ይችላል። ይህንን ለምን አይሉም? ቃሉ ይልቅስ ያንን ነው የሚለው። 1ቆሮ. 15፥45 እንዲሁ ደግሞ፡- ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፎአል፤ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ። ይላል። ዘፍ. 2፥7ም በዕብራይስጡ በቀጥታ ያንን ነው የሚለው። (:וַיְהִי הָאָדָם לְנֶפֶשׁ חַיָּה ዋይሂይ ሃአዳም ልኔፌሽ ኻያህ)። እንደዚህ ቃል አካሄድ ከሄድን ሰው ሕያው ነፍስ ሆነ ስለተባለ ሰው ነፍስ ነው ማለት ይቻላል። አባባሉ ነፍስ ያለው ሰው ወይም ሕያው የሆነ ሰው ማለት ቢሆንም። ሰው ነፍስ እየተባለ ብዙ ተጽፏል። ነገር ግን፥ ነፍስ ሲልም ሕያውነትን መግለጡ እንጂ ሰው ያንን ብቻ ነው ማለት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን ማንነት ለመግለጥ የተጠቀመባቸውን ቃላት እየሰነጠርን ሰውን ለያይተን የስሕተት መታወቂያ ፈጥረን መስጠት የለብንም። ሰው ሰው ነው፤ ሥጋም፥ ነፍስም፥ መንፈስም በዚህ ሰው በተባለ ክቡር አካል ይገኛሉ። ሰው ግን ሲጀመርም ሲጨረስም ሰው ነው።

ነፍስና መንፈስ በመጽሐፍ ቅዱስ የውስጡን ማንነታችንን የሚያሳየው ገላጭ ቃል ነው። አንዳንድ ቦታ ለያይቶ ያስቀምጣቸዋል፤ ሌላ ቦታ አንዱን ብቻውን እንደ ኢቁሳዊው ማንነታችን ገላጭ አድርጎ ያሳያል። ለምሳሌ፥

ዮሐ. 10፥11 *መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል።* ይላል።

1ዮሐ. 3፥16 *እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል።*

ያዕ. 2፥26 *ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።* ይላል። ይህ በአማርኛ ነፍስ ይባል እንጂ በመጀመሪያው (በግሪክ) ቃሉ መንፈስ ነው።

ሐዋ. 20፥10 *ጳውሎስም ወርዶ በላዩ ወደቀ፥ አቅፎም፡- ነፍሱ አለችበትና አትንጫጩ አላቸው።*

የነፍስን ምንነት ማየት፥ 'ሰው መንፈስ ነው' ባዮችን ስሕተት ይበልጥ ይገልጠዋል። ነፍስ ምንድርን ነው? ነፍስ በዕብራይስጥ שֶׁפֶנ ኔፌሽ፤ እና በ፤ገ ሩዋኽ፤ በግሪክ

ψυχή ፕሱኬ በሚሉ ቃላት ተወክለዋል። ነፍስ በቀላሉ እንደ ብልት በልተን ይኸው ይህ ነው የምንለው ነገር ባለመሆኑ 'ሰው መንፈስ ነው' ባዮች በቀላሉ መራቀቂያና ማሳቻ አድርገውታል። ራሳቸው አወሳስበው የውስብስባቸው ፈቺዎች አድርገውም ራሳቸውን ሾመዋል። ነፍስ ስሜት፥ ፈቃድና እውቀት ብቻ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ነፍስ ሕይወትን ይወክላል፤ ይህ የማይታየው ረቂቅ ማንነታችንና ሕያዋን ሆነን በአካለ ሥጋ እንድንመላለስ የሚያደርገን እስትንፋስ ነው። ነፍስ እስትንፋስ ወይም ሕይወት ያለበት ፍጡርን ያሳያል። ፍጡርን ሕያው ያደረገው የፍጡር የማይታየው ረቂቅ ማንነት ነው። ሰው ሲሞት፥ እስትንፋሱ ስትወጣ (በዕብራይስጥ עַוָּג ጋዋዕ) ነፍሱን ሰጠ ወይም ነፍሱ ጠፋ ይባላል፤ ከዚህ ሕያው ካደረገው ረቂቅ ማንነትም ይለያል፤ ሥጋውም በድን ይሆናል፤ ለምሳሌ፥ ዘፍ. 2፥7፥19፤ 9፥4-16፤ ዘዳ. 19፥21፤ 27፥25፤ ኢያ. 10፥40፤ ወዘተ።

በብሉይ ኪዳን ነፍስ ይህን የሕያውነት መግለጫ ብቻ ሳይሆን ሙሉ የሆነውን ሰውም ይወክላል። ሰው ጠቅላላ ማንነቱ ነፍስ እየተባለም ተጠርቷል። መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ጠቅላላውን ሰውን ነፍስ ይለዋል። ነፍስ ሲለው ግን አካል የሌለው፥ ሥጋ ያልሆነ ነፍስ ማለቱ ሳይሆን ሕያው ሰውን ሊገልጥ የተጠቀመበት አገላለጥ ነው። ለምሳሌ፥

ዘጸ. 1፥5 *ከያዕቆብ ጕልበት የወጡት ሰዎች ሁሉ ሰባ ነፍሶች ነበሩ፤ ዮሴፍም አስቀድሞ በግብፅ ነበረ።* እነዚህ ነፍሶች የተባሉት ሰዎች ናቸው እንጂ ሥጋና መንፈስ የሌላቸው ነፍሶች አይደሉም።

ዘፍ. 46፥15፥18፥22፥25 *ልያ በመስጴጦምያ በሶርያ ለያዕቆብ የወለደቻቸው ልጆችና ሴቲቱ ልጅዋ ዲና እነዚህ ናቸው፤ ወንዶችም ሴቶችም ልጆችዋ ሁሉ ሠላሳ ሦስት ነፍስ ናቸው። . . . ላባ ለልጁ ለልያ የሰጣት የዘለፋ ልጆች እነዚህ ናቸው፤ እነዚህን አሥራ ስድስቱንም ነፍስ ለያዕቆብ ወለደች። . . . ለያዕቆብ የተወለዱለት የራሔልም ልጆች እነዚህ ናቸው፤ ሁሉም አሥራ አራት ነፍስ ናቸው። . . . ላባ ለልጁ ለራሔል የሰጣት የባላ ልጆች እነዚህ ናቸው፤ እነዚህንም ለያዕቆብ ወለደችለት፤ ሁሉም ሰባት ነፍስ ናቸው።*

ዘዳ. 10፥22 *አባቶችህ ሰባ ነፍስ ሆነው ወደ ግብፅ ወረዱ፤ አሁንም አምላክህ እግዚአብሔር ብዛትህን እንደ ሰማይ ከዋክብት አደረገ።*

ኢያ. 8፥25 *በዚያም ቀን የወደቁት ሁሉ ወንድም ሴትም የጋይ ሰዎች ሁሉ አሥራ ሁለት ሺህ ነፍስ ነበሩ።*

በኢያ. 10፥28-39 በከተሞች ውስጥ ያሉ ነፍሳትን በሰይፍ ስለት ማጥፋታቸው ተጽፏል፤ ለምሳሌ፥ ቁጥር 32፥ *እግዚአብሔርም ለኪሶን በእስራኤል እጅ አሳልፎ ሰጣት፥ በሁለተኛውም ቀን ያዙአት፤ በልብናም እንዳደረጉት ሁሉ፥ እርስዋን በእርስዋም ያሉትን ነፍሳት ሁሉ በሰይፍ ስለት መቱአቸው።* ይላል። በሰይፍ ስለት የሙቱት ነፍሳቸውን ነው? ወይስ አካላቸውን፥ ሥጋቸውን? ግልጽ ነው። ነፍሳት ሲል ሰዎችን ማለቱ ነው። እንዲህ ያሉ በርካታ ጥቅሶች በቃሉ ውስጥ ተጠቅሰው ይገኛሉ።

ኤር. 52፥29-30 *ናቡከደነፆርም በአሥራ ስምንተኛው ዓመት ስምንት መቶ ሠላሳ ሁለት ነፍስ ከኢየሩሳሌም ማርኮአል፤ በናቡከደነፆር በሀያ ሦስተኛው ዓመት የዘበኞቹ አለቃ ናቡዘረዳን ከአይሁድ ሰባት መቶ አርባ አምስት ነፍስ ማርኮአል ሰዎች ሁሉ አራት ሺህ ስድስት መቶ ነበሩ።*

እነዚህ ሙሉ አካላዊ ማንነትን የሚያሳዩ ናቸው። እነዚህ ከላይ ያየናቸው ጥቅሶች የሰውን ስሜት፥ ፈቃድ፥ እውቀት መናገራቸው አይደለም። ሰውን በሙሉ ማንነቱ መናገራቸው እንጂ። በአዲስ ኪዳንም እንዲሁ ነው። ነፍስ የተሰኘው የግሪክ ቃል ψυχή ፕሱኬ በአዲስ ኪዳን ከ90 ጊዜያት በላይ ተጠቅሶአል። እዚህም ነፍስ የሰውን ሕያውነትም፥ ረቂቅ ወይም መንፈሳዊ (ኢቁሳዊ) ማንነትም፥ ሙሉ አካላዊ ማንነትንም ይወክላል። ሙሉ ማንነትን ከሚገልጡት መካከል ለምሳሌ፥

ሐዋ. 2፥41 *ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፥ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤*

ሐዋ. 27፥37 *በመርከቡም ያለን ሁላችን ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ነፍስ ነበርን።*

ሮሜ 13፥1 *ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ።* ነፍስ ነው ይገዛ የተባለው እንጂ *ሥጋ* አይልምና በሥጋዬ የወደድኩትን ማድረግ እችላለሁ ብሎ በሥጋው ወንጀል ሊሠራ የሚወድ መንፈስ ነኝ ባይ የለም። ነፍስ ሲል ጠቅላላውን ሰው ነው።

ነፍስ ጠቅላላው የሰው ሁለንተና ነፍስ እየተባለ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ ይገኛል። ነፍስ ጠቅላላውን ሰው ብቻ ሳይሆን ኢቁሳዊ ወይም ረቂቁን ማንነቱንም ወይም ሕያውነቱንም ያሳያል። ባለፈው በሞዴል አንድ ያየነው የዚህ አሳብ ገጽታ ነፍስ ወይም መንፈስ ወይም ነፍስና መንፈስ (ነፍፈስ) የውስጡን ማንነታችንን ወይም ሕያውነታችንን የሚያሳየው ገላጭ ቃል መሆኑን አይተን ነበር።

ነፍስ ወይም ነፍሳት ሲል ከሥጋ የተለዩ፥ ከሥጋ በሞት የተለዩ ሰዎችን ነፍሳትም ይገልጣል። ይህንን የሚያሳዩ ጥቅሶች አሉ። ለምሳሌ፥ ራእ. 6፥9 *አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ፥ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን*

*የሰዎች <u>ነፍሳት</u> ከመሠዊያ በታች አየሁ።* ይላል። እነዚህ ነፍሳት ከሥጋ የተለዩና ትንሣኤን ገና ያልተቀዳጁ በሞትና በትንሣኤ መካከል የሚገኙ ነፍሳት ናቸው። ይህን ያየው ዮሐንስ በራእዩ ቢሆንም እነዚህ ነፍሳት ሕያዋን መሆናቸው ገሃድ ነው። እነዚህ ነፍሳት በምድር በነበሩ ጊዜ ምስክር ወይም ሰማዕታት የሆኑ ሰዎች ናቸው፤ በታላቅ ድምጽ እየጮሁ ስለ በቀል ወይም ቅጣት ይጠይቃሉ፤ ነጭ ልብስ ተሰጣቸውም ይላል፤ እዚያው ራእ. 6፥10-11። ይህ በሞትና በትንሣኤ መካከል ያለው የነፍስ ማንነት ነው፤ ሕያውነት፥ መናገር መቻል፥ ስሜትና ፍትህን መጠየቅ፥ የሚያረጋጋ ነገር መስማትና መቀበል መቻል ይታያል። ይህ ብዙም በዝርዝር ያልተጻፈልን የሰው በሞትና በትንሣኤ መካከል የሚገኝ ማንነት ነው።

መንፈሶች ሲል ሰውን መንፈስ ማለቱ አድርገው የሚወስዱ አሉ። አንዳንዶች ዕብ. 12፥23 ላይ፥ *በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኵራት ማኅበር፥ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ እግዚአብሔር፥ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን <u>መንፈሶች፥</u> የአዲስም ኪዳን መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ፥ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደሚናገር ወደ መርጨት ደም ደርሳችኋል።* ተብሎ የተጻፈውን፥ 'ይኸው፥ መንፈሶች ይላል፤ ስለዚህ ሰው መንፈስ ነው' ይላሉ። አዎን መንፈሶች ይላል፤ ግን የምን መንፈሶች ነው የሚለው? የጻድቃን መንፈሶች ወይም የጸደቁ ሰዎች መንፈሶች እንጂ ጻድቃን የሆኑት ወይም የጸደቁት መንፈሶች ማለቱ አይደለም። ስለዚህ እዚህ መንፈሶች የሚለው ሰው መንፈስ መሆኑን አይመሰክርም። ይልቁንም መንፈሱ የጻድቃን መንፈስ ወይም በጻድቃን ውስጥ ያለው መንፈስ መሆኑን ነው የሚናገረው። ሰው መንፈስ ሳይሆን መንፈስ በሰው ውስጥ ያለ፥ የሰው የሆነ መሆኑን ነው የሚያሳየው።

ሰው መንፈስ ነው ካልን ሰውና መንፈስ፥ መንፈስና ሰው እኩል ናቸው እያልን ነን። ሰው ነፍስ አለው ካልን ማን ነው ነፍስ ያለው? ሰውየው ነው ወይስ መንፈስየው ነው ነፍስ ያለው? በሥጋ ውስጥ የሚያድረውስ ማን ነው? መንፈስየው ነው ወይስ ሰውየው ነው በሥጋ ውስጥ የሚያድረው? በሥጋ ውስጥ የሚያድር ከሆነስ ሥጋው ቀፎው ብቻ ነው ማለት ነው። ለሥጋ ያለን አመለካከት ሥጋ ቀፎ ብቻ ነው፤ ወይም በመጀመሪያው ትምህርት እንዳየነው ቱታ ብቻ ነው የምንል ከሆነ እግዚአብሔር አዳምን ሲፈጥር ያንን ቀፎ ወዲያ ጥሎ ወይም አስቀርቶ ሊፈጥረው አይችልም ነበር?

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ሰው እንጂ መንፈስ ሆኖ እንዲኖር እንዳልፈጠረው ማወቅ አለብን። አዳም በኃጢአት ባይወድቅ ኖሮ እኮ በዚያ ቀፎ ውስጥ፥ በዚያ ቱታ፥ በዚያ አካል ለዘላለም ሊኖር ነበር የተፈጠረው። ካላወቅነው እንወቅ፤ ከረሳን እናስታውስ። አዳም በመጀመሪያ ሲፈጠር ሰው በመሆኑ ምክንያት ሊሞት የሚችል ፍጡር ቢሆንም ሊሞት ግን አልነበረም የተፈጠረው። ሊሞት ካልነበረ ደግሞ ያ ሰውነቱ ዘላለማዊ ሊሆን የሚችል አካል ነበረ ማለት ነው። ከትንሣኤ በኋላም እኮ

አካል ይኖረናል፤ ያ አካል መንፈሳዊ አካል ይባላል፤ ያ አካል ከሌላ ቦታ የሚፈጠር አካል ሳይሆን ይህ ሰውነት፥ ይህ አሁን ያለንበት የተፈጠርንበት አካል፥ እነሱ ቱታ የሚሉት፥ ነው የማይሞትና የማይበሰብስ ሆኖ የሚነሣው። *ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፥ መንፈሳዊ አካል ይነሣል። ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ።* 1ቆሮ. 15፥ 44።

1ጴጥ. 3፥18-19 *ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፥ በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው፤* ይላል። ነፍሳት የሚለው ይህ ቃል ነፍሳት ሳይሆን መንፈሶች (πνεύμασιν) የሚል ነው። ይህ ጥቅስ ሰው መንፈስ ነው የሚሉ ሰዎች አድምቀው የሚጠቅሱት ቃልም ነው። ሰው መንፈስ ነው የሚሉትን አሳብ በከፊል የሚካፈል ይመስላል።

በዚህ ቃል ነፍሳት ወይም መንፈሶች ማለቱ ሰው መንፈስ ነው የሚለውን ትምህርት የማይደግፍ እንደሆነ ለመረዳት ሊቃውንት መሆን የለብንም። ጌታ ለነዚህ ሰዎች የሰበከው፥ *በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፥* ተብሎ ነው። ስለዚህ ሰባኪው ጌታ በመንፈስ ሕያው መሆኑ የመንፈሱን ሕያው መሆን ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ሕያው መሆኑን ወይም ከሙታን መነሣቱን መናገሩ ነው። እንጂ መንፈሱማ ሁሌም ሕያው ነው። መንፈስ አይሞትም። ሰው መንፈስ አለመሆኑን የምናውቅበት አንድ ነጥብ ሰው ሟች በመሆኑ ነው። የክርስቶስ መንፈስ አይሞትም። ጌታ ከሙታን መነሣቱን መጽሐፍ ቅዱን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ብቻ ሳይሆን የአብም የራሱ የወልድም ሥራ ያደርገዋል፤ ሮሜ. 6፥4፤ ዮሐ. 2፥18-22።

ይህ የሆነው ከሞቱ በኋላ እንደሆነ ያረጋግጥልናል። በትክክል መቼ መሆኑን አይገልጥልንም። ከትንሣኤው በፊት ነው ብንል እንኳ የተሰበከላቸው ነፍሳት ወይም መንፈሶች በሥጋ ያልሆኑ ሙታን ናቸው ማለት ነው። የሰዎች መንፈሶች ወይም የታሰሩ መላእክት ሊሆኑም ይችላሉ። ወይም ከታች ስለ ኖኅ ዘመን ስለሚናገር ለሙታን ሳይሆን ይህ ቃል በተጻፈበት ጊዜ በሕይወት ለሌሉ፥ ሙታን ለነበሩ፥ በኖኅ ዘመን ግን ሕያዋን ለነበሩት መናገሩ ነው የሚሉ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎችም አሉ። ይህ ከሆነ ደግሞ መንፈሶች የሚለው አገላለጥ ከላይ ነፍሳት የሚለውን ባየንበት አካሄድ ሊፈታ ይችላል። ሙሉው ሰው በብዙ ቦታዎች ነፍስ እንደተባለ ይህ ቦታም ሙሉውን ሰው መንፈስ አሰኝቶታል ማለት እንችላለን። ወንጌል ሰዎች ይድኑ ዘንድ ለሕያዋን ነውና የሚሰበከው፤ ከሞት በኋላ ፍርድ እንጂ ሌላ ዕድል አለመኖሩን ቃሉ በግልጥ ይነግረናል፤ ዕብ. 9፥22።

ቀደም ሲል እንዳልኩት፥ ማንነታችንን ካላወቅን ሌሎች የሚሉንን ሆነን ለመገኘትና የሚሰጡንን መታወቂያ ተቀብለን እንሆነዋለን። መንፈስ ነህ ሲሉን መንፈስ፥ አምላክ ነህ ሲሉን አምላክ፥ ትል ነህ ሲሉን ትል፤ ሰይጣን ነህ ሲሉን ሰይጣን፤ አንቺና አብ አንድ ናችሁ ሲሉን ነን፤ አይከብደንም። ኬነት ኮፕላንድ እግዚአብሔር ሰማያትን በስንዝሩ ስለለካበት አለካክ በፌዝ መልክ ከተናገረ በኋላ እግዚአብሔርን ከራሱ ቁመናና መጠን ጋር ሲያነጻጽር እንዲህ ብሎ ነበር፥ ". . . He is very much like you and me . . . A being that stands somewhere around 6'2," 6'3," that weighs somewhere in the neighborhood of a couple of hundred pounds, little better, [and] has a [hand]span nine inches across." ብሏል።[17] ትርጉም፤ 'እርሱ [እግዚአብሔር] ልክ እንደኔና እንዳንተ ማለት ነው። . . . ቁመቱ ወደ 6 ጫማ ከ2 ወይ ከ3 ኢንች [1ሜትር ከ90]፥ ክብደቱ ወደ 200 ፓውንድ [90 ኪሎ] ገደማ ነው፤ ሻል ያለ መስፈሪያ ልስጥ፤ የስንዝሩ ርዝመት ወደ 9 ኢንች [23 ሳንቲ ሜትር] ነው።' ብሎአል።

ኮፕላንድ ለእግዚአብሔር ቁመትና ክብደት፥ እንዲሁም ሰማያትን ስለለካበት የስንዝር ርዝመት ልኬት ለመስጠት ንጽጽሩን ያካሄደው ከራሱ ኮፕላንድ ከሚባለው ሰው ጋር ነው። የራሱን ቁመትና ክብደትና ስንዝር ከለካ በኋላ የእግዚአብሔርን ክብደት፥ ቁመት፥ የስንዝሩንም ርዝመት ከእርሱ ትንሽ በለጥ አድርጎት ማለት ነው ግምቱን የተናገረው። እርሱን ራሱን ከእግዚአብሔር በጣም ትንሽ አሳኖ ወይም እግዚአብሔርን ከራሱ ከኮፕላንድ በጣም ትንሽ ብቻ አስበልጦ ነው ልኬቱን ያስቀመጠው። የእግዚአብሔር 'ከላስ' መሆን እንዲህም ያደርጋል። ለዚህ ነው የቃል-እምነት ድውይ ትምህርት ድውያን ክርስቲያኖችን በየቀኑ እየፈጠረ ያለው።

## አሳቾች ንስሐ መግባት የለባቸውም?

በስሕተት ላይ ስሕተት፥ በማሳት ላይ ማሳት ሲጨምሩ ፍርሃት የለባቸውም። ድንግጥ አይሉም። አሳቾች ንስሐ የማይገቡት መሳሳታቸውን ካመኑ የገነቡት ጭድ የሌለው ምርጊት ስለሚፈረካከስባቸው ነው። ብዙዎቹ ስሕተታቸው በማያወላዳ መንገድ ሲነገራቸው፥ ቀድሞ ያሉትን ነገር ስሕተት ነው ሳይሉ በሌላ ይቀይሩታል። የለሰለሰ አሳሳች ቃላት ፈጥረው ዲፕሎማሲያዊ ቋንቋ በመጠቀም ኬላውን ሳይፈተሹ ለማለፍ ጥረት ያደርጋሉ።

---

[17] *በካሴት የተሰራጨ ትምህርቱ፤ Copeland, Spirit, Soul and Body I, side 1.*

ይህንን ትምህርት በተከታታይ በቪድዮ ማቅረብ ከጀመርኩ በኋላ ጥቂት ያልሆኑ ቪድዮዎች ከዩቲዩብ ተወግደዋል። ለምሳሌ፥ 'ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ በሥጋ ውስጥ ያድራል' የሚለው የፓስተር ዶ/ር ቶሎሳ ትምህርት የተሰራጨበት ቪድዮ በስፍራው የለም። ለጣፊው ብስራት ብዧየን ነው፤ አንሥቶታል፤ ለምን? ምናልባት አንሣ ተብሎ ይሆናል። ለምን? ስሕተት ስላለበትና ስም ለመጠበቅ። ይገርማል! ስም ነው መጥጠበቅ ያለበት? ወይስ ስሕተት ነው መስተካከል ያለበት? ሰዎቹ በስሕተታቸውና በማሳሳታቸው መጥጠየቅ አይፈልጉም፤ ንስሐ መግባት ያሳምማቸዋል፤ መልስ መስጠት ደግሞ ያስፈራቸዋል። ደግሞ፥ ስሕተቱ በአደባባይ ተለጥፏልና ማስተባበልም አይችሉም። ስለዚህ፥ ማስወገድ መፍትሔ ይመስላቸዋል።

ሐሰተኛ ነቢያት ሁሉም የሚያደርጉት ያንን ነው። የተሳሳቱበትን ነገር ተሳሳትኩ አይሉም፤ ለነገሩ ተሳስተው ሳይሆን አውቀው ነው የሚያጭበረብሩት፤ እና ተሳሳትን ማለት አይችሉም። ስለዚህ ጠልፈው ያወርዱታል። ሌሎች ከሰቀሉት ደግሞ ተከራክረውም ተደራድረውም ያስወርዱታል። ትምህርት ደግሞ ከዚህም የባሰ አውቀው የሚያደርጉት ነገር ነው። ተዘጋጅተውበት የሚያስተምሩት ነገር ነው እንጂ በድንገት የሚሉት ነገር አይደለም። ስለዚህ፥ ቄስ ዶ/ር ፓስተር ቶሎሳ፥ 'ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ በሥጋ ውስጥ ያድራል።' ያሉትን የቃለ እምነት የስሕተት ትምህርት ማብራሪያና ምንጩንም ቢያስረዱ መልካም ይመስለኛል፤ ቪድዮ ከማስወረድ ይልቅ። ግን የምንኖረው በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መሆኑንና እነሱ ሳያጠፉት በፊት ሌሎች አውርደው ግምጃ ቤታቸው እንደሚያስቀምጡት ማሰብም ቢችሉ መልካም ነው።

የቃለ-እምነት ትምህርት ቃለ-እምነት የተባለበት ምክንያት፥ የምንናገረው ቃል የመፍጠር ኃይል አለው ከሚለው የሳተ ትምህርታቸው መሆኑን ቀደም ሲል አይተናል። እግዚአብሔርም እንኳ ቃሉ ሰማይንና ምድርን የፈጠረለት ስላመነ ነው ይሉናል። እግዚአብሔር ቃሉን ስላመነ! እግዚአብሔር ከእርሱ የሚወጣውን፥ እርሱ ባይኖር ኖሮ ሊወጣ የማይችለውን፥ እርሱ በመኖሩ ምክንያት የወጣውን ቃሉን ስላመነ! ይደንቃል! እግዚአብሔር ባይኖር ኖሮ እኮ ቃሉ አይኖርም ነበር። ይህንን ማወቅ እንደዚህ ከባድ መሆን አልነበረበትም። የኔ ቃል ከኔ የሚወጣ ነው። እኔ ከቃሌ በፊት ነኝ፤ እኔ ባልኖር ቃሌ አይኖርም። ታዲያ እኔ ከኔ በኋላ የመጣውን፥ እኔ ባልኖር የማይኖረውን ቃሌን እኔ የማምነው እንዴት ነው? ሰውን ወደ እግዚአብሔርነት ቆጥ ሲሰቅሉ፥ እግዚአብሔርን ወደ ሰው ተራ ማውረዳቸውን ሳያውቁት ቀርተው አይደለም። ሳያውቁት ቀርተው ኖሮ ቢሆን ለመመለስ ጊዜ በሆነላቸው ነበር። ከእነዚህ ሰዎች በስሕተታቸው እየባሱ የሚሄዱ እንጂ ከዚያ የሚመለሱት በጣት የሚቆጠሩ ናቸው።

እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ነገሮች የፈጠረው እምነት ስላለው አይደለም። እምነትን ለመለማመድ እምነት የሚጣልበት አካል መኖር አለበት። ከአማኙ በላይ የሆነ አካል መኖር አለበት። እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ብቻውን ነው እምነታችንን የምንጥልበት የእምነታችን ማሳረፊያ አምላክ እንጂ፥ እርሱ እግዚአብሔር እምነቱን የሚያሳርፍበት ሌላ ምንም አካል የለም፤ አያስፈልገውምም። እርሱ አማኝ ከሆነ የሚያምነው አምላክ ያስፈልገዋል ልንል ነው። ወይም እኛም የምንለውን ቃል እንደ እርሱ ካመንን እንፈጥራለን ካልን እኛም መንፈስም እግዚአብሔርም ነን ልንል ነው። ፈጣሪ ነና! ይህ ነው ስሕተታቸው። ይህን ስሕተት ማመንና መቀበል ነበረባቸው።

ስለዚህ ጉዳይ Dave Hunt የተባለ የምካቴ ክርስትና ጸሐፊ፥ ይህ እግዚአብሔር ነገሮችን የፈጠረው በራሱ ቃል ስላመነ ነው የሚለው አባባል አመክንዮአዊ አለመሆኑን ከዘረዘረ በኋላ እንዲህ ብሎአል፤

> ለምሳሌ፥ 'ብርሃን ይሁን . . . ምድር ሳርና ቡቃያን ታብቅል . . .' ሲል የተፈጸመው እግዚአብሔር ስለተናገረው ሳይሆን <u>የተናገረው እግዚአብሔር ስለነበረ ነው።</u> ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ሰው ተመሳሳይ ቃላትን የፈለገውን ያህል ጊዜ ቢደጋግምም ምንም ነገር አይፈጠርም። በተጨማሪም፥ እግዚአብሔር በፈቃዱ ብቻ [ቃል ሳይናገር ማለት ነው] ነገሮችን መፍጠር ወይም ማድረግ ይችላል፤ የግድ መናገር የለበትም። ኃይሉ ያለው በእግዚአብሔር ውስጥ እንጂ በቃል ውስጥ አይደለም።[18]

ነገሮቹ የተፈጠሩት እግዚአብሔር ስለተናገረ ሳይሆን የተፈጠሩት ተናጋሪው እግዚአብሔር በመሆኑ ነው። ይህ ትምህርት አዲስ አለመሆኑን ይህ ከ30 ምናምን ዓመታት በፊት የታተመ የDave Hunt መጽሐፍ ይመሰክራል። እነዚህ፥ 'መናፍስት ነን' የሚሉ ሰዎች አንዳንዶቹ ሳይወለዱ፥ አንዳንዶቹ ገና ጡጦ ሲጥሉ የተጻፈ መጽሐፍ ነው። በእግዚአብሔር የተፈጠሩት ነገሮች፥ ሰማይ፥ ምድር፥ አየር፥ ባሕር፥ ዕጽዋት፥ እንስሳት፥ ሁሉም የተፈጠሩት እግዚአብሔር ቃል ስለተናገረ ሳይሆን (በእርግጥ ቃል ተናግሮ ነው የፈጠራቸው) እነዚህ ነገሮች የተፈጠሩት ያንን ቃል ተናጋሪው እርሱ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው! ይህንን አንርሳ። እርሱ እግዚአብሔር ስለሆነ ቢፈልግ በድምጽ ወይም በምልክት ተናግሮ፥ ባይፈልግ ሳይናገርም መፍጠር ይችላል። አስቦ ብቻም መፍጠር ይችላል። ሳያስብም መፍጠር ይችላል።

እኛ ደግሞ ሰዎች ስለሆንን፥ መደባችንም የሰው ስለሆነ ስንናገር ውለን ብናድርም፥ ብንባጅና ብንከርምም ምንም አንፈጥርም። ቀስ ብለን ወይም ጮኸን ብንናገርም አንፈጥርም። በምናውቀው ቋንቋም፥ በማናውቀው ልሳንም ብንናገርም አንፈጥርም።

---

[18] *Beyond Seduction,* pp. 55-56.

እኛ ፈጣሪ አይደለንም። እኛ የእግዚአብሔር 'ክላስ' አይደለንም። 'ሰው መንፈስ ነው፤ ሰው እግዜር ነው' ባዮች ከዚህ አሳችነታቸው ቢመለሱ እንዴት መልካም ነበር።

ይህ እነሱ የሚሉት ተናግሮ ወይም አምኖ መፍጠር የሚቻል ቢሆን ኖሮ የቃል-እምነት ሰባክያን የሚሹትን እየፈጠሩ የምስኪኖችን አማኞች መቀነትና ቦርሳና ኪስ ከማራቆት አፋቸውንና እጃቸውን በሰበሰቡ ነበር። የስግብግብነታቸው መለኪያ ቁንጮው ገንዘብ ነው አይደል? ትምህርታቸውም ከነስሙ የገንዘብ ወንጌል ወይም የብልጽግና ወንጌል ነው የሚባለው፤ አይደል? እና ገንዘብ መፍጠርና በሳጥንና በከረጢት መሙላት ይችሉ ነበር እኮ! ምነው አያደርጉ? ሐሰተኛ ነቢይ ኢዩ ጩፋ አንድ ቀን ብር እንደሚፈጥር ሰብኮ ድራማ ተሠራ። አንዲት የዋኅ እኅት ቦርሳዋ ውስጥ ያልያዘችውን ብር ማግኘቷንም መሰከረች። ግን የዋኅ ሳትሆን ወይ የተጭበረበረች ናት፤ ወይም ራሷም የድራማው ተዋናይት የሆነች አጭበርባሪ ናት! ብቻ ምን ያደርጋል? ብር 'የፈጠረበት' የቪድዮ ክሊፕ ላይ የሕንጻ ማሠሪያ መሬት ለመግዣ 4 ሚሊዮን ብር እንደሚያስፈልገው ልመና አቅርቦ የአካውንቱን ቁጥርም ጻፈ እንጂ! ውኃ ሲቸልስበት! ሌላ ጆይ ጨሮ የተባለ ሐሰተኛ ነቢይም ከምንጣፍ ውስጥ ብሮች 'ፈጥሮ' ነበር። ይህ አሳችነት ብቻ ሳይሆን ማጭበርበርም መሆኑን አውቀው ንስሐ ቢገቡ ምንኛ መልካም ነበር!

ይህ ማጭበርበር መሆኑን የምናውቀው፥ እግዚአብሔር አጭበርባሪ ባለመሆኑ ነው። እግዚአብሔር የሰውን የብር ከርስና ኮርጆ ለመሙላት የአገር ምጣኔ ሀብት የሚያጋሽብ የሐሰት ገንዘብ (forged money) የሚሠራ አምላክ አይደለም። ይህ ባሕርይው አይደለም። ሁለተኛ፥ እኛ አንፈጥርም፤ የሌለ ነገርን ካለመኖር ወደ መኖር አናመጣም፤ ያንን የሚያደርግ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እኛ ሰዎች እና ፍጡራን ነን። አራት ነጥብ። ነጥባችንም ይህ ነው፤ እኛ ሰዎች ነን፤ እኛ አምላክ አይደለንም፤ ፈጣሪዎች አይደለንም።

ኮፕላንድ የእግዚአብሔርን እና ሰውን አንድ መደብ (ክላስ) መሆን ሲናገር፥ "God's reason for creating Adam was His desire to reproduce Himself . . . Adam is as much like God as you could get, just the same as Jesus . . . Adam, in the Garden of Eden, was God manifested in the flesh." ትርጉም፤ 'እግዚአብሔር አዳምን የፈጠረበት ምክንያት ራሱን ማራባት [ማባዛት፥ ማምረት፥ መሥራት፥ መውለድ፥ መፍጠር፥ ኮፒ ማድረግ በሉት] ፈልጎ ነው። አዳም ልክ የኢየሱስን ያህል እቅጩን እንደ እግዚአብሔር ነው። በዔድን ገነት የነበረው አዳም

ማለት በሥጋ የተገለጠ እግዚአብሔር ነው።"[19] እግዚአብሔር ራሱን ሲያባዛ፥ ሲያራባ፥ ሲያመርት ይህንን ማሰብ የሚደንቅ ነው። እነዚህ ሰዎች ዘፍጥረት አንድ እና ሁለት ውስጥ የሚታየውን እግዚአብሔርን በራሳቸው መልክና ምሳሌ ፈጥረውታል።

ወፈፍ የሚያደርጋቸው እንደ ኃይሉ ዮሐንስ ያሉ ሰዎች፥ 'We are exactly like God' የሚሉት መፈክር ይህ ነው። ዘፍ. 1፥26 የሚለው፥ *እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን <u>በመልካችን እንደ ምሳሌአችን</u> እንፍጠር፤ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ።* እግዚአብሔር ኮፐላንድ እንዳሰበው፥ 'ራሳችንን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር' አላለም። ራሳችንን ካለማ 'በመልካችንና በምሳሌያችን' አይባልም። እራስ ነዋ የሚራባው። ይህ ያፈጠጠና ጥሬ ስሕተት ብቻ ሳይሆን፥ አደገኛ ስሕተት ነው። ከእንዲህ ያለው ስሕተት መመለስ ቢሆንላቸው ምንኛ መልካም ነበር!

አሳቾች የአማርኛ ተናጋሪዎች ሆነው በአማርኛ የማይጠቀሙት ለማደናገር ነው። 'We are exactly like God' ማለት ሙሉ በሙሉ፥ ሙቶ በሙቶ፥ ልክ እንደ እግዚአብሔር ነን ማለት ነው። ይህቺ ሙሉ በሙሉና ሙቶ በሙቶ ለአማርኛ ተናጋሪዎች በአማርኛ ስትነገር ትረብሻለች። ስለዚህ በልሳነ እንግሊዝ አጠናግረው የማደናገሪያ ርችት ተኩሰው ያመልጣሉ። በምን ያምታቱ? በምን ውሸቱን እውነት ያስመስሉ? በእንግሊዝኛ የሚናገሩበት ሌላው ምክንያት፥ ቀደም ሲል እንዳልኩት፥ የሰሙት በእንግሊዝኛ ስለሆነ፥ እነኮፐላንድ እንደ ሄግን የእንግሊዝኛ ተናጋሪዎች ስለሆኑ፥ ያንን እንደ በቀቀን መድገማቸውም ነው። ሌላ ደግሞ በምን አዋቂ ይምሰሉ?! በምን የረቀቀ፥ የተራቀቀና ከመደዴው አማኝ የራቀ አስተምህሮ ይፍጠሩ? ለዚህ ነው በአማርኛ እያስተማሩ እንግሊዝኛ የሚዶሉት።

[19] *በካሴት የተሰራጨ ትምህርቱ፤ Copeland, Following the Faith of Abraham I, side 1.*

## መደምደሚያ፤ ሰው ሰው ነው፤ ዛሬም ነገም፥ ለዘላለምም።

እኛ እግዚአብሔሮች ሳንሆን እግዚአብሔር በመልኩና በምሳሌው የሠራን ሰዎች እና ሰዎች ብቻ ነን። ፍጡራን ነን። ይህ ፍጡርነት ወይም ሰውነት ወይም ሰው መሆን፥ ልካችን ነው። ያልበዛብን፥ ያላነሰብን፥ ሠሪያችን፥ ፈጣሪያችን ሁሉን አዋቂው እግዚአብሔር በእውቀቱና በጥበቡ የፈጠረው ማንነታችን ነው። ከዚህ ሌላ በላጭ ወይም አናሳ አድርጎ ሊሠራን ቢወድድ ያደርግ ነበር። ግን ሰው አደረገን። ሰው ነን። ቀደም ሲል እንዳየነው፥ ሰው መሆናቸው አናሳ ማንነት መሆኑን ሰይጣን ነበር ለመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን በዔድን ገነት የነገራቸው። ዛሬም ሰው አይደለንም መናፍስት ነን፤ አማልክት ነን የሚሉን የማንን ጡሩምባ እየነፋልን መሆኑ ይገባን። የሰይጣን ማሚቶዎች እየሆኑ ነው።

በዔድን ገነት ሰይጣን ያለው፥ *እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ።* ነበር። ዘፍ. 3፥5። ሰይጣን፥ 'እንደ እግዚአብሔር' የሚለውን ማሳሳቻ ጨመረበት እንጂ የዛፉቱ ፍሬ እኮ መልካምና ክፉ ማወቂያ መሆኑ አስቀድሞም ተነግሯል። ዘፍ. 2፥9 እና 17 ያንን በግልጽ ይነግረናል። 'እንደ እግዚአብሔር እንድትሆኑ' በማለት ግን ከመምሰል ያለፈ ነውና የመምሰልን ወይም የመልክና ምሳሌን ሳይሆን የመሆንን ፍላጎት ተከለባቸው። ዛሬም፥ 'እንደ እግዚአብሔር ያለን፥ የእግዚአብሔር ክላስ' የሚሉት የማንን ግሳት እያገሱ እንደሆነ አንዘንጋ።

ሰውን በሥጋ ውስጥ ያድራል ሲሉ በሥጋ ውስጥ የሚያድር መንፈስ የሚያስኑ ሰዎች መንፈስ ወደሆነው እግዚአብሔር በማስጠጋት መለኮትን ለማቀዳጀት መጣራቸው ነው። ሰው መለኮት አይደለም፤ ሰው ሰው ነው። ክቡር ሰው። ያልሆነውን መለኮት ሊሆን የሞከረ አንድ ነበረ፤ አጥቢያ ኮከብ ይባላል። እርሱም አይወድቁ ውድቀት ወድቆ፥ እርሱ ያልሆነውን ማንነት ያኔ በዔድን ገነት የጀመረውን ሰውን የማመልኮት ጥረት ዛሬም ያደርጋል። በውጤቱ እንደርሱ ውዳቂ ሆነው እንዲቀሩ እንጂ እንደማይሆኑ ያውቃል፤ የሚያውቀው ደግሞ በሌላ በማንም ሞክሮ ሳይሆን በራሱ ተሞክሮ ነው።

ሰው እንደ መልክዓ እግዚአብሔርነቱ በዚህ አካል ሳለ ሰው ነው፤ ይህ አካሉ ፍጥረታዊ አካል ይባላል። በትንሣኤም አካል የሚሆነው፥ ከሙታን የሚነሣው አካል ሰው ነው። በትንሣኤም መንፈስ አይሆንም፤ አካል ይኖረዋል፤ ያ አካል መንፈሳዊ አካል ይባላል። *ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፥ መንፈሳዊ አካል ይነሣል። ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ።* 1ቆሮ. 15፥44። ከትንሣኤ በኋላም አካል አለ። ያ

አካል መንፈስ አይባልም ሰው ይባላል እንጂ። መንፈሳዊ አካል ይባላል እንጂ መንፈስ አይባልም።

ያ ለዘላለም የምንኖርበት አካላችንም እንኳ መንፈስ አይባልም። ራእ. 21፥3 እንዲህ ይላል፤ *ታላቅም ድምፅ ከሰማይ፦ እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል።* የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ያድራል ይላል እንጂ በመንፈሶች መካከል ያድራል አይልም። በትንሣኤ የሚነሣው ሌላ ሳይሆን ይኸው አሁን ያለን አካል ነው ተለውጦ የሚነሣው። ግን የማይሞት፥ የማይበሰብስ አካል ሆኖ ነው የሚነሣው። መንፈሳዊ አካል እንጂ መንፈስ ግን አይደለም። አሁን ብቻ ሳይሆን ከትንሣኤ በኋላም ሰው መሆናችን ይቀጥላል እንጂ የእግዚአብሔር 'ክላስ' አሁን አይደለንም፤ ኋላም አንሆንም። ባሕርይ እና ማንነት ልዩነት አላቸውና ከመለኮታዊ ባሕርይው ተካፋዮች መሆናችን መለኮት ወይም መለኮታውያን አያደርገንም። ይህን ቀደም ሲል በሰፊው ተመልክተናል። የሰው ሰውነት ወይም የሰው ማንነት፥ ማን መሆን ዘላለማዊ ነው።

ይህን አሳብ ስደመድም ይህን ልበል። ይህ ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ ያለው በሥጋ ውስጥ የሚኖር የሚለው ትምህርት አዲስ ትምህርት አይደለም። ማወሳሰባቸውም መራቀቅ አይደለም፤ ሰውን መንፈስ ነህ ካሉት በኋላ አምላክ ነህ ለማለት ምርኩዝ ማቀበላቸው ነው። 'ሰው መንፈስ ነው' የሚሉትና የሚያስብሉት፥ 'ሰው መንፈስ ስለሆነ፥ ሰው እግዚአብሔር ነው፤' ለማሰኘት ነው። ይህን የሚያስተምሩት ሰዎች አዳዲስ ይሆናሉ እንጂ ትምህርቱ የነበረ፥ ያረጀ፥ የደረጀ፥ ዕድሜ የጠገበ፥ ብዙ ሺህ ዓመት ያስቆጠረ ነው። ምንጩም ዔድን ገነት ነው፤ ጀማሪው ሔዋንን ያሳተው የቀደመው እባብ የተባለው ሰይጣን ነው። ይህ ትምህርት ገና ከመጀመሪያ ወላጆቻችን ጀምሮ የነበረ፥ ያረጀ፥ ግን ቡትቶውን አድሶ የመጣ አጋንንታዊ ትምህርት ነው።

እነዚህ ሰውን መንፈስ ነው የሚሉ ሰዎች መንፈስ አቀባዮች ናቸው። ያላገኘነውን ልዩ መንፈስ ሊያቀብሉን የሚጥሩ ሰዎች ናቸው። በዚያውም ሌላ ኢየሱስ ሊያቀብሉን የሚጥሩ ሰዎች ናቸው። በ2ቆሮ. 11፥3-4 ቃል እጨርሳለሁ፤ *ነገር ግን እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት፥ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ። የሚመጣውም ያልሰበክነውን ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክ፥ ወይም ያላገኛችሁትን ልዩ መንፈስ ወይም ያልተቀበላችሁትን ልዩ ወንጌል ብታገኙ፥ በመልካም ትታገሡታላችሁ።*

ሌላ ኢየሱስ፥ ልዩ መንፈስ፥ ልዩ ወንጌል አለ። እንዲህ ያሉ ስሕተቶችን አንታገሥ።

## ዋቢዎች


ግርማዊ፤ *የበልጸግና ወንጌል፤* አዲስ አበባ፤ 2000 ዓ. ም. ፡፡

ዘላለም መንግሥቱ፥ *ሰው ምንድርነው? ሰው መንፈስ ነው? ሰው ትንሽ እግዜር ነው? ወይስ ሰው ሰው ነው? የመጽሐፉ ዋና ምንጭ የሆነው የቪድዮ ተከታታይ ትምህርት፤ 2020፡፡*

ክፍል አንድ፤ https://www.youtube.com/watch?v=bdJAtfPPVwk
ክፍል ሁለት፤ https://www.youtube.com/watch?v=Sbw16fJP0nc
ክፍል ሦስት፤ https://www.youtube.com/watch?v=9KeVA1-uHpk
ክፍል አራት፤ https://www.youtube.com/watch?v=Xv1aU00N_xU
ክፍል አምስት፤ https://www.youtube.com/watch?v=PR2W01Wab_k
ክፍል ስድስት፤ https://www.youtube.com/watch?v=YjyCEau9hLY
ክፍል ሰባት፤ https://www.youtube.com/watch?v=xK2BSEElE7c

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፤* አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ፤ 1948 ዓ. ም.፡፡

ደስታ ተክለ ወልድ፤ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፤* አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ፤ 1962 ዓ. ም.፡፡

ጳውሎስ ፈቃዱ፤ *ደ'ም የእግዚአብሔር ኢቻ ሆንን!?* መጣጥፍ፡፡

ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ፤ ፕሮፌሰር *የኦሮሞ እና የአማራ እውነተኛ የዘር ምንጭ ፥* Nebadan Publications 2008 ዓ. ም. አዲስ አበባ፤ ገጽ 140-44 እና 268-71፡፡

Copeland, Spirit, Soul and Body I, side 1. በካሴት የተሰራጨ ትምህርቱ፡፡

Copeland, Following the Faith of Abraham I, side 1. በካሴት የተሰራጨ ትምህርቱ፡፡

Copeland, K. *Our Covenant with God*, Harrison House, Tulsa OK. 1976.

Exodus TV Show፡ https://www.youtube.com/watch?v=DaSXi8EKlKk

Guzik, David. *David Guzik's Commentary on the whole Bible;* electronic version.

Hoekema, Anthony A. *Created in God's Image,* Wm. B. Eerdmans Publishing Company, 1986. Database 2009 WORD*search* Corp. Electronic Version

Hunt, Dave. *Beyond Seduction,* Harvest House Publishers, Eugene, OR. 1986.